# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 224 ሚያዝያ 14 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












ፎቶ፡ ሐዲስ አብርሃ

# ከሥራ ጠባቂነት ወደሥራ ፈጣሪነት

አስቴር ኤልያስ

ዜና ሐተታ

እጅ ካልቦዘነ ሥራ አይጠፋም እንደሚባለው በኦሮሚያ ክልል በሸገር ከተማ አስተዳደር፣ በገላን ጉዳ ክፍለ ከተማ በተለያየ ሴክተር ተደራጅተው ወደሥራ የገቡ ማኅበራት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሥራ ጠባቂነት ወደሥራ ፈጣሪነት እየተሸጋገሩ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

ቀደም ሲል ቋሚ ሥራ ያልነበራቸውና ገሚሱም በቤት እመቤትነት ኑሯቸውን ይገፉ እንደነበር የሚናገሩት በማኅበር የተደራጁ ዜጎች፣ በአሁኑ ወቅት ግን በገላን ጉዳ ማዘጋጃ ቤት አማካይነት በተገነባላቸው ሼዶች ውስጥ በማኅበር ተደራጅተው ሥራ ከጀመሩ ከአንድ ወር በላይ እንደሆናቸው ያስረዳሉ። በአጭር

ከሥራ ጠባቂነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# አምስት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ወደክልሉ ገብቷል

አመለወርቅ ከበደ

አዲስ አበባ፡- ለዘንድሮ የምርት ዘመን አምስት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ወደ ክልሉ መግባቱን የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ። 100 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የተፈጥሮ ማዳበሪያ መዘጋጀቱም ተገልጿል።

የቢሮው ምክትል ኃላፊ አቶ በሪሶ ፋይሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዘንድሮ ዓመት የምርት ዘመን አምስት ሚሊዮን የአፈር ማዳበሪያ ወደ ክልሉ ገብቷል።

በዘንድሮ ዓመት ለበልግና ለመኸር ምርቶች ስምንት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለማግኘት መታቀዱን አስታውሰዋል።

የግዢ ሂደቱ በግብርና ሚኒስቴር በኩል የሚፈጸም እንደመሆኑ ለኦሮሚያ ክልልም የሚያስፈልገው ቀርቧል፤ በዚህም እስካሁን አምስት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ከወደብ ተጓጉዞ ወደ ክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች ገብቷል ብለዋል።

እንደ አቶ በሪሶ ገለጻ፤ ወደ ክልሉ ከገባው የአፈር ማዳበሪያ ከአንድ ሚሊዮን ኩንታል በላይ የሚሆነው በማኅበራት በኩል ለአርሶ አደሮች ተሰራጭቷል።

ከክልሉ ስፋት አንጻር የደረሰው የአፈር ማዳበሪያ በቂ ባይሆንም የተፈጥሮ ማዳበሪያ የማዘጋጀት ሥራም

አምስት ሚሊዮን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# ከወጪ ንግድ ሁለት ነጥብ 16 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ተገኘ

ማሕሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ስምንት ወራት ውስጥ ከወጪ ንግድ ሁለት ነጥብ 16 ቢሊዮን ዶላር መገኘቱን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያ አቶ ተስፋዬ ታደሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በበጀት ዓመቱ ስምንት ወራት ኤክስፖርት ከተደረጉ የወጪ ንግድ ምርቶች ሦስት ነጥብ 14 ቢሊዮን ዶላር

ከወጪ ንግድ ሁለት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# በአዲስ አበባ በትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ ከአራት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር በላይ ተንቀሳቅሷል

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- በትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ ከአራት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር በላይ መንቀሳቀሱን የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ፡፡ በማኅበር ለተደራጁ ከ35 ሺህ በላይ መምህራን ለቤት መሥሪያ የሚሆን ቦታ ከተማ አስተዳደሩ እንደሚያቀርብ ቢሮው ጠቁሟል።

የቢሮው ኃላፊ ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ቢሮው በሚያከናውነው የትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ ዕቅድን መሠረት በማድረግ በትምህርት ተቋማት ውስጥ በገንዘብ፣ በእውቀት፣ በጉልበት፣ በአይነት በመለየት ከአራት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር በላይ ተንቀሳቅሷል፡፡

ንቅናቄው በትምህርት ቤቶች አካባቢ ያሉ በርካታ ችግሮች ለመፍታት አግዟል

በአዲስ አበባ በትምህርት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# በምስራቅ ሸዋ ዞን 11 ሚሊዮን ኩንታል የበጋ መስኖ ስንዴ ምርት ተሰብስቧል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በዞኑ ዘንድሮ በበጋ መስኖ የለማ 11 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት መሰብሰቡን በኦሮሚያ ክልል የምሥራቅ ሸዋ ዞን ግብርና ጽሕፈት ቤት ቢሮ አስታወቀ፡፡

የዞኑ የግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ መስፍን ተሾመ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዞኑ የግብርና ሥራን በሁለት ከፍሎ እየሠራ ይገኛል፡፡ የመጀመሪያው ለሀገር ኢኮኖሚ ተጠቃሚ ናቸው በተባሉ ዘርፎች ላይ በንቅናቄ የሚሠራ ሲሆን ሌላኛው መደበኛ የግብርና ሥራ ነው ብለዋል፡፡

ዞኑ በስፋት የሚያመርተውን የስንዴን ምርት ይበልጥ ለመጨመር የበጋ መስኖ ስንዴን ማልማት ከጀመረ አምስት ዓመት ሆኖታል ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ የበጋ ስንዴ በየዓመቱ በመሬት ሽፋን፣ በጥራት እንዲሁም በምርት ብዛቱ እየጨመረ መጥቷል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በዘንድሮ የበልግ ወቅት 350 ሺህ ሄክታር መሬት በበጋ ስንዴ ለመሸፈን ታቅዶ 389 ሺህ ሄክታር መሬት ማልማት ተችሏል ብለዋል ፡፡

ምርት የመሰብሰብ ሥራው እየተከናወነ መሆኑን የገለጹት አቶ መስፍን፤ አጠቃላይ 14 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት ለማግኘት ታቅዶ እስካሁን 11 ሚሊዮን ኩንታል መሰብሰብ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

ከዚህ ውስጥ ትላልቅ ክላስተሮችን በመምረጥ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ምርት የመለየት ሥራም ተከናውኗል ሲሉ አስረድተዋል።

ሰብል ከተሰበሰበ በኋላ አርሶ አደሩ ምን ማድረግ አለበት የሚለው ቅድመ ዝግጅት መደረጉን አንስተው፤ በእቅዱ መሠረት ሁለት ሺህ አርሶ አደሮች ወደ ኢንቨስትመንት ማሸጋገር እንዲሁም አርሶ አደሩ ከሚያገኘው ገቢ 35 በመቶ እንዲቆጥብ መደረጉን ተናግረዋል፡፡

እስካሁን አርሶ አደሩ ስምንት ቢሊዮን ብር እንዲቆጥብ መደረጉን ገልጸው፤ በተቆጠበው ብርም 178 ትራክተሮች እና ሦስት ኮምባይሮችን መግዛቱን ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ መስፍን ገለጻ፤ የአትክልትና ፍራፍሬው ልማት ዞኑ በስፋት የሚታወቅበት ነው፡፡ በተለይም የአቮካዶ ምርትን በጥራትና በብዛት በማምረት ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን ምርት መጠኑን ለማሳደግ እየተሠራ ይገኛል፡፡

በዚህ ዓመትም 300 ቶን ምርት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ እስካሁን 60 ቶን ለውጭ ገበያ ማቅረብ ተችሏል ብለዋል፡፡



የአቮካዶ ምርት ሲጀመር በሁለት ወረዳዎች ብቻ እንደነበር ያስታወሱት ኃላፊው፤ አሁን በዞኑ ባሉ ሁሉም ወረዳዎች እየተመረተ እንደሚገኝ ገልጸዋል ፡፡

በዞኑ ትኩረት እና ቁጥጥር የሚሻው ጉዳይ የገበያ ትስስር ነው ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ ምርት የመደበቅ እና ደላሎች ገበያው ላይ ጣልቃ መግባት ሥራው ላይ ችግር እየፈጠረ መሆኑን ጠቁመዋል።

ዞኑም ይህን ለመቆጣጠር ከባለድርሻ አካላት ጋር የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ማከናወኑን ገልጸው፤ ይህም በቂ ባለመሆኑ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

# በመዲናዋ ከ26 ሺህ በላይ ዜጎች ከጎዳና ተነስተዋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ከ26 ሺህ በላይ ዜጎች ከጎዳና በማንሳት የተሻለ ሕይወት እንዲኖራቸው መሠራቱን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሴቶች ሕጻናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ አስታወቀ።

በቢሮው የማኅበራዊ ሴፍቲኔትና ኑሮ ማሻሻል ዳይሬክተር አቶ ቢኒያም ግርማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመዲናዋ ባለፉት ዘጠኝ ወራት በከተማ አስተዳደሩና ዓለም ባንክ አማካኝነት ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ያደረጉ 26 ሺህ 671 ዜጎችን እንዲነሱ ተደርጎ የተሻለ ሕይወት እንዲኖራቸው ጥረት ተደርጓል።

ከአጠቃላዩ ከጎዳና ከተነሱ ዜጎች መካከል 20 ሺህ 740ው በከተማ አስተዳደሩ አማካኝነት ከጎዳና የተነሱ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ከዚህ ውስጥ 15 ሺህ 264 ወንዶችና አምስት ሺህ 476ቱ ሴቶች እንደሆኑ አስረድተዋል። በዓለም ባንክ ድጋፍ ደግሞ በከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔትና ሥራ ፕሮጀክት አማካኝነት አምስት ሺህ 931 ዜጎች ከጎዳና መነሳታቸውን አመላክተዋል።

ባለፉት ዘጠኝ ወራት አምስት ሺህ 931 ዜጎች በከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔትና ሥራ ፕሮጀክት አማካኝነት ከጎዳና ሕይወት እንዲወጡ ተደርጓል ያሉት አቶ ቢኒያም፤ አንድ ሺህ 451 ሕጻናትን የያዙ እናቶችን፣ አንድ ሺህ 812 ወጣቶች እንዲሁም ሁለት ሺህ 101 ሕጻናትና 567 አረጋውያን ናቸው ብለዋል።

ዜጎች በሥራ ዕድል ፍለጋ፣ በአቻ ለአቻ ተፅዕኖ፣ ቤተሰቦቻቸውን በሞትና በተለያዩ ምክንያቶች ሲያጡ ለጎዳና ሕይወት እንደሚዳረጉ ጠቅሰው፤ በተለይም የኢኮኖሚ አቅም ዝቅተኛ መሆን፣ በሀገሪቱ በነበረው ግጭት ችግሩን ካስፋፉ ምክንያቶች መካከል ዋነኞቹ መሆናቸውን አስረድተዋል።

ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ዜጎች ለአደንዛዥ ዕፅ ተጋላጭ እንደሚሆኑና ለአስገድዶ መደፈር ችግሮች ተጋላጭነታቸው እንደሚጨመር ገልጸው፤ ዜጎችን የማቋቋም እንዲሁም ወደ መጡበት ማኅበረሰብ የመመለስ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አመላክተዋል።

በዓለም ባንክ ድጋፍ ዜጎችን ወደ መጠለያዎች በማስገባት ተገቢውን የሕይወት ክህሎትና አጫጭር ቴክኒክና ሙያ ሥልጠናዎች ይሰጣሉ ያሉት አቶ ቢኒያም፤ ወደ ማኅበረሰቡ በማቀላቀል እራሳቸውን ችለው እንዲኖሩ የማድረግ ሥራዎች ይሠራል ብለዋል።





በመዲናዋ ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ካደረጉ ዜጎች መካከል ልጅ የያዙ እናቶች፣ ወጣቶች፣ ሕጻናትና አረጋውያን እንደሚገኙ ጠቅሰው፤ ከ20 አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በመሆን ከሦስት እስከ ስድስት ወር የሚቆይ የሕይወት ክህሎት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠናዎችን መሰጠቱን ገልጸዋል።

በ2014 ዓ.ም በተደረገ ጥናት በመዲናዋ ከ50 ሺህ በላይ ውሎና አዳራቸውን በጎዳና ላይ ያደረጉ ዜጎች መኖራቸውን የተናገሩት አቶ ቢኒያም፤ ችግሩን ለመቅረፍ የችግሩን መነሻዎች ለይቶ ከምንጩ መፍትሔ መስጠት እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

# በድሬዳዋ በመስኖ በዓመት ሁለቴ ማምረት የሚቻልበት ዕድል ተፈጥሯል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በድሬዳዋ ከተማ የመስኖ መሠረተ ልማቶችን በማስፋፋት የአካባቢው አርሶ አደር በዓመት ሁለት ጊዜ ማምረት የሚችልበት ዕድል መፈጠሩን የከተማ አስተዳደሩ ግብርና፣ ውሃ፣ ማዕድን እና ኢነርጂ ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮ ኃላፊው ኃላፊ አቶ ኑረዲን አብደላ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የድሬዳዋ አካባቢዎች ዝናብ አጠር ናቸው። ይህንን ችግር ሊቀርፍ የሚችል የመስኖ መሠረተ ልማቶችን የማስፋፋት ሥራ በትኩረት እየተሠራ ነው። ይህ የመስኖ ልማት ሥራም በዓመት ሁለቴ ማምረት የሚቻልበት ዕድል ተፈጥሯል፡፡

በድሬዳዋ ከተማ የመስኖ መሠረተ ልማቶችን በማስፋት የአካባቢው አርሶ አደር በዓመት ሁለት ጊዜ ማምረት የሚችልበት ዕድል ተፈጥሯል ያሉት አቶ ኑረዲን፤ በዚህም ከአምስት ሺህ 300 ሄክታር በላይ መሬት በመስኖ እንዲለማ ተደርጓል ብለዋል።

በመስኖ ልማቱ ብርቱካን፣ ማንጎ፣ ፓፓያ እና ሌሎችም ምርቶች እየለሙ ይገኛሉ ያሉት አቶ ኑረዲን፤ በተሠሩት የመስኖ ልማቶች ላይ የከርሰ ምድር ውሃን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ እየተከናወነ እንደሆነ ገልጸዋል።

በተለይ ብዙ ምርት ሊሰጡ የሚችሉ ዘሮችን በመጠቀም እና ለአርሶ አደሩ ትምህርትና ሥልጠና በመስጠት በፍራፍሬና በአትክልት ዘርፍ ውጤታማነትን የማጠናከር ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ገልጸው፤ የአፈር ማዳበሪያ፣ የውሃ መሳቢያ ሞተርን (ፓምፕን) ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ የግብርና ግብዓቶችን የማሟላት ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

በየዓመቱ አዳዲስ የመስኖ መሠረተ ልማቶችን በማስፋት ረገድ በዓመት ቢያንስ 200 ሄክታር መሬት በመስኖ እንዲለማ ይደረጋል ያሉት አቶ ኑረዲን፤ ከተማ አስተዳደሩ የከርሰ ምድር ውሃ ሀብት ልማት ላይ ጥናት በማድረግ ለአርሶ አደሩ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝም ተናግረዋል።

የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር አራት የገጠር ወረዳዎች ያሉት ሲሆን በእነዚህ ወረዳዎች የግብርናውን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን ቢሮ ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ የመስኖ መሠረተ ልማቶችን የማስፋት ሥራ እንደሀገር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት እንደሚያጠናክርም ገልጸዋል።

በድሬዳዋ ቆላማ አካባቢዎች አምና 68 ሄክታር መሬት ላይ ስንዴ ለማልማት በተደረገው ሙከራ ውጤት መገኘቱን የገለጹት አቶ ኑረዲን፤ ይህን ለማስፋት ከምርምር ተቋማት ጋር በትብብር እንደሚሠራም አመልክተዋል።

# "ውድድሩ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉን በማስተዋወቅ ረገድ የላቅ ሚና አለው"

- አቶ መላኩ አለበል
የኢንዱስትሪ ሚኒስትር

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ታምርት የጎዳና ላይ ውድድር አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉን በማስተዋወቅ ረገድ የተጫወተው ሚና ላቅ ያለ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ገለጹ። የኢትዮጵያ ታምርት የ10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫ ትናንትና በመስቀል አደባባይ ተካሂዷል።

የጎዳና ላይ ሩጫ ውድድሩን ያስጀመሩት የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል በወቅቱ እንደገለጹት፤ ውድድሩ አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉን በማስተዋወቅ ረገድ የሚጫወተው ሚና ላቅ ያለ ነው።

የውድድሩ ዓላማ በኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ተመርተው ለዓለም አቀፍ ክለቦች የሚቀርቡ ትጥቆችን ለማስተዋወቅ ነው ያሉት አቶ መላኩ፤ የአምራች ዘርፉን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሀገር ውስጥ ምርትን ማስተዋወቅና ጤናማ ሠራተኛ ሊኖር ይገባል ብለዋል። ለዚህም በውድድሩ 80 በመቶ የሚሆኑት ተወዳዳሪዎች አምራች የኢንዱስትሪ ሠራተኞችና የዘርፉ ተዋናዮች እንዲሆኑ መደረጉን አንስተዋል።

አምራች ኢንዱስትሪዎች በዓይነት፣ በጥራትና በመጠን ምርቶቻቸውን እያሳደጉ መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ በዘርፉ የሚከናወኑ ውጤታማ ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት አትሌት ገዛኸኝ አበራ በበኩላቸው፤ ውድድሩ የኢትዮጵያን ምርቶችን ለብዙኃኑ ለማስተዋወቅ አማራጭ መንገድ ሆኗል።



በኢትዮጵያ የሚገኙ አምራች ድርጅቶች ምርቶቻቸውን በአትሌቲክስ ዘርፍ ቢያስተዋውቁ በርካታ ሰዎችን በቀላሉ ተደራሽ ማድረግ ይችላሉ ብለዋል።

የኢትዮጵያ ታምርት ሩጫ ውድድር አትሌቶች ልምዳቸውን የሚያካብቱበትና ተተኪ አትሌቶች የሚገኙበት ዕድልን እንደሚፈጥርም ተናግረዋል።

ትናንት በተካሄደው የኢትዮጵያ ታምርት የ10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫ በወንዶች አትሌት ገመቹ ዲዳ 1ኛ፣ አትሌት ሌሊሳ ኩማ 2ኛ፣ አትሌት መዝገቡ ስሜ 3ኛ ደረጃን ይዘው አጠናቀዋል።

በሴቶች ደግሞ አትሌት ጌጤ አለማየሁ 1ኛ፣ አትሌት መብራት ግደይ 2ኛ፣ አትሌት ፀሐይነሽ ከፈለ 3ኛ ደረጃን ይዘው ነው ያጠናቀቁት።

በወንዶች አንደኛ ደረጃን ይዞ ያጠናቀቀው የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚው አትሌት ገመቹ ዲዳ ለኢፕድ እንደገለፀው፤ ውድድሩ በፉክክር የተሞላና ለተተኪ አትሌቶች ዕድል የሚሰጥ ነው። የአትሌቶች ቁጥር በጨመረ ቁጥር በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች ለቀሪው ዓለም ለማስተዋወቅ ይረዳል ብሏል።

በውድድሩ የሴቶች አሸናፊና የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ አትሌት ጌጤ አለማየሁ በበኩሏ፤ ተተኪ አትሌቶችን መሠረት ያደረጉ የሩጫ ውድድሮች ማስፋፋት ይገባል፤ ይህም የሀገር ውስጥ ውድድርን ከማበረታታት ባለፈ ጤናማና ንቁ ሠራተኞች በተቋማት እንዲኖሩ ይረዳል ብላለች።

በውድድሩ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ የወጡት ተወዳዳሪዎች ከሜዳሊያ በተጨማሪ እንደየቅደም ተከተላቸው የ250 ሺህ ብር፣ የ150 ሺህ ብር እና የ100 ሺህ ብር ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

ውድድሩን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በጋራ አዘጋጅተውታል። በጎዳና ላይ ሩጫው ከ10ሺ በላይ ግለሰቦች እና ከ27 ክለቦች የተወጣጡ 538 አትሌቶች የተሳተፉ ሲሆን ከዚህ ቀደም በ2015 ዓ.ም በ5 ኪሎ ሜትር ሩጫ በእንጦጦ ፓርክ መደረጉ ይታወሳል።

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሚያዚያ 29 ቀን 2014 ዓ.ም መጀመሩ ይታወቃል። ንቅናቄው ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሃገር ውስጥ ለማምረት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የውጭ ምንዛሪ ወጪን በማዳን ውጤት እያስገኘ መሆኑ ተመላክቷል።



ሂሩት ካሣው(ዶ/ር)

## የመስተንግዶ ባለሙያዎች
### የአለባበስ ኮድ መመሪያ ዝግጅት በመጠናቀቁ በቅርቡ ፀድቆ ተግባራዊ ይሆናል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡ በሆቴሎች የሚሠሩ ሴት የመስተንግዶ ባለሙያዎች ከሀገሪቱ ባሕል ውጪ የሆነውን አለባበሳቸውን ለማስተካከል የሚያስችል የአለባበስ ኮድ መመሪያ ዝግጅቱ በመጠናቀቁ በቅርቡ ፀድቆ ተግባራዊ እንደሚደረግ የአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ገለጸ።

የአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ሂሩት ካሣው (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአንዳንድ ሆቴሎች የሴት መስተንግዶ ሠራተኞች አለባበስ ከሀገሪቱ ባሕል ወጣ ያለ ነው።

ይህን ለማስተካከል የሚረዳ የመስተንግዶ ባለሙያዎች የአለባበስ ኮድ መመሪያ ዝግጅቱ ተጠናቆ ለከንቲባ ጽሕፈት ቤት እንዲፀድቅ በመላኩ መመሪያው በከተማዋ ካቢኔ በቅርቡ ፀድቆ ተግባራዊ እንደሚደረግ ይጠበቃል ብለዋል።

ለቱሪስቶች መስተንግዶ ሲሰጥ የሀገራችንን ባሕልና እሴት በጠበቀ መልኩ መሆን አለበት ያሉት ኃላፊዋ፤ በሆቴሎች ያለው የመስተንግዶ ባለሙያዎች አለባበስ ሥነ-ሥርዓቱን የጠበቀ መሆን እንዳለበት ተናግረዋል።

ሂሩት (ዶ/ር)እንዳመላከቱት፤ አሁን ላይ የመስተንግዶ ባለሙያዎች በተለይም ሴቶች በአንዳንድ ሆቴሎች አማካኝነት ሥነ-ሥርዓቱን ያልጠበቀ አለባበስ እንዲለብሱ ይገደዳሉ። ድርጊቱ ከሴት ልጅ መብት አኳያ ክብርን ያልጠበቀ እና አሳፋሪ ነው ብለዋል።

መመሪያው ፀድቆ ሥራ ላይ ሲውል በሆቴሎች የሚሠሩ የመስተንግዶ ባለሙያዎች ወጥ የሆነ ዓለማቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የአለባበስ ኮድ እንዲከተሉ ይደረጋል ያሉት ኃላፊዋ፤ ይህም የኢትዮጵያን ባሕልና ወግ ያልጠበቀ የአለባበስ ሥነ ሥርዓትን ለመቆጣጠር እንደሚያስችል አስረድተዋል።

አሁን ላይ በአንዳንድ ሆቴሎች የሚታየውን ከባሕል ያፈነገጠ የመስተንግዶ ባለሙያዎች አለባበስ መስተካከል እንዳለበት የከተማው ነዋሪዎች ጥያቄ እንደሚያቀርቡ ገልጸው፤ መመሪያው ሲፀድቅ የሁሉንም ጥያቄ እንደሚመልስ አብራርተዋል። ሕጉ ከፍተኛ የገንዘብ ቅጣትም ጭምር ያለው በመሆኑ መመሪያውን በሚተላለፉ ላይ ቅጣት እንደሚጣል ጠቁመዋል።

የአለባበስ መመሪያውን ለማውጣት ቢሮው ሁለት ዓመት ሲሠራ መቆየቱን ተናግረው፤ ሕጉ ከፀደቀ በኋላ ወደ ርምጃ እንደሚገባ አመላክተዋል። ሕጉ እስኪፀድቅ የቁጥጥር ሥራ የሚሠራ ሲሆን በሚደረገው ክትትልና ድጋፍም አሁን ላይ ለውጦች መኖራቸውን ተናግረዋል።

በቱሪዝም ዘርፉ ውድድር በዓለም አቀፍ ይዘት ያለው በመሆኑ ደረጃውን ያልጠበቀ መስተንግዶ የሚሰጥ ከሆነ ቱሪስቶች ተመልሰው እንደማይመጡ የሚገልጹት ሂሩት (ዶ/ር)፤ በሆቴሎች መልካም መስተንግዶ እንዲሰጥ ለማስቻል ቢሮው በየዓመቱ ሁለት ሺህ ለሚደርሱ በሥራ ላይ ላሉ መስተንግዶ ሰጪ ባለሙያዎች ሥልጠና እንደሚሰጥ አስታውቀዋል።

በከተማዋ ያሉ ዓለም አቀፍ ሆቴሎች የመስተንግዶ ባለሙያዎቻቸው አለባበስ ጥሩ መሆኑን ጠቅሰው፤ በመጠኑ ከሴት የመስተንግዶ ባለሙያዎች የፀጉር አያያዝ ሥነ-ሥርዓት ጋር በተያያዘ የማይፈቀዱ ነገሮች በአንዳንድ ሆቴሎች የሚታዩ በመሆኑ እንዲሻሻሉ ክትትል ይደረጋል ብለዋል።



# ከኪጋሊ ጋር የተደረገው ስምምነት መዲናዋን ይበልጥ ለማስዋብ ተጨማሪ አቅም ይፈጥራል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባና የኪጋሊ ከተሞች የትብብር ስምምነት መዲናዋን ይበልጥ ለማስዋብ ተጨማሪ አቅም የሚፈጥር በመሆኑ ሁለቱ ከተሞች የጋራ እቅድ አውጥተው መሥራት እንደሚገባቸው የኢትዮጵያ ከተሞች ትብብር መድረክ ዋና ዳይሬክተር አቶ አንዱዓለም ጤናው ገለጹ፡፡

አቶ አንዱዓለም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አዲስ አበባ እና ኪጋሊ በውስን ጉዳዮች ላይ በጋራ ለመሥራት የእህትማማችነት ስምምነት ማድረጋቸው ለሁለቱ ከተሞች ዕድገት ጠቃሚ ነው፡፡

ኪጋሊ እንደ አዲስ አበባ ሰፊ ከተማ ባትሆንም በዋናነት የምትታወቀው በሦስት ነገሮች ነው ያሉት አቶ አንዷለም፤ ይህም በዘመናዊ አገልግሎት አሰጣጥ፤ በቆሻሻ አወጋገድ እና በአረንጓዴ ልማት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ አንዱዓለም ገለጻ፤ ኪጋሊ ከአዲስ አበባ በሰፋፊ መንገዶች ግንባታና ምንም እንኳን የነዋሪው ፍላጎት አሁንም ከፍተኛ ቢሆንም በቤት ልማት ተሞክሮዎችን መውሰድ ትችላለች፡፡ አዲስ አበባ ደግሞ ከኪጋሊ ከተማ የማስዋብ ፕሮጀክቶች ሰፊ ልምድ በመቅሰም አቅሟን ማሳደግ ትችላለች።

ስምምነቱ በጋራ ለመሥራት እንደመግቢያ በር ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ሁለቱ ከተሞች በተፈራረሙባቸው ዘርፎች የሚገኙ ተቋማት የጋራ ዝርዝር እቅድ አውጥተው ሊሠሩ እንደሚገባም አመልክተዋል።

ሁለቱ ከተሞች በተፈራረሙባቸው ዘርፎች የሚገኙ መሥሪያ ቤቶች በጋራ እቅድ አውጥተው ካልሠሩ ውጤቱን መለካትም ሆነ የሚፈለገውን ግብ ማምጣት አይቻልም ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ከተሞቹ ባለሙያዎችን ወደ ኪጋሊ እና አዲስ አበባ በመላላክ ሥልጠና መስጠትና እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን በመገምገም ድጋፍ እንዲደረግ በማድረግ ግንኙነቱ ውጤት እንዲያመጣ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

አቶ አንዱዓለም እንደተናገሩት፤ በተደጋጋሚ በተሠሩ ጥናቶች እንደተስተዋለው፤ በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ካሉ ከተሞች ጋር የሚደረጉ ስምምነቶች ውስን ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ አይደሉም።

አብዛኞዎቹ ከውጭ ከተሞች ጋር የተደረጉ ስምምነቶች ይዘታቸው ሲታይ ጥቅል ነው፡፡ ይህም ስምምነት ተደረገ ከማለት ውጪ ጥቅም ላይ ሲውል አይስተዋልም ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

የሁለቱ ከተሞች ስምምነት በውስን ጉዳዮች ላይ ያተኮረ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ አስታውቀው፤ በቆሻሻ አወጋገድ፤ በአረንጓዴ ልማት እና በመሰል ጉዳዮች ላይ በጋራ ለመሥራት የተደረገ ስምምነት በመሆኑ ይበልጥ ውጤታማ ለመሆን ያግዛል ሲሉ ተናግረዋል።

በውስን ዘርፎች ላይ ትኩረት ያደረገው ስምምነት ፈጻሚ በሆኑ የሴክተር መሥሪያ ቤቶች እና የከተማ አስተዳደሩ በቅርበት እየተከታተሉ ለማስፈጸም የሚችሉበት አካሄድ ለማበጀት ይረዳል ብለዋል።

በሌላ በኩል ስምምነቱ ከአፍሪካ ሀገር ጋር መሆኑ ሁልጊዜ የአውሮፓና አሜሪካ ሀገራትን ከማየት ከአፍሪካ ሀገራት ጋር እርስ በርስ ለመማማር የሚያስችል ዕድል ይፈጥራል ሲሉ ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸዋል፡፡

አዲስ አበባና የሩዋንዳ ርዕሰ መዲና ኪጋሊ የእህትማማች ከተማነት ስምምነት ሰሞኑን ፈርመዋል፤ ስምምነቱን የፈረሙት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ እና የኪጋሊ ከተማ ከንቲባ ሳሙኤል ዱሴንግዩምቫ መሆናቸው ይታወሳል።

# በአዲስ አበባ በትምህርት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ያሉት ኃላፊው፤ የተማሪና የክፍል ጥምርታን በማሻሻል፣ የትምህርት ቤትን ውበት ለተማሪዎችና ለመምህራን ሳቢ በማድረግ፣ ግብዓት በማሟላት ሥራ የተሠራበት ውጤታማ የትምህርት ንቅናቄ መደረጉን ተናግረዋል።

በቀጣይ የትምህርት ንቅናቄ ሥራዎችን የከተማ አስተዳደሩ በልዩ ትኩረት እየገመገመ የፌዴራል መንግሥትም ክትትል እያደረገበት ይቀጥላል ብለዋል።

የቢሮ ኃላፊው እንዳመላከቱት፤ በንቅናቄው ባለሀብቶች፣ የቀድሞ ተማሪዎችና ድጋፍ አድራጊዎች በየተቋማት አካባቢዎች ያሉ ፀጋዎችን በመለየትና በማስተሳሰር ትምህርት ቤቶች ያለባቸውን ችግር ለመቅረፍ ሰፊ ጥረት አድርገዋል።


ትምህርት ቢሮው ከትምህርት ንቅናቄው ጎን ለጎን ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በመቀናጀት አቅም በፈቀደና የመምህራንን ጥያቄ መመለስ የሚቻልባቸውን ሥራዎች እያከናወነ መሆኑን ጠቁመው፤ ለመምህራን መኖሪያ ቤቶችን ለማስተላለፍ የተጀመረው ጥረት ውጤት እያመጣ መሆኑን አመላክተዋል።

435 ቤቶችን ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ልምድ ላላቸው ዕድለኛ መምህራን የማስተላለፍ ሥራ እየተሠራ መሆኑን አንስተዋል። በተጨማሪ በማኅበር ለተደራጁ ከ35 ሺህ በላይ መምህራን ለቤት መሥሪያ የሚሆን ቦታ ከተማ አስተዳደሩ እንደሚያቀርብላቸው ኃላፊው አስረድተዋል።

ከተማ አስተዳደሩ ለመምህራኑ የሚሆኑ ሌሎች መሠረተ ልማቶችን እንደሚያሟላ ጠቁመው፤ መምህራኑ 30 በመቶ ቆጥበው 70 በመቶውን ደግሞ ከሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ጋር በማገናኘት የቤት ግንባታ ሥራ ውስጥ እንዲገቡ የሚያስችል ውጤታማ ሥራ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት መምህራኖች በመደራጀት ላይ መሆናቸውን አስታውቀው፤ በቀጣይ ተግባራዊ ለማድረግ መምህራኑ ከፋይናንስ ተቋማትና የግንባታ ሂደቱን ከሚያከናውኑ አካላት ጋር እንዲገናኙ ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል።

የመኖሪያ ቤት አቅርቦቱ ሥራ ለመምህራን ትልቅ ተስፋን የጫረ መሆኑን ኃላፊው አንስተው፤ በተያዘው ዓመትም ትልቅ አፈጻጸም ከታየባቸው ሥራዎች መካከል አንዱ መሆኑን አመላክተዋል።



ዘሳስም ሙሳት(ዶ/ር)

# ከወጪ ንግድ ሁለት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ለማግኘት ታቅዶ ሁለት ነጥብ 16 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል።

አፈጻጸሙ ከእቅዱ አንጻር 69 በመቶ መሆኑን ጠቁመው፤ ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት አፈፃፀም ጋር ሲነጻጸርም የ164 ነጥብ 18 ሚሊዮን ዶላር ቅናሽ አለው ብለዋል።

በስምንት ወሩ ከወጪ ንግድ የተገኘው ገቢ በዋናነት ከግብርና ምርቶች ከማኑፋክቸሪንግና ከማዕድን እንዲሁም ከሌሎች ምርቶች መሆኑን አቶ ተስፋዬ ገልጸዋል።

ገቢው በምርት አይነት ሲታይ ቡና 716 ነጥብ 423 ሚሊዮን ዶላር፣ አበባ 311 ነጥብ 496 ሚሊዮን ዶላር፣ የጥራጥሬ ምርቶች 229 ነጥብ 877 ሚሊዮን ዶላር እንዲሁም የቅባት እህሎች 225 ነጥብ 75 ሚሊዮን ዶላር በማስገኘት ከፍተኛውን ድርሻ የያዙ ምርቶች መሆናቸውንም አስታውቀዋል።

የጫት ኬላዎች መበራከትና ተደራራቢ ታክስና ቀረጥ መኖር፣ በድርቅ ምክንያት የቁም እንስሳት አቅርቦት እጥረትና በሚገኙባቸው አካባቢዎች የሚያጋጥሙ የፀጥታ ችግሮች፣ ኮንትሮባንድና ሕገወጥነት በስፋት ለወጪ ንግድ እቅዱ መዳከም ምክንያቶች መሆናቸውንም ጠቅሰዋል።

በተጨማሪም የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በልዩ ሁኔታ ክትትል የሚያደርግባቸው የወጪ ንግድ ምርቶች መኖራቸውን ጠቁመው፤ በበጀት ዓመቱ ስምንት ወራት ውስጥ ክትትል ከሚያደርግባቸው ምርቶች ወጪ ንግድ 617 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ መገኘቱን ገልጸዋል።

የወልና ኢንቨስትመንት እርሻ መመሪያ ተግባራዊ መደረጉ፣ የአኩሪ አተር፣ ቀይ ቦሎቄና ማሾ ምርቶች ዓለም አቀፍ ገበያ ፍላጎት መሻሻሉ እንዲሁም የሰሊጥ ምርት መጨመሩ በበጎነት ከታዩ ውጤታማ ሥራዎች መካከል መሆናቸውን አመላክተዋል።

አዳዲስ ምርቶችን ወደ ወጪ ንግድ ሥርዓቱ ለማስገባት፣ የወጪ ንግዱ ከሕገ ወጥነት ተላቆ በሕጋዊ የአሠራር ሥርዓትና የሕግ ማዕቀፍ ብቻ እንዲመራ የማድረግ የወጪ ንግድ ምርቶችን ብዝኃነት፣ ጥራትናና መጠን የማሳደግ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑንም ጠቁመዋል።

# ከሥራ ጠባቂነት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ጊዜ ውስጥ ለውጦችን እያስተዋሉ መሆናቸውንና በቀጣይ ሥራቸውን አሳድገው ከራሳቸው አልፈው አገርን ለመጥቀም እንደሚተጉ ነው ያመላከቱት።

ሮበሌ፣ መለሰ እና ጓደኞቻቸው የወተት ከብትና እርባታ ኅብረት ሽርክና ማኅበር አባል የሆኑት አቶ መለሰ ጋረደው እንደሚናገሩት፤ ማኅበሩ በአምስት አባላት ሲመሠረት 16 የወተት ከብትና እርባታ እንስሳቶችን ይዘው ነው። ሥራውን የጀመሩት መንግሥት ባመቻቸው ሼድ ሲሆን፣ ቀደም ሲል ግን ተባራሪ ሥራ በመሥራት ጉልበትና ገንዘባቸውን ከመጨረስ ውጭ ያተረፉት ነገር አልነበረም። በአሁኑ ወቅት አቅም በማጎልበት ላይ በመሆናቸው ለሦስት ሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠር እንደቻሉ ይናገራሉ።

የቀድሞዎቹ ሥራ አጦች፤ ከሥራ ጠባቂነት ወደሥራ ፈጣሪነት እየተሸጋገሩ በመሆናቸው ለሌሎች ሥራ ማግኘት ምክንያት መሆን መቻላቸውን ያስረዳሉ።

በገላን ጉዳ ክፍለ ከተማ ዳለቲ ወረዳ ማሕሙድ፣ ሀዋ እና ጓደኞቻቸው ኅብረት ሽርክና ማኅበር አባል የሆኑ አቶ ሐጂ ከድር በበኩላቸው፤ ማኅበራቸው፤ መንግሥት በሰጠው ሼድ ሁለት ሺ 500 የእንቁላል ዶሮዎችን በማርባት ላይ እንደሚገኝ ይገልጻሉ።


ቀደም ሲል ሥራ ያልነበራቸው መሆኑንም ጠቅሰው፤ አሁን በገላን ጉዳ ክፍለ ከተማ በተደረገላቸው ድጋፍና ያልተቋረጠ ክትትል ውጤታማ ሥራ በማከናወን ከራሳቸው አልፈውም ለሁለት ሰው የሥራ ዕድል መፍጠራቸውን ይናገራሉ።

ማኅበራቱ በተደረገላቸው ድጋፍ ወደሥራ መግባታቸውን ጠቅሰው፤ የውሃ እና የመብራት ችግርም እንደሌለባቸው ነው ያመላከቱት። ይሁንና ሼዱ አጥር የሌለው መሆኑ እንዲሁም፣ የከብት እና የዶሮ መኖ እጥረት በመኖሩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ መሆኑን አንስተዋል።

የሸገር ክፍለ ከተማ የገላን ጉዳ ማዘጋጃ ቤት ሥራ አስኪያጅ አቶ ዱጉማ ሙለታ በበኩላቸው እንደሚያስረዱት፤ ከሦስት ወር በፊት ሼዶችን ለመሥራት ብዙ ጥረት ተደርጓል። ጥረቱ ተሳክቶም 106 ሼዶች የተሠሩ ሲሆን፣ በእነዚህም ሼዶች ውስጥ ዘጠኝ ክላስተር ይገኛል። ከእነዚህም ውስጥ የወተት ላም እርባታ፣ የሥጋ እና የእንቁላል ዶሮ እርባታ፣ የከብት ማደለቢያና ሌሎችም ይካተቱበታል። አንድ ሼድ እስከ 40 ላሞች ወይም በሬዎችን የሚይዝ ነው።

እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ ሼዶቹ የተሠሩት ለወጣቶችና ለሥራ አጦች ሲሆን፣ በልማድ ከብቶችን ያረቡ ለነበሩ አርሶ አደሮችም ጭምር ነው። በአሁኑ ወቅት በሼዶቹ ውስጥ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆኑት ሥራ መጀመር ችለዋል። ሼዶቹ መብራትም ውሃም እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን፣ የሚቀረው የአጥር ሥራም በመሠራት ላይ ይገኛል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል የሥራ ዕድል ፈጠራ ቢሮ በጋራ በሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ያተኮረ የመስክ ምልከታን ለጋዜጠኞች ባስጎበኙበት ወቅት የሥራ ዕድሉ የተፈጠረላቸው ማኅበራት፣ መንግሥት ባመቻቸላቸው ሼዶች በመጠቀም ውጤታማ ሥራ መጀመራቸውን አሳውቀዋል።



# አምስት ሚሊዮን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ተሠርቷል ሲሉ ተናግረዋል።

በክልሉ የሚገኙ ሁሉም ወረዳዎች የተፈጥሮ ማዳበሪያ የሚያዘጋጁበት ማዕከል መቋቋሙን አንስተው፤ እስካሁን ድረስም 100 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ኮምፖስት በክልሉ መዘጋጀቱን አስታውቀዋል።

የተፈጥሮ ማዳበሪያ አጠቃቀም እንደአፈሩ ይዘት ቢለያይም ከውጭ ከሚመጣው የተሻለ ጥቅም ይሰጣል ያሉት አቶ በሪሶ፤ በቀጣይነት የኬሚካል ይዘት ያላቸውን የአፈር ማዳበሪያዎች መጠን በመቀነስ የተፈጥሮ ማዳበሪያን በስፋት ለመጠቀም ትኩረት ተሰጥቷል ብለዋል።

የተፈጥሮ ማዳበሪያን ከመጠቀም አንጻር ለአርሶ አደሮች መድረኮችን በማዘጋጀት ሆነ በተገኙ አጋጣሚዎች የግንዛቤ ሥልጠና እየተሰጠ ነው ብለዋል። በተጨማሪም የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉም በየወረዳው ከሚገኙ የግብርና ባለሙያዎች ጋር እየተሠራ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

እንደአጠቃላይ የአፈር ማዳበሪያ ስርጭቱ በስፋት የሚከናወንበት ወቅት ላይ እንገኛለን ያሉት አቶ በሪሶ፤ የማዳበሪያ ስርጭቱን እስከሚያዚያ ወር መጨረሻ ድረስ ለማጠናቀቅ እቅድ መቀመጡን ጠቁመዋል። ለዚህም ከማኅበራትና በየደረጃው ከሚገኙ የግብርና አመራሮች ጋር እየተሠራ መሆኑን አብራርተዋል።

በክልሉ በኤክስቴንሽን ተጠቃሚ የሆኑ አርሶአደሮች ቁጥር ከዚህ በፊት በተሠራ መረጃ አራት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ነበሩ ያሉት ምክትል ኃላፊው፤ አሁን ላይ ቁጥራቸው ወደ አምስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ከፍ ማለቱን ጠቁመዋል። የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ የሆኑ አርሶአደሮች በሙሉ የአፈር ማዳበሪያ ተጠቃሚ መሆናቸውን አመላክተዋል።

አቶ በሪሶ እንደተናገሩት፤ ሕገወጥ የማዳበሪያ ንግድና እንቅስቃሴን ለመከላከል የአርሶ አደሩን ማንነት የሚገልጽ መታወቂያ እንዲያመጣና የከፈለበትን የባንክ ደረሰኝ እንዲያስገባ ይደረጋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጥያቄዎችን በኃይል አማራጭ ለመፍታት የሚደረግ እንቅስቃሴ ሕገወጥና ተቀባይነት የሌለው ነው!

በሀገሪቱ የአስተዳደር ወሰን እና ማንነትን መሠረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ትናንት ተነስተዋል፤ ዛሬም እየተነሱ ነው። ለጥያቄዎቹ አግባብ ባለው መንገድ፣ አግባብ ያለው መልስ መስጠት ካልተቻለ ጥያቄዎቹ ነገም ጥያቄ ሆነው መቀጠላቸው የማይቀር ነው። የግጭት እና አለመግባባት ምንጭ የመሆናቸውም አጋጣሚም የሰፋ ነው ።

ማናቸውንም ጥያቄዎችን በኃይል ለመፍታት የሚደረግ የትኛውም ዓይነት እንቅስቃሴ፣ የጥያቄዎቹን የግጭት ምንጭነት ከፍ ከማድረግ፣ በሕዝቦች መካከል ያልተገባ ቁርሾን እና የጠላትነት መንፈስን ከመፍጠር ባለፈ ዘለቂ መፍትሔ ሆኖ ሊያገለግል አይችልም ።በዚህ መንገድ የተፈታ ችግርም የለም ።

ከለውጡ በፊትም ሆነ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በሀገሪቱ የአስተዳደር ወሰን እና ማንነትን መሠረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎችን በሠላማዊ መንገድ በሕዝበ ውሳኔ የሚፈቱበትን መንገድ ለመፍጠር የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል። ጥያቄዎቹ ወደ ግጭት እንዳይወስዱም በብዙ ጥንቃቄ ተስተናግደዋል ።

በተለይም በአማራ እና በትግራይ ክልል መካከል ያለው የአስተዳደር ወሰን እና የማንነት ጥያቄዎች፣ የሀገራዊ ግጭት ምንጭ እንዳይሆኑ በለውጥ ኃይሉ በኩል በገለልተኝነት፣ በሰከነ መንፈስ ለማየትና ዘላቂ መፍትሔ ለማስቀመጥ የተሞከረበት መንገድ፣ በብዙ መልኩ ተስፋ ሰጭ እንደነበርም የሚታወስ ነው ።

ይህ ችግር በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በሕወሓትና በፌዴራል መንግሥት መካከል ከነበረው ጦርነት ጋር በተያያዘ ቀጣይና ተጨማሪ የግጭት ምንጭ እንዳይሆን፣ በደቡብ አፍሪካ፣ ፕሪቶሪያ በተደረገው የሠላም በስምምነት በቂ ትኩረት ከተሰጣቸው የስምምነቱ አካሎች አንዱ እንደነበርም ይታወቃል ።

መንግሥት በክልሎቹ መካከል ያሉ የአስተዳደር ወሰን እና የማንነት ጥያቄዎች የሕዝብን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ባካተተ መልኩ በሠላማዊ መንገድ የሚፈቱበትን የመፍትሔ ሀሳብ በግልጽ አስቀምጧል። ይህም ችግሩን በመፍታት ሂደት ውስጥም ክልሎቹ የሕዝብን ፍላጎት እና ምርጫ አክብረው የሚንቀሳቀሱበትን የኃላፊነት አሠራር ያስቀመጠ ነው።

የፌዴራል መንግሥትም ችግሩን በዘላቂነት በሕዝበ ውሳኔ ለመፍታት ጥያቄ በሚነሳባቸው አከባቢዎች የሚገኙ የታጠቁ ኃይሎች እንዲወጡ፣ በግጭት ምክንያት ከየአካባቢው የተፈናቀሉ ዜጎች ወደ አካባቢያቸው ያለ ቅድመ ሁኔታ እንዲመለሱ ፣ እስከዚያም አካባቢዎቹ ከጉዳዩ ገለልተኛ በሆነው የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት እንዲጠበቅ አቅጣጫ አስቀምጧል ።

መንግሥት ችግሩን ለመፍታት የሄደበት መንገድ፣ ጥያቄዎቹ ወደ ግጭት እንዳያመሩ ከመከላከል ባለፈ፣ ጥያቄዎቹ የሕዝብ ከመሆናቸው አኳያ ዘላቂ ሕዝባዊ መፍትሔ እንዲያገኙ የሚያስችል፤ በቀጣይም ተመሳሳይ ችግሮችን ለመፍታት እንደ አንድ ትልቅ ተሞክሮ ሊወሰድ የሚችል ነው ።

ይህ በአካባቢውም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ሠላም አጽንቶ ከማስቀጠል አንጻር ከፍተኛ ፋይዳ ያለውን የመንግሥት ውሳኔ በአግባቡ ተረድቶ ማስፈጸም፣ ከሁሉም በላይ የክልሎቹ አመራሮች ኃላፊነት ነው። ይህንን ባለማድረግ ለሚፈጠር ችግርም ቀዳሚ ተጠያቂ የሚሆኑት እነዚሁ አካላት ናቸው ።

ብዙ ወገኖቻችንን የቀጠፈ የሰሜኑ ጦርነት የፈጠረው ጠባሳ ገና ባላገገመበት፣ የብዙ እናቶች የልብ ስብራት ሰቆቃ ባልተፈወሰበት፣ ሀገር እንደሀገር ጦርነቱ በፈጠረው የኀዘን ቁዘማ ባልወጣችበት አሁናዊ እውነታ፣ ጥያቄዎችን በኃይል ለመፍታት መሞከር የተጨማሪ ሀገራዊ ስብራት ምንጭ ከመሆን ባለፈ ትርጉም ያለው መፍትሔ ሊሆን አይችልም ።

ያለንበት አሁናዊ ሀገራዊ እውነታ በጉልበት እንፈታተን የሚባልበት አይደለም፣ ይህ ዓይነቱ የጥፋት መንገድ እስከዛሬ ያስከፈለን ያልተገባ ዋጋ በቂ እና ከበቂ በላይ ነው። ስለሆነም በማናቸውም ሁኔታ ጥያቄዎችን በኃይል አማራጭ ለመፍታት የሚጥሩ ኃይሎችን መላ ሕዝባችን በቃችሁ ሊላቸው ይገባል!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የግብርናውን ዘርፍ መልካም ዕድሎች አሟጠን እንጠቀም!

**እስመ ለአለም**

የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት በማሳደግ በኩል እንደ ሀገር በርካታ ተግባሮች ተከናውነዋል፤ ይህን ተከትሎም በርካታ ለውጦች ታይተዋል፡፡ የልማቱን አማራጮች በማስፋት፣ የአርሶ አደሩንና የግብርናውን ቤተሰብ አመለካከት በመቀየር፣ በግብዓት፣ በፋይናንስ አቅርቦትና በመሳሰሉት ላይ በእርግጥም ለውጦች ታይተዋል፡፡

ከመኸርና ከበልግ እርሻ ተገቢውን ምርት ለማግኘት እየተከናወኑ ባሉ ተግባሮች ምርትና ምርታማነቱን ማሳደግ ተችሏል፡፡ ግብርናውን በሜካናይዜሽን፣ በምርጥ ዘርና በማዳበሪያ በመደገፍ፣ ለአርሶ አደሩ ሥልጠናዎችን በመስጠት፣ የኩታ ገጠም እርሻን በማስፋፋት የምርምር ሥራዎችን መሬት ላይ በማውረድ በእርግጥም ምርትና ምርታማነትን በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ ተችሏል፡፡

አንድም ማሳ ጦም እንዳያድር በሚል በተወሰደ እርምጃ ለኢንቨስትመንት የተያዙ መሬቶች ሳይቀሩ በሰብል እንዲሸፈኑ በማድረግ ተሠርቷል፤ በተቋማት ግቢ የሚገኙ ለልማት ያልዋሉ መሬቶችም በተመሳሳይ ለእርሻ ሥራ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

ሰብሎችን እንደ አንበጣና ተምች ካሉት ተባዮች በመጠበቅ፣ ብክነቶችን በመከላከል ላይ በትኩረት በመሥራትም ምርትና ምርታማነቱ ይበልጥ እንዲያድግ በመሠራቱ ለውጦችን ማምጣት ተችሏል፡፡

እነዚህ ሁሉ ሆነውም ከግብርናው ዘርፍ እየተገኘ ያለው ምርት ከሀገሪቱ ፍላጎትና አቅም አኳያ ሲታይ አሁንም እዚህ ግባ የሚባል ሊሆን አልቻለም። ዘርፉ ካለው እምቅ አቅም አኳያ፣ ሀገር ዘርፉን ይዛ ብዙ ርቀት ለመጓዝ ካላት ጽኑ ፍላጎት አኳያ ሲታይ በእርግጥም ዘርፉ ገና ብዙ እንዳልተሠራበት ይገለጻል። ግብርናው ብዙ ከወጣበት የምግብ ዋስትናን በሚገባ ከማረጋገጥ ባለፈም በውጭ ምንዛሪ ግኝትና በመሳሰሉት ብዙ ሀብት ሊገኝበት እንደሚችል የሚታመንበት እንደመሆኑ ይህን ለማረጋገጥ ገና ብዙ መሠራት ይኖርበታል፡፡

መንግሥትም ባለፉት ዓመታት ይህን ሁኔታ ለመቀየር ግብርናውን ከዝናብ ጥገኝነት ሊያወጣ የሚችል፣ ሀገሪቱ ያላትን የውሃና የመሬት ሀብት በሚገባ በመጠቀም በተለይ የሰብል ምርትና ምርታማነቷን ማሳደግ በሚያስችል ሥራ ላይ ተጠምዷል፡፡

ይህም በተለይ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በሚገባ እየታየ ነው፡፡ በዚህ ልማት እየተከናወነ ያለው ተግባር በሀገሪቱ የውሃ ሀብትና ለም መሬት ላይ በሚገባ ከተሠራ የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት አሁን ካለበት ጥሩ ሁኔታም በእጅጉ እንዲመነደግ ማድረግ ይቻላል። ይህንንም በዚህ ልማት ባለፉት ዓመታት ከተከናወኑ ተግባሮች መረዳት ይቻላል፡፡

የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት በ2011 ሲጀመር የተገኘው 100 ሺ ኩንታል ስንዴ ነበር፤ ይህን ምርታማነት በ2016 ዓ.ም 120 ሚሊዮን ኩንታል ለማድረስ ታቅዶ እየተሠራ ነው፡፡ ከደረሰው የበጋ መስኖ ስንዴ አዝመራ እስከ አሁንም ከ58 ሚሊዮን ኩንታሉ ስንዴ ተሰብስቦ ወደ ጎተራ ገብቷል፡፡ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ የታየው ለውጥ ምን ያህል እንደሆነ ከዚህ መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡

በዚህች ሀገር ከአንድ ማሳ ሁለት ሦስቴ ማምረት እየተቻለ ነው፡፡ የመኸርና የበልግ ወቅትን ብቻ ተጠቅሞ የእርሻ ሥራን ከመሥራት በመውጣት፣ በዓመት እስከ ሁለት ሦስቴ ማምረት መቻል ምን ያህል ምርታማነትን ሊጨምር እንደሚችል፣ ምን ያህል የአርሶ አደሩን ሕይወትም መቀየር እንደሚችል መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በከተማ ግብርና እና በሌማት ትሩፋት እየተከናወኑ ያሉ ተግባሮች ከተሜው ሸማች ብቻ ከመሆን እንዲወጣ እያደረጉ ናቸው፡፡ ግብርናን የከተማም ሥራ ጭምር ማድረግ እየተቻለ ሲሆን፣ በከተሞችና አቅራቢያቸው የሚገኙ ክፍት ቦታዎችን ለግብርና ሥራ በማዋል ዜጎች ከአትክልትና ፍራፍሬ፣ የወተትና ወተት ተዋፅዖ፣ ወዘተ ምርቶችን በስፋት የሚያገኙበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ከየከተሞቹ የሚወጡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱትም ሥራው ውጤታማ እየሆነ መጥቷል፡፡

የሀገራችን አርሶ አደር በበጋ ወቅት አዝመራው ከሰበሰበ በኋላ በሥራ ፈትነት ነበር የሚታወቀው። ይህ ሁኔታ በጥር ወር አካባቢ መካሄድ በጀመረው የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ መሰበር የጀመረ ሲሆን፣ በመስኖ ልማት በተለይም በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ደግሞ በከፍተኛ ሁኔታ እምርታ ማሳየት ችሏል። አርሶ አደሩን ለዚህ አይነት ሕይወት፣ ግብርናውን ለእዚህ አይነቱ የላቀ ደረጃ የበቃ ይህ የእርሻ ልማት እንዲበራከት ማድረግ ላይ በቀጣይም በትኩረት መሥራት ይኖርበታል፡፡

በቀጣይም የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ሊያሳድጉ የሚችሉ የትኛዎቹም ዕድሎችና ምቹ ሁኔታዎች በሚገባ ሊሠራባቸው ይገባል፡፡ ልንጠቀምባቸው የሚችሉ በርካታ ዕድሎች አሁንም አሉን፡፡

አንዳንዴ ወቅቶች መልካም ዕድሎችን ይዘው ይመጣሉ፡፡ ወቅቶች ሲሰጡ መስጠታቸውን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ለአብነትም የዘንድሮውን የበጋ ወቅት መጥቀስ ይቻላል፡፡ እንደ ዘንድሮው የበጋ ወቅት ያለ ዝናብ ሲገኝ መሥራት ባለብን ላይ መሠራት ይኖርብናል፡፡

የዘንድሮው በጋ ገርና እርጥብ ነው፤ ዝናብ ሰጥቶናል፡፡ በአዲስ አበባም ከአዲስ አበባ በተለያዩ አቅጣጫዎች ሲወጣም ሜዳው ጋራው ሸንተረሩ አረንጓዴ ሆኖ ነው የሚታየው፡፡ ይህ ወቅት ይዞት የመጣው ዕድል ብዙ ነው፡፡

ዝናቡ እንስሳት በቂ ግጦሽና ውሃ እንዲያገኙ፣ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብሮች የተተከሉ የፍራፍሬና የተለያዩ የዛፍ ተክሎች እድገት እንዲፋጠን፣ ምርታማነት እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ የጓሮ አትክልቶች በበጋ ወቅት ጉዳት እንዳይደርስባቸው ብቻ አይደለም የሚያደርገው፤ ምርታማ እንዲሆኑም ያስችላል፡፡

የመሬት እርጥበት እንዲጨምርና የመኸርና የበልግ እርሻው በሬዎችን ሳይጎዳ በቀላሉ እንዲፈጸም ያስችላል፡፡ በተሰነጠቀው ማሳ የዝናቡ ውሃ እንዲተኛና ወደ መሬት እንዲሰርግ በማድረግ ለመሬት እርጥበት መጨመር ትልቅ አስተዋፅዖ ያበረክታል፡፡

ለመስኖ አገልግሎት የሚውሉ ወንዞች ውሃን ከመሚጠጥ ከመታደግም በላይ አቅማቸው እንዲጨምር ያደርጋል፤ ሰፋ አርጎ ለሚያስብም ዝናቡ የከርሰ ምድር ውሃ አቅም እንዲጎለብት ያስችላል፡፡

ይህ አይነቱ ዝናብ የሚገኝበት የበጋ ወቅት ምንም አንኳ እንደ መኸር፣ በልግና የመስኖ ወቅቶች የራሱ መርሐ ግብር ወጥሎት እንደ ዘር ወቅቱ በሬ ተጠምዶ ሆ ተብሎ የእርሻ ሥራ ባይከናወንበትም፣ ለግብርናው ሥራ በአጠቃላይ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ስለመሆኑ ንግግር አያሻውም፡፡

የበጋ ወቅት ዝናብ ስላለው ፋይዳ ከዓመት በፊት ድርቅ በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን ጉዳት ባስከተለበት ማግስት በጋ ላይ በጣለው ዝናብ የዝናብ ውሃ እንዲይዙ የተሠሩ ግድቦች ውሃ የያዙበት ሁኔታና ውሃው ለከብቶችና ለሰዎች የሰጠው ጥቅም ሲታሰብ የበጋ ወቅቱን ዝናብ መያዝ አስፈላጊነትን ፋይዳ ያመለክታል፡፡ አንዲትም ጠብታ ውሃ ብትሆን እንዳትባክን ለመሥራት ከወዲሁ መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

በመንግሥት የተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎችን በመጠቀም ብዙ ርቀት መጓዝ እንደታቸለ ሁሉ መልካም አጋጣሚዎች ይዘዋቸው የመጡ አቅሞችንም በሚገባ አሟጦ መጠቀም ይገባል፡፡

የብሔራዊ ሜትዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ባለፉት ወራት በተለያዩ አካባቢዎች ዝናብ ጥሏል፡፡ መሬት ላይ የሆነውም ይሄው ነው፡፡ አሁንም ዝናብ ማግኘት የሚቻልባቸው ሁኔታዎች ሰፊ ናቸው፡፡ ይህን ተፈጥሮ የቸረንን የዝናብ ፀጋ ለመጠቀም አርሶ አደሮች እንደሚታትሩ ይጠበቃል፡፡ ይህ ጥረታቸው ግን በባለሙያ በሚገባ ሊታገዝና ውጤታማ በሆነ መልኩ ሊቃኝ ይገባል፡፡

# ነፃ ሃሳብ

# ስታርትአፕ የወጣቱ የአዲስ ሕይወት አቅጣጫ

**ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽክታብ)**

መንግሥት በኢኮኖሚ ግንባታ ሂደት ላይ በተለይም የወጣቱን ሕይወት የሚቀይሩ፣ የተሻሉ አቅጣጫዎችን በመትለም በርካታ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል፡፡ ከነዚህ መንግሥታዊ የኢኮኖሚ አቅጣጫዎች መሀል ስታርትአፕ በዋነኝነት ይጠቀሳል፡፡ የቃሉ ትርጓሜ ጀማሪ ሥራ ፈጣሪነት ሲሆን ማዕከል አድርጎ የሚነሳውም ወጣቱን ነው፡፡

ወጣትነትና ልማት የአንድ ሳንቲም ሁለት መልኮች ናቸው፡፡ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የወጣት ቁጥር ባለባቸው ሀገራት ትርጉሙ ሚዛን ደፍቶ ይገኛል፡፡ መንግሥትም ይሄን አዲስ አስተሳሰብ ወደመሬት ሲያወርድ ወጣቱን ማዕከል ባደረገ እና ሀገራዊ የልማት ለውጦችን መሠረት ባደረገ መልኩ ነው፡፡

ስታርትአፕ መነሻው ሃሳብ ነው መድረሻው ደግሞ ሀገርና ማህበረሰብ ነው፡፡ እኚህ የለውጥ ጥልፍልፎች ከወጣቱ የሥራ ፈጣሪነት ተነስተው በትላልቅ ኢንዱስትሪዎችና ግብር ከፋይነት አልፈው ከፍ ያለ ዓለም አቀፍ ትስስርን በመፍጠር የውጭ ምንዛሬ በማምጣት ለሀገር ግንባታ ምሰሶ መሆን የሚችሉ ናቸው፡፡

አፍሪካን ጨምሮ ብዙ የዓለም ሀገራት አሁን ላይ በዚህ ወጣት ተኮር በሆነ የሥራ ፈጣሪነት እንቅስቃሴ ላይ ናቸው፡፡ መንግሥትም የነበሩ ለሥራ ፈጣሪዎች የማይመቹ ሕጎችን በማስተካከል ሃሳብ ላላቸው ሥራ ፈጣሪዎች ምቹ ምህዳርን በመፍጠር የስታርትአፖችን የለውጥ ምዕራፍ በማቀላጠፍ ላይ ይገኛል፡፡

በሃሳብ ፈጣሪነት ዳብረው ከቅርብ በመነሳት ሩቅ መድረስን አላማቸው ያደረጉ ወጣቶች ራሳቸውን ቀይረው ሀገራቸውን የሚጠቅሙበት አቅጣጫ በመሆኑ አሁን ላይ እንደ አንድ ሀገራዊ አጀንዳ ሆኖ እየተሠራበት ነው፡፡

ኢኮኖሚ ለአንድ ሀገር የጀርባ አጥንት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይሄ እውነታ አካል ለብሶ እውን የሚሆነው ደግሞ ከጥቃቅን እስከ ከፍተኛ ባሉ ለሥራ እድል መፍጠሪያ በተዘረጉ ክፍት፣ ነፃና አዋጪ መድረኮች ነው፡፡ ወጣቱን ተሳታፊ ባደረገ፣ ለላቀ ሃሳብ ቅድሚያ በሰጠ የሥራ ክህሎት ዳብሮና በልጽጎ ኢኮኖሚውን ሞተር ሆኖ የሚያሳድግ ነው።

እንደ ደቡብ አፍሪካ፣ ናይጀሪያ፣ ሴኔጋልን የመሳሰሉ የአፍሪካ ሀገራት ወጣቱን ባነቃ የስታርትአፕ የሥራ ፈጠራ በኩል ሀገራቸውን ከውጪው ማህበረሰብ ጋር በማስተሳሰር ተጨማሪ ገቢን እያገኙ መጥተዋል፡፡ በእኛም ሀገር እንደራይድ ያሉ የትራንስፖርት አማራጮች በወጣቱ የሥራ ፈጣሪነት የመጡ ናቸው። ከተቀጣሪነት ወደቀጣሪነት በመሸጋገር ከፍተኛ ግብር ከፋይም ናቸው፡፡

ስታርትአፕ እንደሀገር ፋይዳው ከዚህም የላቀ ነው፡፡ ከግለሰብ የሃሳብ ልህቀት ተነስቶ ዓለም አቀፋዊነትን የሚይዝ ነው፡፡ ለዚህ እንደምሳሌ የሚነሱት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑ እንደአፕልና ማይክሮ ሶፍትን የመሳሰሉ ካምፓኒዎች ናቸው፡፡ እኚህ ካምፓኒዎች ባለቤት አላቸው፡፡ መነሻቸው ግለሰብ ሲሆን መድረሻቸው ግን ዓለም አቀፋዊነት ሆኗል፡፡

ሲነሱ በሃሳብ ሲያበቁ ደግሞ በለውጥና በላቀ ትርፍ ነው፡፡ ብልጌትም ሆነ ቤዞስ ወደዚህ ሥራ ፈጣሪነት ሲገቡ ተራማጅ በሆነ እና በማይገታ ህልም ነው፡፡ ህልማቸው ፍሬ አፍርቶ ለብዙዎቻችን እንጀራ ሆኖ በየቤታችን ገብቷል፡፡ የስታርትአፕ ጽንሰ ሃሳብም እንዲሁ ነው፡፡ ከሃሳብ መንጭቶ የሚፈስ የትጋት፣ የንቃትና የጽናት ንቅናቄ ነው፡፡

ንቅናቄው እንዳይቆምና እንዳለፈው ጊዜ ሥራ ፈጣሪዎች ተስፋ ቆርጠው ትግላቸውን እንዳይተው አሁን ላይ መንግሥት ፖሊሲዎችን በማሻሻል፣ የብድር አቅርቦቶችን በማመቻቸት፣ የቦታና የንግድ ፍቃድ አሠራርን በማዘመን፣ የባለሙያ ክትትሎችን በማድረግ ወጣቱን ከህልሙ ጋር ሊያገናኝ ታጥቆ የተነሳበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

ባለፈው ጊዜ የነበረው ሁኔታ ለጀማሪ ቀርቶ ለነባር ሥራ ፈጣሪዎች አስቸጋሪ ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ወጣቱ ወደሥራ እንዳይገባ፣ ነባር ሥራ ፈጣሪዎች ተስፋ ቆርጠው በነበሩበት እንዲቆሙ ያስገደደ ነበር፡፡ አሁን እነዚህ ተግዳሮቶች ተቀርፈው ሁሉም ነገር በተስተካከለ ምቹ ሁኔታ ላይ ባለተሰጥኦዎች መክሊታቸውን እንዲጠቀሙ መንገዶች ተከፍተዋል፡፡

በዚህም መሠረት በርካታ ወጣቶች በአነስተኛና በጥቃቅን ከፍ ባለ ደረጃም ተደራጅተውና ተቧድነው የእድሉ ተጠቃሚ በመሆን ጅማሮ ላይ ናቸው፡፡ የተጀመረው የአቅጣጫ ለውጥ ለነባርና ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች ተስፋን የሚሰጥ፣ በሀገር ኢኮኖሚ ላይም ለውጥ የሚያመጣ እንደሆነ በብዙዎች ተተንብየዋል፡፡

የመንግሥትን ጅማሮ ለጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች ጉልበት የሚሆኑ ቀሪ የቤት ሥራዎች ሲጠናቀቁ በኢኮኖሚ ግንባታው ላይ የተሻለ እምርታ ይኖረዋል፤ ወደ ሀገር ቤት እንዲገቡ የተፈቀደላቸው እንደ የውጭ ሀገር ባንኮች ዓይነት ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ያላቸው ተቋማት ስታርትአፕን በማበረታታት ረገድ የጎላ ሚና ሊያበረክቱ የሚችሉበትም እድል ሰፊ ነው፡፡

የሀገር ቤት ባንኮች ብድር የመስጠት ሂደት በቅድመ ሁኔታዎች የተሞሉ መሆናቸው፤ የውጭ ሀገር ባንኮች ግን ከዚህ በተሻለ መንገድ የተበዳሪውን ግለሰብ ሃሳብ፣ የሥራ ፈጣሪነት ክህሎት ታሳቢ ማድረጉ ለእስታርትአፖች እጅግ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ሀገር ከግለሰብ ወደ ማህበረሰብ የሚሄድ የሃሳብ፣ የክዋኔ ውህድ ናት፡፡ የእያንዳንዱ ሥራ ፈጣሪ ወጣት ሃሳብ ማረፊያው ማህበረሰብ ነው። ብልጌትና ቤዞስ ከሆነች አንድ መንደር ተነስተው በሃሳባቸው በኩል ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ግልጋሎት እየሰጡ ነው። የእኛም ሀገር የሥራ ፈጣሪነት ጽንሰ ሃሳብ ከዚህ ተለይቶ ሊታይ አይገባም፡፡

ባለፈው ጊዜ በቢሮክራሲ ሆነ በማይመች አካሄድ መንገድ የዘጋንባቸው ሥራ ፈጣሪዎች ለሀገር የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ እንደከለከልናቸው ሊታሰብ ይገባል፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ ደግሞ ወጣቱ በሃሳቡ፣ በተሰጥኦው፣ በመክሊቱ፣ በእውቀቱ በተመቻቸ መንገድ ላይ ራሱን ጠቅሞ፣ ቤተሰቡን አገልግሎ ለሀገር የሚሰጥበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው፡፡ ስታርትአፕስ ከሥራ ፈጣሪነት እኩል ሊነሳ የሚገባው ሌላኛ መገለጫው ‹ከሥራ አጥነት ወደሥራ ፈጣሪነት፣ ከጠባቂነት ወደሰጪነት፣ ከልመና ወደልግስና፣ ከተቀጣሪነት ወደቀጣሪነት› መሸጋገር የሚለው ነው፡፡

ሥራ ፈጣሪ ወጣቶች በተሻሻለ ፖሊሲና ተስፋን በሚሰጥ መበረታታት አቅማቸውን እንዲጠቀሙ ካላደረግን፣ በአንቂና በአብቂ ሕገ ደንቦች፣ ከጠባቂነት በሚያወጣ የኢኮኖሚ ጽንሰ ሃሳብ ስር ካልተሰለፍን፣ ከአንድ ዓይነት ልምምድ ርቀን ሥራ ፈላጊነትን ወደሥራ ፈጣሪነት የሚቀይር ማህበራዊ ንቃትን ካልፈጠርን በጀመርነው አሮጌ መንገድ ልውጥ ማምጣት አይቻልም፡፡ ስታርትአፖች የሀገር የኢኮኖሚ ተስፋዎች እንደሆኑ በመንግሥት ታምኖበታል ይሄ እውነታ በክዋኔ ታግዞ ለውጥ ለበስ እንዲሆን የሁላችንም አስተዋጽኦ ያስፈልጋል።

አንድ ሥራ ፈጣሪ ዜጋ ሥራ ፈጥሮ ሲሰራ በስሩ ምን ያክል ሠራተኞችን እንደሚያስተዳድር አስበንዋል? አንድ ግለሰብ በተመቻቸ ፖሊሲና በተቃና መንገድ ላይ ራሱን ሲያቆም በስሩ ምን ያክል ነፍሶችን እንደሚያስጠልል ገብቶናል? ይሄ ተራ የሚመስል ግን ደግሞ እንደ አንድ ሰፊና ግዙፍ ሀገር፣ ብዙሃኑ ወጣት እንደሆነባት ሀገርና ከድህነት ለመውጣት እንደሚታትር ማህበረሰብ ተቀዳሚ ጥያቄ ነው፡፡ የአንድ ሥራ ፈጣሪ መነሳት የብዙ ሥራ አጥ ወጣቶች ተስፋ መጀመሪያ ነው፡፡ አንዱ አንዱን ይዞ እየተነሳ ሲሄድ ይሄ ነው ሀገራዊ ለውጥ ማለት፡፡ ይሄ ነው የኢኮኖሚ ግንባታ የሚባለው፡፡

በተመረቅን ማግስት ብዙዎቻችን የትምህርት ማስረጃችንን ይዘን እንዲቀጥረን የምንሄድበት ድርጅት የሃሳብ ውጤት ነው፡፡ ለብዙዎቻችን እንጀራ የሆኑ ተቋማት በሃሳብ የበለጸጉ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ናቸው፡፡ የእስታርትአፕ ዋነኛ አላማም ይሄ ነው፡፡ ትውልዱ ሥራ ፈጣሪ ሆኖ ከተረጂነት እንዲወጣ፣ አቅሙን፣ ጊዜውን፣ ገንዘቡንና እውቀቱን በሀገር ግንባታ ላይ እንዲያውል አቅም የሚፈጥር አስተሳሰብ ነው፡፡

በነገራችን ላይ የሥራ አጥ ቁጥር ጨመረ ብለን ስናወራ ቀዳማይ መነሻችን ሊሆን የሚችለው የሥራ ፈጣሪዎች አለመኖር ነው፡፡ ሥራ ፈጣሪዎች አሉ ማለት የሥራ አጥ ቁጥር አይኖርም አሊያም ይቀንሳል። አሁን ላይ እንደሀገር የደረሰብን የኢኮኖሚ ድቀት፣ የድህነት መስፋፋት፣ የኑሮ ውድነት፣ የሥራ ማጣት እንዲሁም የጠባቂነት ልክፍት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ለሥራ ፈጣሪዎች ምቹ ካልሆነ ሁኔታዎች ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ነው፡፡

ስታርትአፕስ የኢኮኖሚ ሞተር ነው ካልን ሥራ ፈጣሪዎች በብዛትና በጥራት ሊኖሩን ይገባል፡፡ ሥራ ፈጣሪ ወጣቶች በሌሉበት ሁኔታ ስታርትአፕ የኢኮኖሚ ሞተር መሆን አይችልም፡፡ የጀመርናቸው ወጣት ተኮር የልህቀት ጅማሬዎች ሰፍተውና ገዝፈው ከድህነት እንደሚታደጉን እሙን ነው፡፡ ከልመና ወደልግስና በምናደርገው ግስጋሴም የራሳቸውን በጎ ዐሻራ አሳርፈው እንደሚታዩ ይታመናል፡፡

የለውጥ ቀስቱ ከግለሰብ ወደማህበረሰብ ነው፡፡ ማህበረሰብ እንዲለወጥ የግለሰብ ለውጥ ቀዳሚው ነው፡፡ ግለሰብ እንዲለወጥ ደግሞ እንደስታርትአፕ ያሉ የሥራ ፈጣሪ ምቹ መድረኮች እንዲበዙ ግድ ይላል፡፡ ይሄ እንዲሆን ምቹ ፖሊሲ፣ ምቹ ሁኔታ ወሳኝነት አለው፡፡ በለመድነውና ለማንም ምቹ ባልሆኑ መንገዶች ላይ ተጉዘን ለውጥ ማምጣት አንችልም፡፡ ለውጥ እንዲመጣ ነባር አስተሳሰቦቻችን መቀየር፣ ሳር ያላበቀሉ ኮቴዎቻችንን መለወጥ ያስፈልገናል፡፡

ፈረንጆች “ከፍጥነት አቅጣጫ ይበልጣል” ይላሉ፡፡ የቱንም ያክል ብንፈጥን የአቅጣጫ ለውጥ ካላደረግን ትርጉም የለውም፡፡ መንግሥት በጀት በመመደብ፣ ምቹ ምህዳርን በመፍጠር የአቅጣጫ ለውጥ አድርጓል፡፡ ሌሎች የተሻለ እምርታን ሊያመጡ ለሚችሉ ሁኔታዎች ካሉም ያንን በማድረግ ወጣቱን የሥራ ፈጣሪነት አቅም ለማሳደግ ቆርጫለሁ ብሏል፡፡ ከየትኛውም ሥራ ፈጣሪ ወጣት ጎን በመሆን አጋርነቱን ለማሳየትም ቃሉን ሰጥቷል፡፡ እንደነዚህ ዓይነቶች የአቅጣጫ ለውጦች ናቸው ከነባሩ ልምምድ አርቀው አዲስ ተሃድሶን የሚያጎናጽፉን፡፡

ለዚህ የተለያዩ የግልና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ኃላፊነት አለባቸው፡፡ እድገት በህብረት እንደሚመጣ ሁሉ የወጣቱ የነገ ተስፋም በሁላችንም ትከሻ ላይ የወደቀ ነው፡፡ በተለይ የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር የመንግሥትን የአቅጣጫ ለውጥ በመከተል የሥራ ፈጣሪዎችን ጉዳይ እንደተቀዳሚ የቤት ሥራው ወስዶ እየሠራ ይገኛል፡፡ ከጥቃቅን እስከ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ድረስ ላሉ ሥራ ፈጣሪዎች ፖሊሲ ከመቅረጽ ጀምሮ የትኛውንም አስፈላጊ ግልጋሎት ለመስጠት ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

መጪውን ጊዜ እንዲህ ባሉ በተሻሉና ለውጥ ተኮር በሆኑ እንቅስቃሴዎች መቃኘት እንደ ሀገር የማደጋችን፣ እንደ ማህበረሰብ ደግሞ ከተረጂነት የምንላቀቅባቸው አጋጣሚዎች መሆን ይችላሉ። ዓለም በሃሳብ ነው የተቀየረችው፣ ሃሳባውያን ሃሳባቸውን ወደተግባር እንዲቀይሩ መንገድ ጠራጊ ሥርዓት ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው። በስታርትአፖች የሥራ ፈጣሪነት ሀገራችን አዲስ የለውጥ ምዕራፍ ውስጥ እንደምትገባ እምነቴ ነው።

> **ሀገር ከግለሰብ ወደ ማህበረሰብ የሚሄድ የሃሳብ፣ የክዋኔ ውህድ ናት፡፡ የእያንዳንዱ ሥራ ፈጣሪ ወጣት ሃሳብ ማረፊያው ማህበረሰብ ነው፡፡ ብልጌትና ቤዞስ ከሆነች አንድ መንደር ተነስተው በሃሳባቸው በኩል ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ግልጋሎት እየሰጡ ነው፡፡ የእኛም ሀገር የሥራ ፈጣሪነት ጽንሰ ሃሳብ ከዚህ ተለይቶ ሊታይ አይገባም**

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ከሌማት ተርፎ ማቀነባበሪያ እየጠየቀ ያለው የወተት ምርት

ማህሌት አብዱል

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ከተመሠረቱ የወተት መንደሮች መካከል አንዱ በሆነው በእነ አቶ ሣሕሌ በርታ መንደር ተገኝተናል፡፡ አቶ ሣሕሌ በርታ በእንድብር ከተማ ልዩ ስሙ የሰሚ የተባለ አካባቢ ነዋሪ ናቸው፡፡ የባንክ ሠራተኛ ነበሩ፤ ጡረታ ከወጡ በኋላ የጡረታ ገንዘብ ብቻ መጠበቅ አልተመቻቸውም፤ የራሳቸውን ሥራ ለመጀመር ያስባሉ፡፡

ለእሳቸውም ሆነ ለቤተሰባቸው የሚሆን ሥራ ለመሥራትም ከልጆቻው ጋር ይመክራሉ፤ ማኅበር ያቋቁማሉ፡፡ በ2013 ዓ.ም የነበረቻቸውን አንዲት የተሻሻለ ዝርያ ያላት ላም መነሻ በማድረግ የወተት ሃብት ሥራ ለመጀመር ለከተማው አስተዳደር አመልክተው መሬት አገኙ፤ ከኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ደግሞ 150 ሺ በብር ተበደሩ፤ በዚህም ጊደሮች ገዝው የወተት ሃብት ልማቱን ማስፋፋቱን ተያያዙት፡፡

አቶ ሣሕሌ አሁን ከነጥጆቹ 12 የወተት ላሞች አሏቸው፤ ከእነዚህ መካከልም ስድስቱ ናቸው። ከእያንዳንዷ ላም በቀን ከ20 ሊትር በላይ ወተት በማለብና በመሸጥ ተጠቃሚ መሆናቸውን የሚገልጹት አቶ ሣህሌ፣ ‹‹ከዚህ ቀደም ቤተሰቤን ለማስተዳደር የገቢ አቅሜ ይፈትነኝ ነበር፤ አሁን ግን በወተት ምርቱ በማገኘው ገቢ በአስተማማኝ ሁኔታ ቤተሰቤን ከማስተዳደር አልፌ ኢኮኖሚዬንም እያሳደኩኝ ነው›› ሲሉ ያብራራሉ፤ በቀጣይም የተሻሻሉ ላሞቻቸውን ቁጥር ከፍ በማድረግ የወተት ልማታቸውን የማስፋፋት እቅድ አላቸው፡፡

አቶ ሣሕሌ ለዚህ ለመድረሳቸው የወረዳው አስተዳደር በተለይም የግብርና ባለሙያዎች ሚና ወሳኝ እንደነበረም ጠቅሰው፣ ‹‹በተለይ ሕክምና የሚሰጡ የግብርና ባለሙያዎች ሌት ተቀን ሳይሉ በፈለግናቸው ጊዜ ሁሉ እየተገኙ ድጋፍ ያደርጉልናል፤ ለዚህም ነው ምርታማነትን በተሳካ ሁኔታ ማምጣት የቻልነው›› ይላሉ፡፡

አቶ ሣሕሌና ቤተሰቦቻቸው አሁን በየቀኑ የሚያልቡትን ወተት ለአካባቢው ነዋሪዎችና ለካፍቴሪያዎች በማከፋፈል ይሸጣሉ፡፡ ሰባት የሚሆኑት ላሞች እርጉዝ በመሆናቸው የሚቀጥለው ዓመት የላሞቻቸው ቁጥር በእጥፍ ያድጋል፤ የወተት አቅርቦታቸውም በዚያው ልክ ከፍ ይላል፡፡ ይህ ሁኔታ አቶ ሣሕሌን ቢያስደስታቸውም፣ የላሞቻቸው ብዛት እየጨመረ እንዲሁም የሚመረተው ወተት መጠን ከፍ እያደረጉ በመጡ ቁጥር ወተቱን የሚረከባቸው እንዳያጡ ሰግተዋል፡፡

‹‹የወተት ሃብት ልማቱን የማስፋፋት ፍላጎት ቢኖረንም፤ ብዙ ባመረትን ቁጥር የሚወስድልን እንዳናጣ እንፈራለን፤ አሁንም ቢሆን የወተት መንደሩ እየተስፋፋ በመምጣቱ የወተት አቅርቦቱና ፍላጎቱ የሚመጣጠን አልሆነም›› ይላሉ፡፡ በአካባቢያቸው የወተትና የወተት ተዋፅዖ ማቀነባበሪያ ቢከፈት ወተታቸውን የሚረከባቸው እንደሚያገኙ ጠቅሰው፣ ይህ ሲሆን ከስጋት ነፃ እንሆናለን፤ ተጠቃሚነታችንም ያድጋል የሚል እምነት አላቸው፡፡ ‹‹የእኛ ተጠቃሚነት ባደገ ቁጥር ከተማችንንም እናሳድጋለን›› ሲሉ ይገልፃሉ።

በአካባቢው እንደመብራት፣ ውሃና መንገድ መሠረተ ልማት ያሉት አቅርቦት ችግር መኖሩም ሌላው ስጋታቸው ሆኗል፡፡ ችግሩ እንደእሳቸው በወተት ሃብትም ሆነ በሌላ የግብርና ኢንቨስትመንት ለመሠማራት የሚፈልጉ ግለሰቦችን እንደማይጋብዝም ነው ያመለከቱት፡፡ ‹‹በተለይ የመብራት ጉዳይ አንገብጋቢ ነው፤ በእኛ መንደር ብቻ ሰባት የወተት ማኅበራት አሉ፤ የዶሮና የንብ መንደሮችም እየተስፋፉ ነው ያሉት፤ ይሁንና በቂ መብራት ባለመኖሩ ምክንያት እኛም ልማታችንን ለማስፋፋት፤ አዳዲሶቹም እኛን አይተው እንዳይገቡ እንቅፋት እየሆነ ነው፤ ስለሆነም የሚመለከተው አካል አፋጣኝ ምላሽ ሊሰጠን ይገባል›› ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡


በሌላ በኩል የተሻሻሉ ዝርያዎች አባለዘር እና ለማባዛት ሥራው ወሳኝ ግብዓት የሆነው የናይትሮጂን አቅርቦት በዞኑ ከፍተኛ እጥረት መኖሩን ጠቅሰው፣ አርሶአደሩ በሚፈልገው ጊዜ የማዳቀል ሥራ ለመሥራት መቸገሩን አቶ ሣሕሌ አመልክተዋል፡፡ ይህም ከወረዳው አቅም በላይ መሆኑን ጠቅሰው፣ የሌሎች አካላት እገዛ



አቶ ሳህሌ በርታ፣



አቶ መሃመድ ሙደሲር፣



ፎቶ- ዳኜ አበራ

ወሳኝ መሆኑንም ነው የተናገሩት፡፡

የጉራጌ ዞን ግብርና መምሪያ ምክትል ኃላፊና የእንስሳት ዘርፍ ኃላፊ አቶ መሐመድ ሙደሲር እንደሚሉት፤ የሌማት ቱሩፋት መርሐ-ግብር በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በ2015 ዓ.ም በይፋ እንደሃገር ከተጀመረ ወዲህ በዞኑም የወተት፣ የዶሮ፣ የማርና ሥጋ መንደሮችን የማቋቋም ሥራ በስፋት ተከናውኗል፡፡ ከዚህም ባሻገር የዓሣ እርባታ በተለየ መንገድ በአካባቢው የማስለመድ ሥራ እየተሠራ ነው፡፡ በተለይም የወተት መንደር ልማት ሥራው በዞኑ ባሉ 10 ወረዳዎች፣ አምስት ከተማ አስተዳደሮችና 185 ቀበሌዎች ላይ 525 የወተት መንደር ለመመሥረት ታቅዶ ነው እየተሠራ ያለው፡፡

‹‹ለዚህም 60 የሚሆኑ ማኅበራት ተደራጅተው በወተትም በዶሮ እርባታም፤ በንብ ማነብና የሥጋ ከብት ልማት ላይ ተሰማርተው እየሠሩ ነው›› የሚሉት ኃላፊው፤ የወተት ሃብት ልማት ሥራ የሌማት ትሩፋቱ ከመተግበሩ በፊት በሦስት የማዳቀል ዘዴዎች በመሥራት የተሻሻሉ የወተት ላሞችን የማስፋፋት ሥራ ሲከናወን መቆየቱን ያመለክታሉ፡፡ ‹‹በዞናችን ያሉ አርሶአደሮች ቢያንስ አንድ የተሻሻለ ዝርያ ሊኖራቸው ይገባል ብለን እየሠራን ነበር›› ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

በዚህም በዞኑ ካሉ የቀንድ ከብቶች ውስጥ 23 በመቶ የሚሆኑት ብቻ የተሻሻለ ዝርያ እንዳላቸው አቶ መሐመድ ተናግረው፣ ቀሪው 77 በመቶ የሚሆነው የከብት ሃብት ዝርያ ለማሻሻል ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ‹‹በየዓመቱ 10 በመቶ የሚሆነውን ከብት ዝርያ ማሻሻል አለብን ብለን ትኩረት አድርገን እየሠራን ነው፤ በዚህ ዓመት 22 ሺ የዳልጋ ከብቶችን ዝርያ አሻሽለናል›› ሲሉም ይናገራሉ፡፡

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ የሌማት ትሩፋት መርሐግብር ዋና ዓላማ በምግብ እህል ራስን መቻል እንደመሆኑ በተለይም የዞኑን አርሶአደሮች የምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ ባለፈ የተመጣጠነ ምግብ እንዲኖራቸው በማድረግ መቀንጨርን ሙሉ ለሙሉ ለማስቀረት ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ነው፡፡

አሁን ባለው መረጃ በወተት ሃብት ወደ 120 ሺ የዞኑ ነዋሪዎች ተጠቃሚ ሆነዋል፤ በዶሮ ልማት ደግሞ 69 ሺ ፤ በሥጋ ሃብት ደግሞ ወደ 80 ሺ የሚጠጉ ነዋሪዎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ይህ ግን ለወጣቶች የተፈጠረውን የሥራ ዕድል እንደማያካትት አንስተው፤ ባለፈው ዓመት በተከናወነው ሥራ የእቅዱን 50 በመቶ ዞኑ ማሳካቱን ይጠቅሳሉ፡፡ መርሐ ግብሩ ለአራት ዓመታት ለመተግበር የታቀደ እንደመሆኑ ልማቱንም ሆነ ተጠቃሚነቱን የማስፋት ሥራ ከዚህም በላይ ይሠራል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ መሐመድ ገለጻ፤ የአርሶአደሩን ገቢ ከማሳደግ አኳያ በመርሐ-ግብሩ አርሶአደሩ በምግብ እህል ራሱን እንዲችል ከማድረግ በዘለለ የገቢ አቅሙን ከፍ የሚያደርጉ ልማቶችን እያከናወነ ነው፡፡ ዛሬ ዶሮ የሚያረባው አርሶ አደር እንቁላል ሸጦ ከብት እየገዛ ነው፤ ሃብቱን እያሰፋና ኑሮውን እየለወጠ ነው፡፡ በተለይም ደግሞ ከእርዳታ ጠባቂነት ተላቆ ሌሎችን የሚጠቅም እንዲሆን፤ ሃገሩንም የሚገነባ ትውልድ ለመፍጠር የዞኑም ሆነ የክልሉ መስተዳድር በመቀናጀትና በመናበብ ትኩረት አድርገው እየሠሩ ናቸው፡፡

እነአቶ ሣሕሌ ያነሷቸውን ጥያቄዎች በሚመለከት ለቀረባለቸው ጥያቄ በሰጡት ማብራሪያም ‹‹የተነሱ ጥያቄዎች ትክክል ናቸው፤ እኛም ሥራውን በቅርበት እየተከታተልን ስለሆነ እናውቃቸዋለን፤ በተለይም የክልልና የፌደራል መንግሥት መውሰድና መፍታት ያለበት ችግር የአባላዘርና የናይትሮጂን አቅርቦት ችግርን ነው፤ ክልላችን ውስጥ ሆሳዕና ላይ ብቻ አንድ ማዕከል አለ፤ እሱም ከተበላሸ በክልሉ ዞኖች በሙሉ ሥራ ያቆማሉ›› ይላሉ፡፡ በተለይም ላሞች የኮርማ ፍላጎት በሚያሳዩበት ጊዜ ቶሎ የማዳቀል ሥራ ካልተሠራ በትንሹ ለ21 ቀናት ያህል የወተት ምርቱም የሚከስርበት ሁኔታ ይፈጠራል፤ ይህም የወተት አልሚዎቹን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ የዞኑ አስተዳደር ለክልሉም ሆነ ለፌደራል መንግሥት የናይትሮጂን ማዕከል ግንባታ እንዲከናወን ጠይቋል፤ ይሁንና እስካሁን ችግሩ አልተፈታም፡፡ በተመሳሳይ በዞኑ የዝርያ ማሻሻያ ማዕከል የነበረ ቢሆንም የማሻሻያው ማሽን በመበላሸቱ ላለፉት ሰባት ዓመታት አገልግሎት አልሰጠም፡፡ በመሆኑም የሚመለከተው የመንግሥት አካል የናይትሮጂን ማዕከላት በየአካባቢውና ለአርሶ አደሩ በሚቀርቡበት ሁኔታ እንዲገነባ ድጋፍ ማድረግ፤ የዝርያ ማሻሻያ ማሽኑንም ማሽን መጠገን፤ አልያም በአዲስ የመተካት ሥራ ይጠበቅባቸዋል፡፡

‹‹አርሶአደሩ ያነሷቸው የመንገድ፤ የውሃና መብራት ጥየቄዎችም ቢሆኑ ትክክለኛ ናቸው፤ እኛም ይህን ጉዳይ እንደ አንድ የልማት አጀንዳ ይዘን እየሠራን ነው›› የሚሉት አቶ መሐመድ፣ በተለይም ኮረብታማና ዳገታማ አካባቢዎችን ለማስተካከልና ለልማትና እንቅስቃሴ ምቹ ለማድረግ በዞኑ አቅም የሚቻለውን ሁሉ ለመሥራት እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ ከመብራት ጋር ተያይዞ የትራንስፎርመር ተከላ ጥያቄውም ዞኑ ተገቢነቱን እንደሚያምን ተናግረው፤ ይህንንም ጉዳይ በተደጋጋሚ በደብዳቤም ሆነ በቃል ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ማቅረቡን ያስረዳሉ፡፡ አፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኝም ከክልሉ ኃላፊዎች ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ የውሃ መሠረተ ልማት ችግርም እንዲሁ ከተማ አቀፍ መሆኑን አንስተው፣ ይህንንም በዘላቂነት ለመፍታት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ነው የተናገሩት፡፡

‹‹ ከገበያ ጋር በተያያዘ የተነሳው ጥያቄ ግን ብዙም የሚያሳስብ አይደለም፤ ከዚህ ቀደም በዚህን ያህል መጠን ይመረት ስላልነበር ተረካቢ አካል ስጋት ይሆናል ተብሎ አልታሰበም›› ሲሉ ገልጸው፣ የመርሐ ግብሩም ዋና ዓላማ የእያንዳንዱን ቤተሰብ የምግብ ዋስትና ማረጋገጥና የተመጣጠነ ምግብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፤ የእኛም ትኩረታችን እዚህ ላይ ነው›› ብለዋል፡፡ በቀጣይ ከወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ጋር የማስተሳሰር ሥራ በመሥራት ስጋቱን እንዲቀረፍ ጥረት እንደሚደረግ አስታውቀው፣ በአካባቢው ቢያንስ አንድ ማቀነባበሪያ እንዲገነባ ለባለሃብቶች ጥሪ እያቀረብን ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

የክልሉ ርዕሰ መስተዳደር አቶ እንዳሻው ጣሰው ከኢፕድ ጋር በነበራቸው ቆይታ በአርሶአደሮቹ የተነሱትን ጥያቄዎች አስመልክተው ሲገልጹ፤ ‹‹የወተት ምርት ጉዳይ በሁለት መንገድ መመለስ መቻል አለበት የሚል እምነት አለን›› ብለዋል፡፡ እሳቸው እንዳብራሩት፤ አንደኛው እንደተባለው ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎችን በየአካባቢው ማስፋፋት፤ በሁለተኛ ደረጃ የስርጭቱን ማስፋፊያ መንገድ መቀየስ ይሻል፡፡

የሚያመርተው አካል መሸጥ ብቻ ሳይሆን ተጠቃሚ ሊሆን ይገባል ሲሉም ጠቅሰው፣ ምክንያቱም የግብርና ልማታችን አንዱ አጀንዳ ኅብረተሰባችን የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኝ ማድረግ ነው›› ሲሉ መናገራቸው ይታወሳል፡፡ ‹‹አንዳንድ ቦታ ላይ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ሃብታም መሆን ጀምረዋል፤ የተለያዩ ምርቶችን ያመርታሉ፤ ግን ምርቱን አይጠቀሙትም፤ የሰው ለውጥ ደግሞ የሚታየው መጀመሪያ እሱና ቤተሰቦቹ የተመጣጠነ ምግብ ማግኘት ሲችል ነው፡፡ በአጠቃላይ ግን እንደ ክልል እየተሠራ ያለ ነገር አለ፤ ጥያቄያቸውም ትክክል ነው ብለን ነው የምንወስደው›› በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በሌላ በኩልም አቶ እንዳሻው እንደተናገሩት፤ በመሠረተ ልማት ረገድ የክልሉ በጀት በፈቀደ መጠን የገጠርም ሆነ የከተማ መንገዶች እየተሠሩ ነው፡፡ አንዳንድ የመንገድ ግንባታዎች አምስትና ከዚያ በላይ ዓመታት የፈጁ አሉ፤ አሁን በተቀመጠው አቅጣጫ 95 በመቶ በላይ ያለቁ ጉዳዮች እነሱን ማስጀመር ነው። አንዳንዱ መንገዱ ይያዝና ድልድይ የለውም፡፡ግን መንገድ የሚባለው ድልድዩን ጨምሮ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ጉድለቶች ነበሩ፤ እሱን የማስተካከል ሥራ ተሠርቷል፡፡ ሆኖም ከኅብረተሰቡ ፍላጎት አንፃር ግን የሚቀረን ብዙ ነገር አለ፤ እሱ ላይ ተረባርቦ መሥራት ይገባል፡፡

‹‹በውሃ ላይ በብዙ ቦታ በደንብ እየተሠራ ነው፤ ከከርሰምድር የማውጣት፣ የማጎልበት፣ የማስጠናት ሥራዎች እየተከናወኑ ናቸው፤ ሰው አማራጭ ንፁሕ የመጠጥ ውሃ እንዲያገኝ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ጥሩ ናቸው ብለን ነው የምንወስደው፡፡ ለምሳሌ የወልቂጤ ከተማ በወር አንዴ ነበር ውሃ የሚያገኘው፤ አሁን ቀኑን አሳጥረነዋል፡፡ በአስር ቀንና ከዚያ በታች ውሃ ያገኛል፡፡ ከዚህ ቀደም ሆቴል ያደረ ሰው ውሃ የማያገኝበት ሁኔታ ነበር፤ አሁን ግን ቢያንስ በባልዲ የሚያገኝበት ሁኔታ አለ። አሁንም አቅም በፈቀደ መጠን የኅብረተሰቡን ጥያቄ እንመልሳለን ብለን እናስባለን›› ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ማህበራዊ
# አስኳላ

# 12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናና የተማሪዎች ዝግጅት

**ግርማ መንግሥቴ**

የባለፈው ዓመት የ12ኛ ክፍል አጠቃላይ መልቀቂያ ፈተና ውጤት አስደሳችነቱ ሲጠበቅ አስደንጋጭነቱ ታውጆ በወቅቱ ፈጥሮት የነበረው አሳዛኝ ስሜት የሚረሳ አይደለም። ጉዳዩ ወደፊትም ቢሆን፣ በተለይም በትምህርት ምሁራን ዘንድ፣ ሳይጠቀሱ ከማይታለፉት ትምህርታዊ ጉዳዮች (መጥፎ ገጠመኞች) መካከል ፊት መሪው እንደሚሆን ይጠበቃል። ወደፊት የሚመጡት የትምህርት ዓለም ሰዎች እንዳይደግሙት በአስተማሪነቱ ሁሌም ቢሆን የሚጠቀስ እንጂ በይሁነኝ ሊታለፍ የሚችል ተራ ጉዳይ አይሆንም።

በተለይ በወቅቱ እንደ አጠቃላይ በማህበረሰቡ፤ እንዲሁም ከራሱ ከተፈታኙ ተማሪው ጀምሮ ቤተሰብ፣ መምህራን፤ እንዲሁም ከአካባቢና የትምህርት ባለሙያዎች ጀምሮ መላው ህብረተሰብን ያሳዘነ፤ ቆም ብሎም እንዲያስብ እድል የሰጠ፤ ከፖሊሲ ጀምሮ በርካታ ነገሮች ዳግም እንዲፈተሹና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ይሻሻሉ ዘንድ የሚያስገድድ ውጤት ነበር ባለፈው ዓመት የተመዘገበው ያለፉ ተፈታኞች በመቶኛ 3ነጥብ2 ሆኖ የተመዘገበበት።

በወቅቱ የሚመለከታቸው፣ "ከፈረሱ አፍ" እንዲሉ የጉዳዩ ባለቤት የሆኑ ተቋማት እና የየተቋማቱ አስተዳዳሪዎች ሲናገሩት እንደነበረው፤ የተገኘው ውጤት "እጅግ አስደንጋጭ" ብቻ ሳይሆን እጅግም አሳፋሪ ነበር። የዚህ ደግሞ መነሻው ከዛ በፊት በነበሩት ዓመታት በትምህርት ላይ የተሠራው አሻጥር ሲሆን፤ ይህ አሻጥር ከስሩ ተመንግሎ እስካልተጣለ ድረስ ችግሩ የመጨረሻ እልባት ሊያገኝ አይችልም።

በወቅቱ፣ የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ሰጥተውት በነበረው መግለጫ እንዳሉት "በ2015 ዓ.ም 845ሺህ ተማሪዎች ፈተናው ላይ ተቀምጠው የማለፊያ፣ ወይም ከግማሽ በላይ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች 27ሺህ 267 (3ነጥብ2 በመቶ) ሲሆኑ፤ (19ሺህ 17 ከተፈጥሮ ሳይንስ፤ 8ሺህ 250 ተማሪዎች ደግሞ ከማህበራዊ ሳይንስ) ብቻ" ነበሩ። ዘንድሮ ይህ ሁሉ ወደኋላ መቅረት፤ ይህ ሁሉ ጉዳትና ሀገራዊ ኪሳራ... ተወግዶ አዲስ ውጤት ይመዘገባል የሚል የብዙዎች ተስፋ ከወዲሁ በስፋት እየሄደ ይገኛል።

ባለፈው ዓመት 649 የተፈጥሮ ሳይንስ ከፍተኛው ውጤት ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን፤ በማህበራዊ ሳይንስ ደግሞ 533 ሆኖ መመዝገቡ ይታወሳል። ይህም ዘንድሮ፣ የፀጥታ ችግር ያለባቸውን አካባቢዎች ሳይጨምር ከ670ሺህ በላይ ተፈታኝ ተማሪዎች ለፈተና ተመዝግበው እየተጠባበቁ ባሉበት ሁኔታ፣ የአምናው ውጤት በከፍተኛ የተፈታኝ ተማሪዎች ጥረት ይቀየራል፤ ተቃራኒ በሆነ መልኩም ይለወጣል ብለው ሃሳባቸውን ከወዲሁ በመሰንዘር ላይ ያሉ ወገኖች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

በ2015 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ከተፈተኑት ተማሪዎች መካከል ደግሞ 3ነጥብ2 በመቶ (ወንድ 18ሺህ 383፤ ሴት 8884) የሆኑት ብቻ ከ50 በመቶ በላይ ማምጣታቸውን ተከትሎ በወቅቱ፣ በተለይ የጉዳዩ ባለቤት በሆነው፣ በትምህርት ሚኒስቴር አማካኝነት አስደንጋጭ ተብሎ ሲነገር፤ "አስደንጋጭ" የተባለው ውጤት እንደሚያሳየው ለፈተና ከተቀመጡት ከ980ሺህ በላይ ተማሪዎች መካከል 30ሺህ ገደማ ብቻ ከ50 በመቶ በላይ ውጤት ማግኘት የቻሉ መሆኑ ሲታወጅ ያልተከዘ፤ ቆም ብሎ ወደ ኋላ እና ወደፊት ያላሰበ፤ "ችግሩ ምንድን ነው?" በማለት ራሱንም ሆነ ሌላውን ያልጠየቀ አልነበረም። "ከ50 በመቶ በታች ያመጡ ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲ መቀላቀል" እንደማይችሉ ሲገለፅም እንደዛው።

ኢዜአ "ዘንድሮ በሚሰጠው የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ተማሪዎች የተሻለ ውጤት እንዲያመጡ የቅድመ ዝግጅት ሥራ በትኩረት እየሠሩ መሆናቸውን አስተያየታቸውን የሰጡ የአፋርና አማራ ክልል ትምህርት ቢሮዎች ገለፁ።" (ኅዳር 13/2016) በማለት የዘገበውም ሆነ ሌሎች እዚህ ያልጠቀስናቸው የአምናውን 3ነጥብ2 በመቶ ለመቀልበስና የተሻለ



ተማሪ ሲያ ገብሩ፣

ውጤት ለማምጣት ቀን ከሌት በመሥራት ላይ እንደሚሆኑ ከወዲሁ መገመት ይቻላልና ከአምናው ዘንድሩ ጥሩ ውጤት ይጠበቃል።

"ባለፈው ዓመት የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ከወሰዱት 5ሺህ 300 የክልሉ ተማሪዎች መካከል ከ50 በመቶ በላይ ያመጡት 19 ተማሪዎች ብቻ" መሆናቸውን፣ የዚህ ምክንያቱ ደግሞ "ዓመታትን ያስቆጠረ የትምህርት ጥራት ችግር" መሆኑን ለጣቢያው የተናገሩት የአፋር ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ አብዱ ሀሰን ይህንን ውጤት ለመቀልበስና ከአምናው የተሻለ ውጤት ለማምጣት "ይህን ውጤት ለማሻሻል በክልሉ ያሉ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ከመደበኛ ክፍለ ጊዜ ውጭ የማጠናከሪያ ትምህርት እየተሰጠ" ይገኛል፤ በተጨማሪም "በክልሉ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውና በትምህርታቸው የተሻሉ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር የ'አፋር ታለንት አካዳሚ' ተቋቁሞ ወደ መማር-ማስተማር ስራ ገብቷል"።

ትምህርት ሚኒስቴር ከተፈታኞች ውስጥ 96 በመቶዎቹ ከግማሽ በታች ውጤት ማምጣታቸውን መግለፁን ተከትሎ፣ "ችግሩን ለመፍታት ከመምህራን፣ ከርዕሰ መምህራን፣ ከተማሪ ወላጆችና ከተማሪዎች ጋር ሰፊ ውይይት መደረጉንና ከችግሩ ለመውጣት በአብሮነት መሠራት እንደሚያስፈልግ መግባባት ላይ" መደረሱን ከላይ የተጠቀሱት የዘርፉ ኃላፊዎች የተናገሩ ሲሆን፣ በሌሎችም ተመሳሳይ እንቅስቃሴዎች ተደርገው ከሆነ የባለፈው ዓመት የ3ነጥብ2 ከመቶ ውጤት ተቀልብሶ የዘንድሮው የዚህን ግልባጭ ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ መገመት ይቻላል። "ከትምህርት ቤቶችና ተማሪዎች ጀምሮ ሁሉም ያለበትን ሃላፊነት በየደረጃው እንዲወጣ አቅጣጫ አስቀምጠን በቅድመ ዝግጅት ላይ እየሰራን ነው" የተባለውንም ለሌሎች ተሞክሮ ሊሆን የሚችል ከመሆኑ አኳያ እዚህ መጥቀሱ ተገቢ ይሆናል።

በያዝነው ዓመት ሰኔ ወር ላይ ይሰጣል ተብሎ የጊዜ ሰሌዳ የተጣለለት ብሔራዊ መልቀቂያ ፈተና ከሌሎቹ ዓመታት ለየት የሚያደርጉት በርካታ ጉዳዮች ያሉ ሲሆን፤ እንደ ፈተናዎች ድርጅት ከሆነ የፈተና ዝግጅት ሥራው የሀገሪቱን ሥርዓተ ትምህርት የተከተለ እና ተማሪዎቹን በአግባቡ መመዘን በሚያስችል መልኩ መዘጋጀቱ፤ ተማሪዎች በሥነ-ልቡና እራሳቸውን እንዲያዘጋጁ የተለያዩ ተግባራት መከናወናቸው፤ ተማሪዎች የሚፈተኗቸውን የትምህርት ዓይነቶች አውቀው ዝግጅት እንዲያደርጉ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር መከናወኑ፤ ብሔራዊ ፈተናው ለ3ኛ ጊዜ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሚሰጥ መሆኑ፤ ትምህርት ሚኒስቴር ለተፈጥሮ ሳይንስ እና ማኅበራዊ ሳይንስ የትምህርት መስኮች፣ ለእያንዳንዳቸው በስድስት የትምህርት ዓይነቶች እንዲሰጥ በወሰነው መሠረት የሚከናወን መሆኑ፤ ባለፈው ዓመት በአማካይ "1 ሺህ 326 ትምህርት ቤቶች ደግሞ አንድም ተማሪ" ያላሳለፉበት ሁኔታ መኖሩና ዘንድሮ ያ ዳግም ይከሰታል ተብሎ የሚጠበቅ



ፎቶ- ዳኜ አበራ፤

ተማሪ ናሆም መስፍን፣

አለመሆኑ ወዘተ የሚጠቀሱ ናቸው።

ይህንኑ ፈተና በተመለከተ፣ ምንም እንኳን የብሔራዊ ፈተናዎች ድርጅት "ፀጥታ በሌለባቸው አንዳንድ አካባቢዎች" በሚል ቢያልፈውም፣ በሀገሪቱ ፀጥታ ያለ መኖሩ ጉዳይ ከፍተኛ ችግር ስለመሆኑ አመላካች አካባቢዎች መኖራቸው አልቀረም።

የአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ ተተኪ ኃላፊ አቶ ፀጋ ተሰማ ሰሞኑን እንደገለፁት በብሔረሰብ አስተዳደሩ ስር የሚገኙ 43 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 12ኛ ክፍል ያሏቸው ቢሆንም፣ በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ሳቢያ መማር-ማስተማር በሚከናወንባቸው 20 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብቻ ያሉ ተማሪዎች ናቸው ሀገራዊ መልቀቂያ ፈተናውን የሚወስዱት። ይህ፣ ከግማሽ በላይ ትምህርት ቤቶችን ከፈተና ውጭ ያደረገው በቂ ማሳያ ነውና የሰላም ማጣት ትርጉሙ ምን እንደሆነ፤ የጉዳቱ ወሰን የት ድረስ እንደሆነ በእግረ መንገድ ሳይሆን በቀጥታ የሚለው አለና ልብ ያለው ሁሉ ልብ ሊል ይገባዋል።

የባለፈው ዓመት 3ነጥብ2 በመቶ ውጤትን በተመለከተ የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትሩ ብርሃኑ ነጋ ውጤቱን ይፋ ባደረጉበት ወቅት "የመግቢያ ፈተናዎቹ ውጤት ማሽቆልቆል ትምህርት ቤቶች፣ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የተማሪዎች ወላጆች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ለትምህርት ጥራት ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጡ ማንቃቱ"ን መግለፃቸው የሚታወስ ነው። በዚሁ የሚኒስትሩ መግለጫ መሠረት አስፈላጊው ሥራ ሁሉ ተሰርቷል ተብሎ ይገመታል ብቻ ሳይሆን ይጠበቃል። በመሆኑም ከባለፈው ዓመት በተሻለ ከዘንድሮው የተሻለ ውጤት ይገኛል ተብሎም ይታሰባል። አምና "አምስት ትምህርት ቤቶች ሁሉንም ያስፈተኗቸውን ተማሪዎች" እንዳሳለፉ የተመሰከረላቸው ሲሆን፤ ዘንድሮ ይህ ቁጥር በሁለት ዲጂት ያድጋል የሚሉ ወገኖችም አሉ።

ወደ ተፈታኝ ተማሪዎች እንምጣ፤ ዝግጅታቸው ምን እንደሚመስልም እንመልከት። ጨዋታችንንም አላማውን "በተግባር የተደገፈ ትምህርት በመስጠት የላቁ ተመራማሪዎችን ማፍራት" ካደረገው፤ ለየት ያለ የማስተማር ሥነ-ዘዴን በመጠቀም፣ ከመደበኛው ትምህርት አሰጣጥ የተለየ መንገድን በመከተል ላይ ከሚገኘው፤ በአንድ የውጭ ዜጋ በሆኑ መምህር፣ በከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ እና በኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎች ማፍራትን አላማው አድርጎ ወደ ሥራ ከገባው፤ በአጭር ጊዜም ስሙን ከገነባው፤ በኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ስር ከሚተዳደረው፤ ከኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ቀዳማዊ ምኒልክ ሳይንስ ሼርድ ካምፓስ እንጀምር።

በካምፓሱ ተገኝተን በጥብቅ ዲሲፕሊን የሚመራውን የመማር-ማስተማር ተግባር ከተመለከትን በኋላ ተማሪዎች ለ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና እያደረጉ ያሉትን ዝግጅት በተመለከተ አስተያየት ለመውሰድ በካምፓሱ አግኝተን ያነጋገርናቸው ሊያ ገብሩ እና ናሆም መስፍን የሚከተለውን ብለውናል።

እንደ 12ኛ ክፍሏ ተማሪ ሊያ ገብሩ አስተያየት ከሆነ ፈተና ማለት ምንም ማለት አይደለም። ከሌሎች ፈተናዎችም ተለይቶ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ አይደለም። በፕሮግራም እስከ ተመራን ድረስ፤ በአግባቡ ትምህርታችንን እስከ ተከታተልን ድረስ፤ እስካጠናን እና የቤተሰቦቻችንን እና የመምህራኖቻችን ምክር እና አስተያየት እስከ ሰማን ድረስ ማትሪክ ፈተና ምንም ሊያሳስበን የሚችል የፈተና ዓይነት አይደለም። በቀላሉ ልናልፈው የምንችለው ፈተና ነው።

ሌላው እንግዳችንና የዚሁ ክፍል እና ትምህርት ቤት ተማሪ ናሆም መስፍንም በዚሁ በሊያ አስተያየት ይስማማል። እሱ እንደሚለው ከሆነ ለተማሪ ፕሮግራም ማለት ቁልፍ ጉዳይ ነው። በፕሮግራም መመራት የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታ ነው። በፕሮግራም ማጥናት፣ በፕሮግራም መጫወት፣ በፕሮግራም መተኛት ወዘተ ለተማሪ መሠረታዊ የሕይወት መርሆች መሆን አለባቸው። ካልሆነ ብዙ ነገሮች ይበላሻሉ።

መኖሪያዋ ገርጂ አካባቢ የሆነው ሊያ ገብሩ እንደምትመሰክረው ከሆነ ለውጤታማነቷ የመምህሮቿና የአጠቃላይ የካምፓሱ አስተዳደር ድርሻ እንዲህ በቀላሉ የሚታለፍ ወይም የሚታይ ጉዳይ አይደለም። ባለውለታዎች ናቸው። ያለ እነሱ መልካም እና ቤተሰባዊ ተግባር ስለ ጥሩ ውጤት መናገር አይቻልም። ይመክሯቸዋል። ያግዟቸዋል። በተለይ ከማትሪክ ጥያቄዎች ጋር በተያያዘ እንዲለማመዱ የሚያደርጉላቸው ከፍተኛ ጥረት ቀላል አይደለም።

ከሰሚት አካባቢ የመጣው ናሆም እንደነገረን ከሆነ እሱ ለጥናት የሚፈልገው አካባቢ በፀጥታ የተሞላ ሲሆን፤ ጊዜውም ሌሊት ቢሆን ይመርጣል።

ከኬጂ እስከ 8ኛ ክፍል በሁለት ትምህርት ቤቶች (ሀርመኒ እና ሳፋሪ አካዳሚ) ትምህርቱን የተከታተለውና ከፍተኛ ውጤት በማምጣት ወደ ኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ቀዳማዊ ምኒልክ ሳይንስ ሼርድ ካምፓስ የገባው ተማሪ ናሆም ከትምህርት ቤት ይገባል፤ ካስፈለገ ትንሽ ዘና ይላል፤ በጊዜ ይተኛል፤ ሰዎች ከተኙ በኋላ በመነሳት ያጠናል፤ ካስፈለገም ያነጋል።

እንደ ናሆም አስተያየት ዘንድሮ 12ኛ ክፍሎች ስድስት ስድስት የትምህርት ዓይነቶችን ይፈተናሉ። እንደ የአንድ ትምህርት ተቋም ተፈተኞች (ባች) ሁሉም በሁሉም ከፍተኛ ውጤት በማምጣት የትምህርት ቤቱን የውጤት የበላይነት ማስጠበቅ ይፈልጋሉ። በዚሁ መሠረትም እየተዘጋጁ ይገኛሉ። በመምህራን በኩልም እየተደረገላቸው ያለው እገዛ ይህንን ታሳቢ ያደረገ ነው።

ትምህርቷን እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ በቪዥን አካዳሚ በመከታተል፤ ከፍተኛ የሚኒስትሪ ውጤት በማውጣት ወደ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ቀዳማዊ ምኒልክ ሳይንስ ሼርድ ካምፓስ የመጣችው ሊያም እንደ ትምህርት ተቋም ሁሉም ከፍተኛ ውጤት ማምጣትን ታሳቢ አድርገው ነው እየተዘጋጁ ያሉት። መምህራኖችም የማትሪክ ጥያቄዎችን ከማለማመድ ጀምሮ በቅርብ በመከታተልና በመርዳት እያደረጉ ያሉት ይህንኑ እነሱን የማብቃት ሥራ ነው።

የግል ዝግጅቷን በተመለከተም እንደምትናገረው ማትሪክ ነው ብላ ምንም የምታካብደው ነገር የለም፤ ከመማሪያ-ማስተማሪያ መጻሕፍት ጀምሮ፤ አጋዥ መጻሕፍትን አካትቶ የማታነባቸው ተያያዥ ጽሁፎች የሉም። በመምህራን በኩል የሚቀርቡ ገለፃዎችንም ሆነ የላቦራቶሪ ሙከራዎችን በጉጉትና በፍቅር ነው የምትከታተለው። ወለም ዘለምን አታውቅም።

የሊያ እና የኖሆም የመጨረሻ አስተያየትና የአቻ ምክር የዘንድሮ ተፈታኞች በሙሉ በርትተው ማጥናት፣ ማጥናት፣ ማጥናት ያለባቸው መሆኑ፤ ገና ለገና ብሔራዊ ፈተና ነው ብሎ ማካበድና ከባድ አድርጎ ማየት የማያስፈልግ መሆኑ ላይ የተመሠረተ ሲሆን፤ በራስ የአጠናን ስልትና ፍላጎት መሠረት አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ላይ ያተኮረ ነው። እኛም የእነዚህኑ ጎበዛዝት ምክርና አስተያየት በማጋራት አበቃን።

**መልካም ፈተና!!!**

# ወቅታዊ

## «ግብርናችን በጥሩ የእድገት ጉዞ ላይ ነው»

**- አቶ ሑስማን ሱሩር**
**በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳደር ማዕረግ**
**የግብርንና ገጠር ልማት ክላስተር አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ኃላፊ**



ፎቶ፦ ዳኜ አበራ

ማህሌት አብዱል

ኢትዮጵያ የተቀናጀ ግብርና ልማት መተግበር በመጀመሯ በዘርፉ ተጨባጭ ለውጥ እያመጣች መሆኑ ይጠቀሳል፡፡ በዋናነት የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ የምግብ ሥርዓትን ከማሻሻል አኳያ እምርታ እያሳየች ትገኛለች፡፡ እያንዳንዱ አርሶ አደር ከራሱ አልፎ ለሌሎች የሚተርፍ ምርት እንዲያመርት በማድረግ የሌማት ቱሩፋት መርሃ ግብርና የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራም አወንታዊ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ፡፡ እነዚህን መርሃ ግብሮች በመተግበር ከፍተኛ ውጤት እያመጡ ካሉ ክልሎች መካከል የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል አንዱ ነው፡፡

ክልሉ እንደ አዲስ ከተመሠረተ ወዲህ ከሌማት ቱሩፋት ጎን ለጎን 30-40-30 ብሎ በነደፈው ኢኒሼቲቭ አማካኝነት እያንዳንዱ አርሶ አደር በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከ100 በላይ የፍራፍሬ ችግኝ እንዲኖረው በማድረግ የራሱን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና ብሎም የገቢ አቅሙን ለማሳደግ እያስቻለው መሆኑን ይገለፃል። በክልሉ እየተከናወነ ያለውን የግብርና ሥራ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጋዜጠኞች ቡድን በቅርቡ የመስክ ጉብኝት ማድረጉ ይታወሳል፡፡

ይህንን በሚመለከት አዲስ ዘመን ጋዜጣ በምክትል ርዕሰ መስተዳደር ማዕረግ የክልሉ የግብርንና ገጠር ልማት ክላስተር አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ሑስማን ሱሩር ጋር ቆይታ አድርጐ እንደሚከተለው አቅርቦላችኋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ክልሉ እንደ አዲስ ከተደራጀ በኋላ የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻልና ልማትን ለማም ጣት ምን እየተሠራ ነው?**

**አቶ ሑስማን፡-** እንደሚታወቀው ክልላችን ከተመሠረተ ገና ስድስተኛ ወሩ ነው፡፡ ባለፈው ዓመት ነሐሴ 15 በአዲስ መልክ ሲደራጅ ብዙ ውስብስብ ችግሮች የነበሩበት ቢሆንም፤ ነገር ግን አመራሩ በነበረው አብሮነት፤ የጋራ ራዕይና የተቀናጀ እንዲሁም የተናበበ እይታ ስለነበረ ክልሉ በተመሠረተበት እለት ቁጭ ብሎ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ውይይት አድርጓል፡፡

በሶስተኛው ቀን የአመራር ምደባ ተደርጓል። አመራሩ በእለቱ ያስቀመጣችው መሠረታዊ ጉዳዮች ነበሩ፡፡ ከጉዳዮቹ መካከል ሕዝቡ ሰፊ የልማት ጥያቄ አለው፡፡ በአብዛኛው በሚባል ደረጃ በንግድ እንቅስቃሴ ያለ በመሆኑ ለቴክኖሎጂ እና ለመረጃ ቅርብ ነው፡፡ ለምሳሌ የከንባታን ሕዝብ ብናነሳ በየትኛው የሀገሪቱ ክፍል በተለያዩ ሥራዎች ላይ ተሰማርቶ የሚገኝ ታታሪ ሕዝብ ነው፡፡ ሃድያም በተመሳሳይ ከሀገር ውስጥ እስከ ውጭ በንግድና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ላይ ነው። ጉራጌና ስልጤም እንደ ሀገር ሥራ ፈጣሪ የሚባሉ ማህበረሰቦች ናቸው፡፡ ይሄ በጥቅሉ ክልሉን ለማሳደግ ትልቅ እድል ነው፡፡

ክልሉ ሲመሠረት አመራሩ የተነሳው በአንድ እጁ ሽግግሩን በሌላኛው እጁ ልማቱን ይዞ ነው፡፡ ልማቱን ለማምጣትም ለአፍታም ቢሆን ማሸለብ አይፈቀድም። ከተቻለ ከ14 እስከ 16 ሰዓት መሥራት ያስፈልጋል። ለዚህም መሰጠት፤ ቁርጠኝነትና ፅናት ይጠይቃል፡፡ ክልሉ ራሱን ችሎ ሲደራጅ የመጀመሪያው ጉዳይ የ30 እና የ40 ዓመት ጥያቄዎችን ወዲያውኑ መልሷል፡፡ ከእነዚህም መካከል የዞንና ልዩ ወረዳ እንሁን ጥያቄዎች ወዲያውኑ ምላሽ እንዲያገኙ አድርጓል። እነዚህን ጥያቄዎች እየመለሱ በሌላ እጅ ደግሞ ልማትን በተሳካ ሁኔታ መምራት ስለሚያስፈልግ አስተባባሪው እንደ አንድ አካል ሆኖ እየሠራ ነው።

በዚህም መሠረት አምስት ዋና ዋና ጉዳዮችን የለየን ሲሆን፤ የመጀመሪያው በክልሉ አስተማማኝ ሰላም ማስፈን ነው፡፡ ሁለተኛው ቁልፍ ጉዳይ የግብርና ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ሲሆን በመቀጠልም የክልሉ የገቢ አቅም ከፍ ማድረግና ሥራ እድል ፈጠራን ማስፋት የሚሉ ጉዳዮችን በቅደም ተከተል አስቀምጠን ወደ ሥራ ገብተናል። ወደ ተግባር ሲገባም የ100 ቀን እቅድ ያቀድን ሲሆን፤ ለእዚህም ስኬት በእጃችን ያሉ እድሎችንና ምቹ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። በሁሉም ዘርፍ ያሉ አንኳር ሥራዎች ለአፍታም ሳይዛነፉ እንዲተገበሩ ጥረት ስናደርግ ቆይተናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በተለይም የግብርናውን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እያከናወ ናችሁ ባላችሁት ሥራ ምን ያህል ውጤታማ እየሆናችሁ ነው?**

**አቶ ሑስማን፡-** አስቀድሜ እንዳነሳሁት ክልሉ ሲመሠረት ቁልፍ ጉዳይ አድርጎ ከያዛቸው የልማት መርሃ ግብሮች መካከል የግብርናውን ምርትና ምርታማነትን በላቀ ደረጃ ማሳደግ ነው፡፡ ለእዚህም መሳካት የተቀናጀ ግብርና ልማትን ለመተግበር ሰፊ ንቅናቄ አድርገናል። በዚህም ንቅናቄ ሰባት መሠረታዊ ጉዳዮች የተያዙ ሲሆን፤ በወቅቱ በነበረው ተጨባጭ ሁኔታ የመኸር ምርትን ሳይዛነፍ መተግበር ዋናው ሥራችን አድርገን ስንረባረብ ነበር፡፡ በተለይም የገባነው ከብክነት በፀዳ መልኩ በቴክኖሎጂ ታግዞ ምርት የመሰብሰብ ሥራ መሥራት አለብን የሚል መሠረታዊ አቅጣጫ ይዘን ነው።ሁለተኛው የበጋ መስኖ ልማት ሲሆን፤ እርጥበትን በመጠቀም ያሉንን ማሳዎች በመስኖ ለማልማት ትኩረት አድርገን ተንቀሳቅሰናል፡፡ በዚህም መሠረት 147 ሺ ሄክታር መሬት በማልማት 33 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማምረት ያቀድን ሲሆን፤ ከዚህም ውስጥ ደግሞ 11 ሺ 230 ሄክታር የበጋ መስኖ ስንዴ በማልማት 434 ሺ ኩንታል ምርት ለማግኘት ጥረት ስናደርግ ቆይተናል፡፡

ሌላው ጉዳይ የሌማት ቱሩፋት መርሃ-ግብር ሲሆን፤ ይህም ለአፍታም ቢሆን ምንም ዓይነት መቀዛቀዝና መፋዘዝ ሳይኖር ለማስቀጠለ ጥረት አድርገናል፡፡ በተለይ ሽግግር ላይ ብዙ ውስብሰብ ነገሮች የሚያጋጥሙ በመሆናቸው ንቅናቄያችን የነበረውን ግለት ጠብቆ እንዲሄድ አቅጣጫ አስቀምጠናል፡፡ በተጨማሪም የአረንጓዴ ዐሻራ ልማት መርሃ-ግብርንም በስፋት የማስቀጠል ትልም ይዘን የተንቀሳቀስን ሲሆን፤ በዋናነት 393 ሚሊዮን ችግኝ ለማባዛት ግብ አስቀምጠን እየሠራን እንገኛለን፡፡ እንዲሁም የተከልናቸውን መንከባከብና የማፅደቅ ሥራ ጎን ለጎን እየተከናወነ ነው፡፡

ከዚህ ባሻገርም ቡና እና ቅመማ ቅመም ልማት ላይ አተኩሮ መሥራት አለብን ብለን አስቀምጠናል፡፡ ሰባተኛው የህብረት ሥራ ልማትና የግብይትና የፋይናንስ ሥራ ነው፡፡ በተለይ ህብረት ሥራ በግብዓት አቅርቦቱ፤ በምርት ግብይት አምራቹን አርሶአደር ካላስፈላጊ የገበያ ሰንሰለትና ደላላ በመከላከል አምራቹ ከሸማቹ ጋር በቀጥታ እንዲገናኝ መሥራት እንዳለብን ተማምነናል፡፡ የገባነው በከተሞች አካባቢ የሚታየውን ተገቢ ያልሆነ የገበያ ውድነትንም ለመከላከል የህብረት ሥራ ማህበራት በዚህ የግብይት ሥርዓት ውስጥ ተዋናይ የሚሆኑበትን ሁኔታ መፍጠር አለብን ብለን ነው ፡፡

እነዚህን ሰባት ጉዳዮች ይዘን ገብተን፤ ባለፈው ዓመት የመኸር ምርት አሰባሰብ በሰብል ከተሸፈነ 532 ሺህ ሄክታር መሬት የጠበቅነው 47 ነጥብ 1 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ነበር ፡፡ ይህንን ምርት ከብክነት በፀዳ ፣ ጥራቱን ጠብቆ በገበያ ተወዳዳሪ በሚሆን መንገድ ምርቱ መሰብሰብ እንዳለበት መግባባት ላይ ደርሰናል። አንዳንድ ጊዜ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊያጋጥም ስለሚችል በክልል ደረጃ ያለው ንቅናቄ እስከታች እንዲወርድና ሁሉንም ባለቤት ባደረገ መልኩ እንዲተገበር ተደርጓል፡፡ በተለይ ምርት አሰባሰብ ላይ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ የጤና ባለሙያዎች፣ አርቲስቶች በዚህ ጉዳይ ላይ ባለቤት እንዲሆኑ ህብረተሰቡን የማንቃት ሥራ ተሰርቷል፡፡

በተለይም ቆላማው የክልላችን አካባቢ ምርት ቀድሞ የሚደርስ በመሆኑና ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የሚመጣ በመሆኑ ምርት የሰበሰብነው በቶሎ ነው፡፡ ያም በመሆኑ እንደ አጋጣሚ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝንብ ቢከሰትም በአጠቃላይ በነበረው ንቅናቄ ከፍተኛ መናሳሳት ተፈጥሮ ምርት ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ ከኦሮሚያ ክልል ከ650 በላይ ኮምባይነሮች በኪራይ በማምጣት ምርቱን በመሰብሰባችንና አጠቃላይ ሥራችንን በሜካናይዜሽን የተመራ በማድረጋችን ብክነት ማስቀረት ችለናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በበጋ መስኖ ልማትና በሌማት ትሩፋቱ የተገኘው ስኬት እንዴት ይገለፃል?**

**አቶ ሑስማን፡-** በክልላችን በበጋ መስኖ ልማት ሥራ ውጤታማ ሰፋፊ ሥራዎችን አከናውነናል፡፡ በተለይም ክልላችን ከሌሎች ክልሎች አንፃር በቆዳ ስፋትም ከእርሻ መሬት አኳያ አነስተኛ እንደመሆኑ ይህንን ውስን መሬት በአግባቡ ተጠቅሞ ፈጣን ልማት ከማምጣት አኳያ የተሠሩት ሥራዎች የሚያበረታቱ ናቸው። ክልሉ ምንም እንኳን ሰፋፊ የውሃ አካላት ባይኖሩትም ያሉትን የውሃ አማራጮችን ሁሉ ተጠቅሞ ዓመቱን ሙሉ ማምረት የሚያስችሉ የመስኖ ልማቶችን አከናውኗል፡፡ እስካሁን ባለው ተሞክሮ ግን አብዛኛው የክልሉ መሬት እየለማ የነበረው ዝናብን በመጠበቅና በአርሶ አደሩ ብቻ ነበር፡፡ በመሆኑም ይህንን ጠንካራና ሥራ ወዳድ ሕዝብ ተጠቅመን ወደ ከፍተኛ እሴት ወይም ገበያ መር የሆኑ ሰብሎችን ለማምረት ተንቀሳቅሰናል። በተለይም ለኑሮ ውድነት መቃለል እና የሥራ እድል ለመፍጠር ትልቅ አስተዋፅኦ ያላቸውን ሰብሎች ላይ አተኩረን ስንሠራ ቆይተናል፡፡

በዚህም መሠረት አትክልትና ፍራፍሬ ምርት ላይ ትኩረት አድርገን ሰርተናል፡፡ ከዚህ ቀደም በክልላችን አርሶ አደሮች ሲመረቱ ከቆዩ የሰብል ዓይነቶች በተጨማሪ ያልተለመዱትንም እንደ ኩከበር፣ ዝኩኒ፣ አበባ ጎመንና መሰል አትክልቶችን ለማልማት አቅደን ከ110 ሺ ሄክታር መሬት በአትክልትና ስራስራ ምርቶች መሸፈን ችለናል፡፡ እስካሁን ባለው መረጃ ከ80 ሺ ሄክታር በላይ ምርት ተሰብስቧል፡፡ በዚህም ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል ተፈጥሯል፡፡ በተለይ ሥራ አጥ የነበሩና ተመርቀው የተቀመጡ ወጣቶች የዚህ እድል ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ የግል ባለሀብቱም መነሳሳት ተፈጥሮለታል፡፡

በሌላ በኩል ምርታማነትን ማጎልበት በመቻሉ በክልላችን ይታይ የነበረውን የግብርና ምርቶች ዋጋ ንረት በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማረጋጋት ተችሏል፡፡ ለአብነት ከቅርብ ጊዜ በፊት ሽንኩርት በኪሎ እስከ 180 ብር ይሸጥ ነበር፤ ቲማቲም 100 ብር ደርሶ ነበር፡፡ አሁን ግን ቲማቲም እስከ 15 ብር ሽንኩርት እስከ 60 ብር ድረስ እየተሸጠ ነው። ይህም ከአካባቢው አልፎ ለሀገር ውስጥ ገበያ መረጋጋት የበኩሉን ሚና ለመጫወት አስችሏል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ሥራውን ስንሠራ ደግሞ በተቀናጀ፣ በተናበበ መልኩ በመሆኑ፤ እስከ ታች ያለው አካል የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት በማበጀታችን የሚታይ ውጤት መጥቷል፡፡

በሌማት ቱሩፋት መርሃ ግብሩ ተጨባጭ ውጤት በመምጣቱ፣ ህብረተሰቡም ጥቅሙን ማጣጣም በመቻሉ ሌሎችም ወደ ግብርና ሥራ እንዲገቡ ከፍተኛ መነቃቃት ተፈጥሯል፡፡ በተለይ ደግሞ በዶሮ፣ በንብ፣ በወተት ልማት ሥራ ላይ በርካታ የክልላችን ነዋሪዎች የመሰማራት ፍላጎት እያደረባቸው ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ያለፈውን ሰባት ወር ተሞክሮ ብናይ፤ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች የዶሮ ልማት ሥራ ለመግባት ጥያቄ አቅርበው ከ4 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ የአንድ ቀን ጫጩትና የ45 ቀን ቄብ ተሠራጭቷል። ይሄ ከዚህ ቀደም ታይቶ አይታወቅም፤ አሁን ላይ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# «ግብርናችን በጥሩ የእድገት...

ከገጽ 9 የዞረ



ፍላጎቱም ሆነ አቅርቦቱ ጨምሯል፡፡ በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች ወጣቶች በኢንተርፕራይዝ ደረጃ ተደራጅተው የዶሮ ጫጩት የማስፈልፈልና የማቅረብ ሥራ እየሠሩ ነው፡፡ ይህም ከዚህ ቀደም በክልሉ የነበረውን የዶሮና የእንቁላል እጥረት በመፍታት ረገድ አወንታዊ ሚና እየተጫወተ ነው፡፡

ኢንሼቲፎቻችን የየራሳቸው ስያሜ አላቸው፡፡ ለምሳሌ ዶሮ ልማትን 5-10-25 የሚባል ኢኒሼቲፍ አለ፡፡ በዚያ መሠረት ለአንድ ቤተሰብ ቢያንስ አምስት ዶሮ እንዲኖር በማድረግ በሶስት ዓመት ውስጥ ከ25 ያላነሱ ዶሮዎች ባለቤት እንዲሆን ታልሞ ተሰርቷል፡፡ ይህም ልማቱ አካታች እንዲሆን ምክንያት ሆኗል፡፡ እያንዳንዱ አርሶ አደር ከሚያረባው ዶሮ የሚያገኘውን እንቁላል በመሸጥ ፍየል ወይም በግ ይገዛል፤ በመቀጠልም ጊደር በመግዛት ኢኮኖሚውን በከፍተኛ ፍጥነት እያሳደገ ነው፡፡ በመሆኑም እኛ የዶሮ እርባታን የምናየው እንደ ኢኮኖሚ ሽግግር ማምጫ መሳሪያ ነው፡፡

በሌማት ቱሩፋት መርሃ ግብር እያከናወናቸው ካሉ ሥራዎች ውስጥ ሌላው የንብ ማነብ ሥራ ሲሆን፤ በዚህም በተደረገው ሰፊ ንቅናቄ አሁን ላይ በክልላችን በርካታ የንብ መንደሮች አሉን፡፡ በዋናነትም አንድ ቤተሰብ ቢያንስ ሶስት ዘመናዊ፤ ሰባት ባህላዊ ቀፎ እንዲኖረው ሲሰራ ቆይቷል። በዚህም የተቀናጀ ግብርና ሥራ አርሶ አደሩ ማር እያመረተ በመሸጥ ሌሎች ተጨማሪ ቀፎች የሚጨምርበትን ሽግግር እያደረገ ይገኛል። ይህም ሲባል የንብ መንደሮችን የምንፈጥረው ዝም ብሎ በምናብ ወይም እንዲሁ ለማለት ያህል አይደለም፤ ይልቁኑ በተጨባጭ መሬት ላይ እየተተገበረ ያለ የልማት ሥራ ነው፡፡ ለዚህም አካታች የሆነ የልማት አቅጣጫ በመከተላችን የሚታይ ውጤት ማምጣት ችለናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ክልሉ '30-40-30' በማለት እየተገበረ ባለው ኢኒሼቲፍ ምን ያህል የአርሶ አደሩን ሕይወት መለወጥ ተችሏል?**

**አቶ ኡስማን፡-** እንደተነሳው የአረንጓዴ ዐሻራ አካል የሆነውና 30-40-30 ኢኒሼቲፋችን በዋናነት የተቀረፀው የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥና ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ነው። ይህም ማለት አንድ ቤተሰብ በሶስት ዓመት 100 የፍራፍሬ ዛፍ ይኖረዋል፡፡ ለክልላችን አግሮኢኮሎጂ የሚስማሙ የፍራፍሬ ዓይነቶችን ለይተናል፡፡ በዚህም መሠረት አፕል፣ አቮካዶ፣ ማንጎ፣ ሙዝና ፓፓያን ለይተናል፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ ግን ማንጎ እንደ ሀገር በሽታ ስለተስፋፋ ለጊዜው አቁመነዋል፡፡ ደጋው ላይ አፕልና አቮካዶ፤ በወይና ደጋውና በቆላው አካባቢ ሙዝ በስፋት እያመረትን ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ቤተሰብ በሶስት ዓመት ውስጥ 100 የፍራፍሬ ችግኝ እንዲኖረው እየተደረገ ነው፡፡

ተቋማት ደግሞ ከ100 እስከ 10 ሺ የፍራፍሬ ዛፍ በሶስት ዓመት እንዲኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ተቋም ሲባልም የማህበረሰብም ሆነ የመንግሥትንም ያካትታል። አብዛኞቹ የማህበረሰብ ተቋማት የምንላቸው የእምነት ተቋማት ሰፊ ጊቢ ይዘው የሚደጎሙት በሕዝብ ነው። ከዘላቂ ማረፊያዎች ውጭ ያሉ የእምነት ተቋማት ቦታዎች ላይ እያንዳንዳቸው 10 ሺ የፍራፍሬ ችግኝ ቢተከሉ የምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ ባለፈ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ አቮካዶ ከ25 እስከ 30 ሺ ብር ያወጣል። 10 ሺ የፍራፍሬ ዛፍ ብንተክል ከአስር ዓመት በኋላ አንዷ ዛፍ በትንሹ 25 ሺ ብር ታወጣለች፡፡ ይህም ማለት እያንዳንዱ ተቋም ከፍራፍሬ ልማት ብቻ 250 ሚሊዮን ያገኛል፡፡ በመሆኑም ሁሉም ቤተእምነት ባሉት ቦታዎች እስከ 10 የሚደርሱ ፍራፍሬዎችን ቢተክል ምዕመናን የሚደግፍ እንጂ ከምዕመናን የሚለምን ሊሆን አይችልም፡፡ ተቋማቱ ከተረጂነት ወደረጂነት ይለወጣሉ፤ ይህ ብቻ ሳይሆን የምግብና ሥርዓት ችግርን ይፈታሉ፤ የሥራ እድል ይፈጥራሉ፤ ምግብ ያቀርባሉ፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓት ያቀርባሉ፤ ለውጭ ንግድ ያቀርባሉ፡፡

ይህ መርሃ-ግብር ከመጀመሩ በፊት አንዳንዶች 'አይሳካም' የሚል ጥርጣሬ ነበራቸው፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ እኛ ባለፈው ዓመት ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ላይ 10 ሺ አቮካዶ በአንድ ቀን ተክለናል፡፡ በኋላ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አምስት ሺ ጨምሮ በአንድ ካምፓስ 15 ሺ አቮካዶ ተተክሏል፤ አሁን ላይ ሁሉም ፀድቋል፡፡ ስለዚህ ሁሉም የትምህርት ተቋሞቻችን በትንሹ ሶስት ሺ ችግኝ ቢተክሉ የመንግሥት ድጎማ አይጠብቁም፡፡ ራሳቸው መንግሥትንም ሆነ ሀገርን የሚደጉሙ ይሆናሉ። ይሄ ዝም ብሎ ያልተገባ ምኞት ወይም ቀቢፀ ተስፋ ሳይሆን ምህራኑን አማክረን በጋራ ባጠናነው ጥናት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

የንብ ቀፎቹም የሚኖሩት ዛፎቹ ላይ ነው፤ ዶሮና ከብቱም በአንድ በተወሰነ ቦታ ላይ የሚሰራ በመሆኑ በትንሽ መሬት ላይ ከፍተኛ ሀብት መፍጠር ይቻላል። ይህንንም ከንባታ ላይም ሌሎች የክልሉ አካባቢዎች ተግብረነው በተጨባጭ ውጤት ያመጣንበት ነው፡፡ ከዚህ ቀደም በማምረት ሳይሆን በመረዳት የሚታወቁ፤ የአደጋ ስጋት የነበሩ አካባቢዎች ዛሬ ወደ ሀብት ፈጣሪነት ተቀይረዋል፡፡ ብልፅግና 'ከእዳ ወደ ምንዳ' እንደሚለው ትናንት እዳ የነበሩ ዛሬ ላይ ወደ ምንዳ ተቀይረዋል፡፡

ከተስፋ መቁረጥ ወደሚጨበጥ ተስፋ ተቀይረዋል። ለአብነት ሲምቢጣን ማንሳት እንችላለን፡፡ የሃላባም ሆነ የስልጤ ሲምቢጣ የተባሉ ሁለት ቀበሌዎች በታሪክ የሚታወቁት በጎርፍ ነው፡፡ በሁለቱም ቀበሌዎች ዝናብ ከመጣ ክልልም ሆነ ፌዴራል ያለ አካል ርዳታ ለማቅረብ፤ ድንኳን ለማድረስ ፤ ለተፈናቀሉ ሰዎች ምግብ ለማቅረብ ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ አሁን ላይ ያ የጎርፍ አደጋ ታሪክ ሆኖ ቀርቷል። በዚህ መርሃ-ግብር አማካኝነት በተፈጠረው መነቃቃት ህብረተሰቡ ባዶ መሬቶችን በማልማትና ሙዝ በመትከል አሁን የፍራፍሬና የአትክልት ቀጠና እስከመሆን ደርሷል፡፡ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ድህነት ጨርቁን ጥሎ ከአካባቢው እየጠፋ ነው፡፡ በመሆኑም የ30-40-30 ኢኒሼቲቭ ብዙ ያላየናቸው እድሎችን እንድናይ ፤ ግብርናችን ወደ ውጤት እንዲሄድ አድርጎልናል፡፡

ሌላ ምሳሌ ልጥቀስ፤ በዚህ መርሃ ግብር አማካኝነት ወደ ልማት ከገቡት ደግሞ የቀድሞ ታሪካቸው ድህነትና ችግር ከሆነባቸው አካባቢዎች መካከል ሻሸጎ ዶኦሻ ጎላ ቀበሌ ስትሆን ፤ ይህች ቀበሌ ቀድማ ድህነትን በማሸነፍ ለሌሎች የክልሉ አካባቢዎች ተምሳሌት ሆናለች። የሚገርመው በአካባቢው የመስኖ አውታር ከተገነባ 15 ዓመት ቢሆነውም፤ ሕዝቡ ግን ግንዛቤ ስላልተፈጠረለትና መስኖውን ተጥቅሞ ስለማያለማ በችግር ውስጥ ለዓመታት ኖሮዋል፡፡ የፍራፍሬ ልማት መርሃ ግብሩ ከተጀመረ ወዲህ ወደ ሀብት ፈጠራ ተሸጋግረዋል። አሁን ላይ ከሰፋፊ የሙዝ መንደሮች ባሻገር በቆሎና መሰል አዝዕርቶች በስፋት እየተመረቱ ነው፡፡ እንግዲህ አስቀድሜ እንደገለፅኩት መሬቱም፤ ውሃውም፤ ሰውም ነበር፤ ሆኖም ሃሳብ ስላልነበርና አቅጣጫ የሚያሳይና ምቹ መደላደል የሚፈጥርለት ባለመኖሩ በድህነት ውስጥ ነበር፡፡ አሁን ሃሳቡ ወደ ተግባር ተቀይሮ ዜጎች ከድህነት መውጣት እና የሥራ እድል መፍጠር ጀምረዋል፡፡ እንደ አጠቃላይ በእኛ ግምገማ ግብርናችን በጥሩ የእድገት ጉዞ ላይ ነው፡፡

ሌላው ከአረንጓዴ ዐሻራ ጋር ተያይዞ ሀገራችን ያላትን ብዙ ፀጋዎች ትርጉም ሳትሰጥ በስህተት መንገድ ላይ ቆይታለች፡፡ እኛ ደግሞ ከክልላችን አንፃር የተለየ ባህሪ ያለው እንሰት እየጠፋ አደጋ ላይ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም እንሰትን ከመጥፋት ወደ ማስፋፋት መሄድ አለብን የሚል ንቅናቄ አካሂደን እንሰት የቀጣዩ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ የሥነ-ምግብ ተስፋ እንዲሆን አቅደን ተንቀሳቅሰናል፡፡ በዚህም የሚታይ ለውጥ አምጥተናል፡፡ በዋናነትም ልማቱን የማስፋፋት ፣ ድህረ ምርት የማቀነባበር ሥራ በመሥራት የሚያስወጣውን ጉልበት የመቀነስና ቴክኖሎጂን መጠቀም እንዲሁም በሽታን ለመቀነስ የጀመርነው ሥራ አለ፡፡

ስለዚህ እንሰት ለሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ለኤክስፖርት በሚሆን መንገድ ወደ ዱቄት ቀይረን የምንልክበትን ሁኔታ መፍጠር አለብን ብለን እየሠራን ነው፡፡ በዚህ ዓመት ወደ 84 ሚሊዮን የእንሰት ችግኝ እናቀርባለን ብለን 87 ሚሊዮን ተክለናል፡፡ ዋና ትኩረት አድርገን እየሠራን ያለነው በቆላማ አካባቢ ነው፡፡ መታወቅ ያለበት፤ ከእንሰት ምርት የሚጣል አንድም ነገር የለም፡፡ እንሰት ለሰው ምግብ ነው፤ ለእንስሳት መኖ ነው፤ ለአፈር ማዳበሪያ ይሆናል፡፡ ከምግብነት አንፃር ጤፍ፣ ሩዝ፣ ገብስም ሆነ ሌላ ሰብል በተጋገረ በሶስተኛው ቀን ይሻግታል፤ ከእንሰት የሚዘጋጀው ቆጮ ተጋግሮ ከአንድ ወር በላይ ይቆያል፡፡ ይሄ ወደፊት ምርምርም የሚደረግበት ነው፡፡ በሚቀጥለው ዓመት 1 ነጥብ 8 ሚሊዮን ለመትከል አቅደን እየሠራን ነው፡፡

ዘንድሮ ለየት የሚያደርገው እንሰት ብዙ በማይታወቅባቸው እንደ ሃላባ ባሉ አካባቢዎች እየለማ መሆኑ ነው፡፡ ንቅናቄያችን በጥቅሉ እንደዚህ ዓይነት የተለዩ ነገሮችን ማምጣት አስችሏል፡፡ አሁን የተገኙት ውጤቶች በሙሉ የአዲሱ እሳቤ ቱሩፋቶች ናቸው፡፡ አዲሱ እሳቤ ፀጋን መለየት፣ የለየነውን ፀጋ ማልማት፣ በመጨረሻም ከፀጋችን በመጠቀም ከድህነት ማምለጥ ነው፡፡ ክልላችን እንደ ተቋቋመ ከድህነት የተሻገረ ህብረተሰብ እንፈጥራለን ብለን ነው የተነሳነው፤ መሻገር ዝም ብሎ በህልም አይሆንም፤ በእያንዳንዱ ቦታ አካባቢውን የሚመስሉ እቅዶች ተዘጋጅተው ወደ ተግባር ገብተናል፡፡ ስለዚህ እስከ አሁን የመጣንባቸው መንገዶች በበጋ መስኖም፣ በሌማት ቱሩፋቱም ሆነ በአረንጓዴ ዐሻራም የሚታዩ ተጨባጭ ለውጦች ተገኝተዋል። በተለይም በሌማት ቱሩፋት ማዕድን ከማትረፍረፍ ባለፈ በአካባቢው ልማት ለበርካታ ወጣቶች የሥራ እድል ተፈጥሯል፤ በዚህ ልማት የተሳተፉ አርሶ አደሮች በተለይም ሴቶች ገቢያቸውን ማሳደግ ችለዋል፡፡ የግል ባለሀብቱም በዚህ ሥራ ላይ ለመሰማራት መነሳሳት ተፈጥሮለታል፤ የቴክኖሎጂ ሽግግር እየመጣ ነው፡፡ አጠቃላይ ዘርፉ ለዜጎች የገቢና የኑሮ ለውጥ ትልቅ እድል መሆኑን በተግባር ማየት ተጀምሯል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ክልሉ ከዚህ ቀደም ባልተለመደ ሁኔታ በቅመማ ቅመም ዘርፍም ለሀገር ከፍተኛ ገቢ እያስገኘ ስለመሆኑ ይጠቀሳል፤ ስለዚህ ሁኔታ ቢያብራሩልኝ?**

**አቶ ኡስማን፡-** ልክ ነው፤ እንደተባለውም ቀደም ሲል ቡና እና ቅመማ ቅመም በዚህ ክልል እብዛም አይታወቅም ነበር፡፡ ነገር ግን ባለፉት ሁለት ዓመታት የቡና መሬትን ሽፋን የማስፋፋት እና ምርታማነቱን የማሳደግ ሥራ እየተሠራ ነው። በዚህ ዓመት ወደ 52 ሚሊዮን ችግኝ እያባዛን ነው፤ ከዚህ ውስጥ 44 ሚሊዮኑ በዚህ ዓመት የሚተከል ነው፡፡ 10 ሚሊዮኑ ከሚያዝያ ጀምሮ እየተተከለ ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን በማድረግ አሁን ወደ 146 ሺ ሄክታር ደርሰናል፤ ይህንን ወደ 165 ሺ ሄክታር ለማድረስ እየሠራን ነው፡፡

ሌላው ቅመማ ቅመም ነው፤ ምቹ የአየር ንብረት በመጠቀም ዝንጅብል፣ ኮሰረት፣ ድንብላልና ሮዝመሪ ወደ ማምረት ገብተናል፡፡ በተለይ ሮዝመሪ ላይ ከፍ ባለመንገድ እየሄድን ነው፤ ሮዝመሪን ለውጭ ገበያ በስፋት ለማቅረብ ጥረት እያደረግን ነው፡፡ በዚህ መነሻ ዘንድሮ

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# ወቅታዊ

## «ግብርናችን በጥሩ የእድገት...



**ይሁንና የኑሮ ውድነቱ ሰው ሠራሽ ነው፤ ምርት እያለ የገበያ ሰንሰለቱ በመራዘሙ ምክንያት የማይገባቸው አካላት በገበያ ውስጥ ገብተው በሚጫወቱት ሕገወጥ ሚና የምርት ዋጋ እየናረ ነበር፡፡ በመሆኑም ህብረት ሥራ ማህበራት በክልል ባሉ ትላልቅ ከተሞች የሰንበት ገበያ፣ የሐሙስ፣ የማክሰኞ ገበያ ወዘተ እያልን በማቋቋም በሳምንት ሁለትና ሶስት ቀን ማህበራቱ ምርቶቻቸውን እያቀረቡ ለአካባቢው ዋጋ መረጋጋት ትልቅ ሚና እየተጫወቱ ነው**

ከገጽ 10 የዞረ

ከስልጤ ዞን ብቻ ባለፉት ዘጠኝ ወራት 22 ሺ 760 ኩንታል ሮዝመሪ ወደ ተለያዩ የዓለም ሀገራት ልከን 4 ነጥብ 1 ሚሊዮን ዶላር ማስገባት ችለናል፡፡ አሁን ይህንን ሮዝመሪ ወደ ጉራጌ ፣ ሃድያ፣ ከንባታ ፤ ወደ ሃላባም የማስፋፋት ሥራ እየሠራን ነው፡፡

ሮዝመሪ ድርቅን እና አሲዳማ አፈርን ይቋቋማል፤ እንዲሁም ደረቃማ በሆነ መሬት ላይ ምርት ይሰጣል።በእነዚህ መነሻዎች ካለፈው ዓመት ጀምረን ሮዝመሪን በተለየ መንገድ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ነው፡፡ በርበሬ ደግሞ እሴት ጨምረን የመላክ ሥራ ጀምረናል፤ 13 ሺ 780 ኩንታል በመላክ 6 ነጥብ 1ሚሊዮን ዶላር ማግኘት ችለናል፡፡ ሮዝመሪን በ2014 ዓ.ም ወደ ገበያ ያስገባነው ቢሆንም፤ ባለፈው ዓመት 2 ነጥብ 8 ሚሊዮን ዶላር ማግኘት ችለናል፡፡ ይሁንና በአካባቢው ሮዝመሪ ከዚህ በፊት የሚታወቀው ለመጥበሻነት እንጂ ዶላር ማምጫነት አይደለም፤ አሁን ሮዝመሪ ከመጥበሻ ወጥታ ወደ ዶላር ማምጫና ሥራ እድል መፍጠሪያ የሀገር ሀብት ምንጭ ሆናለች።

የእኛ ሮዝመሪ አሁን ላይ አውሮፓ ገበያ ገብቶ ግሎባል ካፕ ሰርተፍኬት አግኝቷል፡፡ ሶስት ሺ አርሶ አደሮች ግሎባል ካፕ ሰርተፍኬት እንዲያገኙ አድርጓል። ይህንን ሰርተፍኬት ማግኘታቸው ፕሪሚየም ፕራይዝ እንዲያገኙና አስተማማኝ ገበያ እንዲኖር ያስችላል። ስለዚህ የእኛ ሥራ ጥራቱን ጠብቆ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት ማምረትና ማስፋፋት ነው። መጀመሪያ የነበረው አንድ ቀበሌ ላይ ነው። አሁን በሰልጤ ወረዳዎች ሁሉ የማስፋፋት ሥራ ተሠርቷል። በትምህርት ቤቶች፣ በጤና እና በእምነት ተቋማት የመትከል ሥራ እየተሠራ ነው፡፡ ጉራጌ ላይ ወደ 2 ሺ ሄክታር አካባቢ ደርሷል፡፡ ወደ ሌሎችም የክልሉ አካባቢዎች የማድረስ ሥራ እየተሠራ ነው፡፡ በመሆኑም ሮዝመሪ ለክልላችን በአዲስ እይታ የመጣ አዲስ ምርት ነው፡፡ በቀጣይ ሌሎችንም ቅመማ ቅመሞችንን ለማዕዛማ ዘይት የሚውሉና በትንሽ መሬት ሀብት የሚመነጭባቸውን እየለየን ነው፡፡

ቡናው ላይ የጀመርነው ሥራ በተለይ ባለፉት ወራት አራቱም ዞኖች የየአካባቢያቸውን ስያሜ እንዲያገኙ አድርገናል፡፡ በቀጣይም የማስተዋወቅ ሥራ እንሠራለን፡፡ የአካባቢው ቡና በጣዕም የተለየ ስለሆነ ወደ ውጭ ገበያ እንዲገቡ ከዞኑ ጋር በመተባበር እየተሠራ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በክልሉ የህብረት ሥራ ተቋማት የዋጋ ንረትን ከመከላከል አኳያ ምን ያህል ተጨባጭ ሥራ እየሠሩ ነው?**

**አቶ ሑስማን፡-** ከህብረት ሥራ አንፃር በዚህ ዓመት እንደ ሀገርም እንደ ክልልም ሰፊ የኑሮ ውድነት አጋጥሞ ነበር፡፡ ይሁንና የኑሮ ውድነቱ ሰው ሠራሽ ነው፤ ምርት እያለ የገበያ ሰንሰለቱ በመራዘሙ ምክንያት የማይገባቸው አካላት በገበያ ውስጥ ገብተው በሚጫወቱት ሕገወጥ ሚና የምርት ዋጋ እየናረ ነበር፡፡ በመሆኑም ህብረት ሥራ ማህበራት በክልል ባሉ ትላልቅ ከተሞች የሰንበት ገበያ፣ የሐሙስ፣ የማክሰኞ ገበያ ወዘተ እያልን በማቋቋም በሳምንት ሁለትና ሶስት ቀን ማህበራቱ ምርቶቻቸውን እያቀረቡ ለአካባቢው ዋጋ መረጋጋት ትልቅ ሚና እየተጫወቱ ነው፡፡ ስለዚህ የህብረት ሥራ ማህበራቱ የግብርና ምርቶችን ዋጋ ለማረጋጋት ሸማቹ ህብረተሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ ምርት በማቅረብ ረገድ ሰፊ ሥራዎች ተሰርተዋል።የእኛ ግምገማ እንደሚያሳየው በዚህ ተጨባጭ ውጤቶች መጥተዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በክልሉ ከ30 ዓመታት በፊት ተተክለው የነበሩ ባህር ዛፎችን በሙዝ የመተካቱ ሥራ ምን ያህል ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ይኖረዋል ?**

**አቶ ሑስማን፡-** እንደተነሳው በክልላችን ባህር ዛፍን በፍራፍሬ የመተካት ሥራ በስፋት እየተሠራ ነው፡፡ ይህ ባህር ዛፍ ለኢኮኖሚው እዚህ ግባ የማይባል አበርክቶ ስላለው ብቻ ሳይሆን፤ በሥነ-ምህዳሩ ላይ እያደረሰ የነበረው አሉታዊ ተፅዕኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ያደረሰውን ለአብነት መጥቀስ ካስፈለገ ስልጤ ዞን ላይ የሚገኘው ስልጢ ሃይቅ ተጠቃሽ ነው። ስልጢ ሃይቅ ከሶስት ዓመት በፊት ዙሪያው በባህር ዛፍ የተሸፈነ ነበር፡፡ ሃይቁ በባህር ዛፉ ምክንያት ውሃው እየቀነሰ፤ በዙሪያወም የነበረ የተፈጥሮ ሀብት እየጠፋ ነበር። ሆኖም ባለፉት ሁለት ዓመታት በተሠራው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራና ሰፊ ንቅንቄ 25 ሄክታር ተነቅሎ፤ ሙዝ እንዲተከል ተደርጓል፡፡ እዚህ ላይ ሙዙ ዝም ብሎ የተተከለ አይደለም፡፡ ያመጣው ኢኒሼቲፉ ነው፤ በዙሪያው የሚኖሩ አርሶ አደሮችን የማሳመን ሥራ ተሠርቷል፤ አርባ ምንጭ ሙዝ አምራች አርሶ አደሮች ጋር ተሞክሮ ወስደዋል፡፡

ከኢኮኖሚ ፋይዳ አኳያ በአንድ ስኩዌር ሜትር መሬት ከሁለት ባህር ዛፍ በላይ አይተከልም፤ ከዚህም ቢሆን ገቢ ለማግኘት እስከ ሰባት ዓመት ይወስዳል፡፡ ሲሸጥም አራት መቶ ብር በላይ አይሆንም፡፡ ግን በአንድ ስኩዌር መሬት ላይ አንድ ሙዝ ቢተክል በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ከእናት ሙዙ ውጭ ከ10 እስከ 15 የሙዝ ችግኝ (ሰከር) ማውጣት ይቻላል። ከዚህ ውስጥ ደግሞ ስምንቱን ብቻ ነቅሎ ቢሸጥ 240 ብር ይገኛል፡፡ በድምሩ በችግኝ ብቻ አምስት መቶ ብር ማግኘት ይቻላል፡፡ በመሆኑም መጀመሪያ የሠራነው ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ነው፤ በኋላ ተሞክሮ ወስዶ ወዲያው ወደ ተግባር እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ አሁን ላይ ከሰልጤ ባሻገር ከንባታና አላባ እንዲሁም በሌሎቹ የክልሉ አካባቢዎች ባህር ዛፍ እየተነቀለ ሙዝ የመትከል ሥራ በስፋት እየተሠራ ነው፡፡

ባህር ዛፍ ተዘርዝሮ የማልቁ የሥነ ምህዳር ጉዳቶችን ያደርሳል፤ አንደኛው ውሃ የሚባል አይኖርም፡፡ ወንዝ፣ ሃይቅና ጅረትንም ጭምር የማድረቅ አቅም አለው፡፡ በሌላ በኩል ባህር ዛፍ ባለበት አካባቢ ማንኛውም ሌላ አዝርዕትም ሆነ ተክል አይበቅልም፡፡ ደግሞም ባህር ዛፍ በበቀለባቸው መሬቶች የአፈር ተፈጥሯዊ አወቃቀር ሳይቀር ይቀየራል፡፡ ከሁሉ የባሳው ደግሞ በባህር ዛፍ የተጎዳ አፈርን ወደ ተፈጥሯዊ ይዘቱ ለመቀየር ጊዜ ይፈልጋል። በጥቅሉ ባህር ዛፍ ትጋት የሚፈጥር ሳይሆን ትጋት አምካኝ ነው፡፡ ከገቢ አንፃርም አንዴ ተተክሎ የሚደርስ ከሰባት ዓመት በኋላ ነው፤ በመሆኑ ሕዝቡ ቁጭ እንዲል እንጂ እንዲሠራ አያበረታታም፡፡ አካባቢም ያመክናል፡፡ የአፈር ለምነት የሚባል ነገር አይታሰብም፡፡

የአረንጓዴ ዐሻራ ሥራችን፤ የጠቅላይ ሚኒስትራችን ኢኒሼቲቮች ደግሞ ዘላቂ የሕዝቦችን ጥቅም የሚያረጋግጡ ናቸው። የበለፀገች ሀገር ለመገንባት፣ የዛሬውን ትውልድ እየጠቀመ፣ ለነገው ትውልድ ቅርስ ማኖር ነው፡፡ ያ ከሆነ ሐይቆቻችንም መጠበቅ አለባቸው፤ ወንዞቻችን መልማት አለባቸው፣ ምንጮቻችንም ይበልጥ መጎልበት አለባቸው። ባህር ዛፍ ግን ይህንን እያመከነ ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን ለማስተካከል እየሠራን ነው። በአጠቃላይ በክልላችን የተቀናጀ ግብርና ልማት ሥራችን በውጤታማ ጉዞ ላይ እንደሆነ ገምግመናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በክልሉ እንደ በቆሎ ያሉ ሰብሎች ምርጥ ዘር ፤ እንዲሁም እንደትራክተርና የውሃ መሳቢያ ፓምፖች ያሉ መሳሪያዎች እጥረት እንዳለ በመስክ ምልከታችን ተመልክተናል፡፡ የክልሉ መንግሥት ይህንን ችግር ከመፍታት አንፃር ምን እያከናወነ ነው?**

**አቶ ሑስማን፡-** ሁልጊዜም ቢሆን ልማት ሲመጣ አዳዲስ ፍላጎቶችን ይፈጥራሉ፤ ተፈጥሯዊ ነው፤ ወደ ሃላባ ስትሄዱ ሲምቢጣ የሚባለው አካባቢ ሙሉ ለሙሉ የሚታወቀው በጎርፍ ነው፡፡ መኪና መንገድ ቢፈለግ እንኳን ድንኳን ለማስጋባት ወይም የተፈናቀሉ ዜጎችን ለማውጣት ካልሆነ በስተቀር ሌላ አጀንዳ አልነበረም፡፡ አሁን ላይ ያ አካባቢ በመልማቱ ምርት ለማውጣት የመንገድ ጥያቄ አለ፡፡ እዛ ብቻ አይደለም ሌሎች ቦታዎች ላይ ልማቱ ሲመጣ ልማቱ የወለደው ጥያቄ አለ፤ እሱን መመለስ የግድ ይላል፡፡ እኛ አልምተን፤ መናሳሳት ከፈጠርን በኋላ ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ መስጠት የመንግሥት ግዴታ ነው፡፡

ልማት የወለዳቸው ጥያቄዎች ችግር የማይሆንበት ምክንያት ለምሳሌ ሃላባም ሆነ ሌሎች አካባቢዎች ላይ ፓምፕ እያቀረበ ያለው መንግሥት ነው፡፡ ቀድመው የቀረቡት በነዳጅ የሚሰሩ ነበሩ፤ አሁን ላይ ደግሞ ለአገልግሎት እየዋሉ ያሉት በፀሐይ ኃይል የሚሰሩ ናቸው። በዋጋ እነዚህኞቹ ቀነስ ስለሚሉ፤ ቤኒዚኑንም ሆነ ናፍጣውን ማግኘት እንዲሁም ማጓጓዝም ፈታኝ በመሆኑ አሁን ላይ የሚነሳው ጥያቄ በፀሐይ የሚሰሩ በርከት ብለው ይግቡ የሚል ነው፡፡

በመሠረቱ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማስተዋወቅ ሲባል መንግሥት በተወሰነ ደረጃ ገዝቶ ሊሰጥ ይችላል፤ ሆኖም ገዝቶ የመጠቀም ኃላፊነት የአርሶ አደሩ ነው፡፡ በፀሐይ የሚሰሩትን ፓምፖች ያስገባንባቸው እንደ ሲምቢጣ፣ ላንፎሮ፣ ሳንኩራ ፣ ማረቆና መስቃን አካባቢዎች ላይ ተጨማሪ የይምጣልን ጥያቄ ይነሳል፡፡ የሚመጣው ከውጭ ነው፤ ዝም ብሎ በአጭር ጊዜ የሚሆን አይደለም፤ ግን ደግሞ እየሠራን ነው። በተለይ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማግኘት በግብርና ሚኒስቴርም ጥያቄውን

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

## «ግብርናችን በጥሩ የእድገት...

ከገጽ 11 የዞረ



**ትክክለኛ አልሚው የትኛው እንደሆነ የሚለየው እድል ተሰጥቶ ነው እንጂ እንዲሁ መፈረጅ አይቻልም፡፡ የብድሩ መጠን ይደግ መባሉ ጤናማ ነው፡፡ ነገር ግን የሥራ አጥ ቁጥር ብዙ ነው፡፡ ያለው ሀብት ደግሞ ትንሽ ነው፡፡ በመሆኑም ማጣጣም ያስፈልጋል**

አቅርበናል። እዚህ ላይ ሶላር ፓምፑን ማስመጣት ከጀመርን ገና ሁለት ዓመት አልሞላውም፤ ነገር ግን ፍላጎቱ በአንድ ጊዜ ጨመረ፡፡ ይህ በእኛ እይታ ጥሩ ነው፡፡ በተለይ ከበቆሎ ምርጥ ዘር አኳያ የተነሳው ጥያቄ አጠቃላይ የበቆሎ ዘር እጥረት ኖሮ ሳይሆን ከተለመደው ዝርያ ለመውጣት ካለመሻት የመነጨ ነው፡፡

ፓዮነር የተባለ የበቆሎ ዝርያ እጥረት አለ። የሚባዛው ወለጋና ጎጃም እንዲሁም ጉራጌ ዞን አበሽጌ ላይ ነው፡፡ የሚሰራጨውም ለመላው ሀገሪቱ ነው፡፡ ፍላጎቱ ከፍ ስላለ ለሁሉም ማድረስ አይቻልም፡፡ ግን ፓዮነር የተባለው ዝርያ የሚሰጠውን ያህል ምርት የሚሰጡ ምርጥ ዝርያዎች አሉ፡፡ በመሆኑም ታች ያለው የእኛ መዋቅር ቢሆን አንዱ የገባውን ምርት ዘር ከማየት ይልቅ ሌሎች አማራጮችን ያለ ማየት ችግር አለ። ደግሞም በቆሎ ብቻ መዝራትም ላያስፈልግ ይችላል፤ ሌሎች ሰብሎችን እንደ አማራጭ መጠቀም ይገባል። ድንችም፤ ሽንኩርትም መትከል ይቻላል፡፡ እንደየአካባቢው ሥነ ምህዳር፤ አየር ንብረትና ወቅት እያዩ አዋጭ የሆነውን ምርት ማምረት ይቻላል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሌላ ምሳሌ ላንሳ ዘንድሮ የበጋ ስንዴ አምና ካመረትነው አንፃር በጣም ቀንሰናል፡፡ በዚያ ምትክ የተቀረውን መሬት በአትክልት በመሸፈን አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆን አድርገናል፡፡ በበልግም በቆሎ ማሽላና ዘንጋዳ በተለምዶ ይመረትባቸው የነበሩ አካባቢዎች አትክልት እያለማን ነው። በዚህም ብዙዎች ላይ መነሳሳት ተፈጥሯል። አንዳንዶች ጋር የጎመን ክላስተር፣ የቲማቲም ክላስተር ተፈጥሮ እያለማ ነው፡፡ ምክንያቱም ደግሞ አዋጭ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሄክታር በቆሎ ዘርተን የቱንም ያህል ብንከባከበው ከ80 ኩንታል በላይ በሄክታር ማግኘት አይቻልም፡፡ ድንች ተክለን ከ350 እስከ 450 ኩንታል ማግኘት እንችላለን፡፡ ይህም ከበቆሎው ጋር ፈፅሞ ሊነፃፀር የሚችል አይደለም፡፡ በምርት መጠንም ሆነ በዋጋ የሚገኝ አይደለም፡፡

**አዲስ ዘመን:- በመስክ ጉብኝታችን የወተት ምርት በብዛት እየተመረተ ቢሆንም የገበያ ትስስር ባለመፈጠሩ አምራቾች ይበሳሸብናል የሚል ስጋት አለባቸው፤ ከመሠረተ ልማት ማሟላት ጋርም አትክልት፣ ፍራፍሬና ሰብሉች የሚፈለግበት ቦታ ሳይደርስ እንደሚበላሽ ተመልክተናል። ከዚህ አኳያ ክልሉ ምን እየሠራ ነው?**

**አቶ ኡስማን:-** ገበያ ትስስሩ ላይ የተሠራው ምርቱን ማትረፍረፍ ነው፡፡ በዛው ላይ የገበያ ትስስሩን በተለያየ መንገድ ማጠናከር ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡ በመጀመሪያ የፈጠርነው የወተት መንደሮች ነው፡፡ አምራቾቹ ወደ ህብረት ሥራ ማህበራት እንዲቀየሩ በመቀጠል ተደራጅተው በአነስተኛ ደረጃ እያመረቱ ያሉትን ከሀገር ውስጥ ገበያ ጋር የማስተሳሰር፤ በመቀጠልም አነስተኛ የማቀነባበሪያ ኢንደስትሪዎች ውስጥ እንዲገቡ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው፡፡ ለምሳሌ ከምባታ በቅርቡ ይጀመራል፡፡ በመቀጠል ቡታጅራ፣ ወልቂጤ፣ ወራቤ፣ ሀላባ እያልን እንቀጥላለን። እንደ እኔ እምነት የማስቀመጥና የማጓጓዝ ጉዳይ ችግር አይሆንም፡፡ እርጎውም፣ ቅቤውም፣ ክሬሙም አንዱ ጋር ሲከማች ሌላ ቦታ ሄዶ ይሸጣል፡፡ መጀመሪያ ግን የተሠራው የወተት መንደሮችን የመፍጠር ሥራ ነው፡፡ ጎን ለጎን ገበያውን የማመቻቸት ሥራ እየተሠራ ነው፡፡

የመንገድ ጉዳይ የብላቴ እና ሌሎችም ልማቱ እስካለ ድረስ መንገዱ በተለያየ መንገድ ይሠራል፡፡ በሕዝብ ተሳትፎ የሚሠራ፣ በወረዳ አቅም፣ በዞንና በክልል ደረጃ በዩራፕ ፕሮግራም የሚሠራ እና በክልል አቅም ከዞኖች ጋር በመቀናጀት ይሠራል። ይህም ቅደም ተከተል ወጥቶለት ይሠራል፡፡ ከክልል አቅም በታች የሆነ ጥያቄ ዋናው ልማቱ እስካለ ድረስ የክልል መንግሥት ኃላፊነቱን ወስዶ ይሠራበታል፡፡

**አዲስ ዘመን:- በስልጤ ዞን ሲምቢጣ በተባለው አካባቢ ለዓመታት ጥቅም ሲሰጥ የቆየ የመስኖ ግድብ በመሰበሩ ምክንያት ሙዝ አምራች ገበሬዎች በከፍተኛ ችግር ውስጥ መሆናቸውን አይተናል፡፡ የክልሉ መንግሥት ይህንን ችግር ያውቀዋል? ካወቀ ችግሩን ለመፍታት ምን እየሠራ ነው?**

**አቶ ኡስማን:-** በነገራችን ላይ ይህ የብላቴን ወንዝ በመጥለፍ ለልማት የተሠራው ግድብ ከተገነባ 15 ዓመት አልፎታል፡፡ ሆኖም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ጥቅሙን ተገንዝቦ ልማት ላይ ያዋለው አልነበረም፡፡ ሆኖም ከሁለት ዓመት ወዲህ በተደረገው የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ወንዙ በሚያዋስናቸው ስልጤ ፤ ሃላባና ሃድያ እንዲሁም ጉራጌ ዞኖች ላይ መስኖው በተለይም ለሙዝ አምራቾች ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል። እንዳልኩት ይህ ወንዝ ለዓመታት እንዲሁ ሲፈስ ኖሮ የበጋ መስኖ ማምረት ከተጀመረ በኋላ የላይኛው አምራቾች በተለይ ጉመር ላይ ሲያመርቱ ውሃው እያነሰ መጣ፡፡ በዚሁ ውሃ ምክንያት ሃላባ አንዳንድ ቀበሌዎች አምና እንዳላመረቱ መረጃ አለኝ፡፡

የክልሉ መንግሥት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት እየተካሄደ ይገኛል። የውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር ተደራጅቶ በትብብር እየተሠራ ነው፡፡ ችግሩ ተለይቷል ለመፍትሔው እየተሠራ ነው፡፡ ግድቡ ላይ የደረሰውን ጉዳት በሚመለከት በጎርፍ ጉዳት ደርሶበታል፡፡ ሥራውን ለማከናወን ሀብት እየተፈለገ ይገኛል፤ የክልሉ ውሃ አስተዳደር ኤጀንሲ ይሠራዋል። በሽግግር ላይ ያለ ክልል እንደመሆኑ ጊዜ የሚፈልጉ ሥራዎች አሉ፡፡

**አዲስ ዘመን:- በክልሉ ከአነስተኛና ጥቃቅን ተነስተው ወደ መካከለኛ ኢንተር ፕራይዝነት መሸጋገር ለሚፈልጉ ወጣቶች እየቀረበ ያለው የብድር አቅርቦት አነስተኛ መሆኑን ሰምተናል። ችግሩን ለመፍታት ምን እየሠራችሁ ነው ? ለጀማሪዎች በፋይናስ ተቋማት የተቀመጠው መስፈርትስ ተገቢ ነው ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ኡስማን:-** የብድር አቅርቦቱን በሚመለከት የቸሃ ወጣቶች ለሌሎች ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ጥሩ ሞዴል የሚሆኑ ናቸው፡፡ ከ28 ሺ ብር ተነስተው አሁን በርካታ ሚሊዮን ብር ላይ ደርሰዋል፡፡ ከአንድ ሄክታር ተነስተው ዛሬ 30 ሄክታር አካባቢ አልምተዋል፡፡ ይሄ ደግሞ ብዙ ሀብት እየፈጠረ ነው፡፡ ለእርሱ ሀብት መፍጠር ብቻ ሳይሆን አምስት ሆነው በርካታ የሥራ እድል ፈጥረዋል፡፡ ይሄ ሽግግር ነው፡፡ መጀመሪያ ትናንሽ ኢንተርፕራይዝ ነበሩ፣ ወደ መለስተኛ ከሄዱ በኋላ ወደ ኢንቨስተር ሲሸጋገሩ ከልማት ባንክ ጋር ይተሳሰራሉ፡፡ ችግሩ በዚህ ይፈታል፡፡ እንደተነሳው ከክልሉ ኢንደስትሪና የኢንቨስትመንት ቢሮ ጋር ባደረግናው የመስክ ምልከታ ችግሩን አይተናል፤ ብዙም ባረዘመ ጊዜ ችግሩ መልስ ይሰጠዋል፡፡

መስፈርትን በሚመለከት የሚሠራው የክልሉ ሥራ እድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ነው። ሀገራዊ መስፈርት ተደራጅቷል። በእነርሱም በኩል እርሾ ያስፈልጋል፤ እርሾና መንግስት የሚያቀርበው መመጣጠን አለበት። ማየት ያለብን ያደጉ ሀገራትን አይደለም፡፡ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ሀብት በየቦታው ባክኗል፡፡ ትክክለኛ አልሚው የትኛው እንደሆነ የሚለየው እድል ተሰጥቶ ነው እንጂ እንዲሁ መፈረጅ አይቻልም፡፡ የብድሩ መጠን ይደግ መባሉ ጤናማ ነው፡፡ ነገር ግን የሥራ አጥ ቁጥር ብዙ ነው፡፡ ያለው ሀብት ደግሞ ትንሽ ነው፡፡ በመሆኑም ማጣጣም ያስፈልጋል፡፡ የተሳሳተ አስተሳሰብ በመያዝ ገንዘብ ተበድረው ያልተቀየሩ ብዙዎች አሉ፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ተበድረው ሰርተው የተለወጡ፤ ለሌሎችም የሥራ ዕድል የፈጠሩም አሉ፡፡ በመሆኑም ሁሉንም በሚዛኑ ማየት ተገቢ ነው ባይ ነኝ፡፡

**አዲስ ዘመን:- ምስራቅ ጉራጌ ዞን መስቃን አካባቢ የግሪሳ ወፍ ወረርሽን መከሰቱን አይተናል። ይህንን በመከላከል ረገድ ምን እየተሠራ ነው?**

**አቶ ኡስማን:-** እንደተባለው በመስቃን የተወሰነ አካባቢ ላይ በጣም ጥቂት በሚባል ደረጃ የግሪሳ ወፍ ሥርጭት ታይቷል፡፡ ሆኖም በወረርሽኝ ደረጃ የሚነሳ አይደለም፡፡ ግን ደግሞ ጥቂት ቢሆን ምላሽ መስጠት ስላለበት ከግብርና ሚኒስቴር ጋር እየተነጋገርን እንገኛለን። በሄሊኮፍተር ኬሚካል ርጭት መፍትሔ ለማምጣት እየተሠራ ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን ሄሊኮፍተሮቹ የሚመጡት ከአጎራባች ክልሎች እየተነሱ በመሆኑና ርቀት ያለው በመሆኑ የሚፈለገው ያህል ውጤት በፍጥነት ማምጣት ከባድ ነው፡፡ በመሆኑም በቅርብ ርቀት ማረፊያ ሥፍራ ለማዘጋጀት ከግብርና ሚኒስቴር ጋር እየተነጋገርን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን:- ስለጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**አቶ ኡስማን:-** እኔም ስለክልሉ የልማት ሥራ እንዳብራራ እድሉን ስለሰጣችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ ለዩክሬን የ61 ቢሊዮን ዶላር ወታደራዊ ድጋፍ አፀደቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



የአሜሪካ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከወራት ክርክር በኋላ ለዩክሬን በርካታ ቢሊዮን ዶላሮች ወታደራዊ እርዳታ ለማድረግ ውሳኔ አሳልፏል።

በኮንግረሱ ብዙ ተቃውሞ ገጥሞት የነበረው ይህ የ61 ቢሊዮን ዶላር ወታደራዊ ድጋፍ ዩክሬን ራሷን ከሩሲያ ወረራ ለመመከት ያግዛታል ተብሏል።

አሁን ድጋፉ ‘መቼ’ ነው ለዩክሬን የሚደርሰው የሚለው ጥያቄ መነጋገሪያ ሆኗል። ምናልባትም በቀናት ውስጥ እርዳታው ለዩክሬን መድረስ እንደሚጀምር መላ ምቶች አሉ።

የሩሲያ ጥቃትን ለመከላከል እጅግ ወሳኝ ለሆነው ወታደራዊ ድጋፍ ምስጋናቸውን የገለጡት የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ዜሌንስኪ፤ “ዴሞክራሲ እና ነፃነት ሁሌም ዓለም አቀፍ ጠቀሜታ አላቸው፤ አሜሪካ ድጋፍ ማድረግ ከቀጠለች ደግሞ መቼም ቢሆን አይከስምም” ብለዋል።

አክለው ድጋፉ ጦርነቱ እንዳይስፋፋ ከማድረጉም በላይ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ሕይወት ይታደጋል ሲሉ ተደምጠዋል።

የክሬምሊን ቃል አቀባይ ድሚትሪ ፔስኮቭ በበኩላቸው እርዳታው “አሜሪካን የበለጠ ሀብታም ያደርጋታል፤ ዩክሬንን ደግሞ የበለጠ ያላሽቃታል አልፎም ለበርካታ ዩክሬናውያን ሞት ምክንያት ይሆናል” ብለዋል።

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በአውሮፓውያኑ የካቲት 2022 ነው ሁሉን አቀፍ ጦርነት ዩክሬን ላይ ያወጁት። በጦርነቱ ከሁለቱም ወገኖች በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች እና ሠላማዊ ዜጎች ሲገደሉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዩክሬናውያን ደግሞ ተሰደዋል።

ያለፈው ቅዳሜ ዕለት የፀደቀው እርዳታ ከዩክሬን ባለፈ 26 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ለእስራኤል፤ 9 ነጥብ 1 ቢሊዮን ዶላር ለጋዛ ሰብዓዊ እርዳታ፤ 8 ነጥብ 1 ቢሊዮን ዶላር ደግሞ ራሳቸውን “ከኮሚዩኒስት ቻይና እንዲጠብቁ” እንደ ታይዋን ላሉ የእስያ ፓሲፊክ ግዛቶች እና ሀገራት ተሰጥቷል።

ምክር ቤቱ ከገንዘብ እርዳታው ባለፈ የቲክ ቶክ ባለቤት የሆነው የቻይናው ኩባንያ ማኅበራዊ ሚዲያውን እንዲሸጥ አሊያም እንዲታገድ የሚለውን ረቂቅ አፅድቋል።

አዋጁ በ311 ድጋፍ እና በ112 ተቃውሞ ሲፀድቅ ምክር ቤቱ በጭብጨባ የቀለጠ ሲሆን አንዳንድ ተወካዮች የዩክሬንን ባንዲራ ሲያውለበልቡ ታይተዋል።

አዋጁ ቀጥሎ ወደ ሴኔት የሚሄድ ሲሆን ሴኔቱ በጥቂት ቀናት ውስጥ ያፀድቀዋል ተብሎ ይጠበቃል። ቀጥሎ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ይፈርሙበታል።

ፕሬዚዳንት ባይደን የምክር ቤቱን ውሳኔ አወድሰው “ፈርማዬን በፍጥነት አኑሬ ሕግ ከሆነ በኋላ የጦር መሣሪያ እና ሌሎች ቁሳቁሶች ወደ ዩክሬን መላክ አለብን” በማለት ሴኔቱም በፍጥነት እንዲያፀድቀው ጠይቀዋል።

የኔቶ ዋና ፀሐፊ ጄንስ ስቶልተንበርግ ይህ እርዳታ ከአውሮፓ አጋሮች እየተደረገ ያለውን ድጋፍ ያጠናክረዋል ብለዋል።

የአውሮፓ ኅብረት ኃላፊዎች በጋራ ባወጡት መግለጫ ደግሞ “ዩክሬን ራሷን ከሩሲያ ለመጠበቅ የሚደርግላት ሁሉ እርዳታ ይገባታል” ሲሉ ተደምጠዋል።

የዩክሬን የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ኃላፊ አሌክሳንደር ሜሬዥኮ ውሳኔውን “ታሪካዊ” ካሉት በኋላ “በእርግጠኝነት የሠላማዊ ዜጎችና ወታደሮችን ሕይወት ይታደጋል” ሲሉ ለቢቢሲ ተናግረዋል።

በምዕራባውያን እርዳታ ላይ ጥገኛ የሆነችው ዩክሬን በተለይ በቅርብ ሳምንታት እየገፋ ከመጣው የሩሲያ ጦር ራሷን ለመከላከል ከውጭ የሚመጣ እርዳታ ትሻለች።

የጦር መሣሪያ እጥረት የገጠማቸው የዩክሬን ወታደሮች በጦርነት ቀለህና ቁሳቁስ እየቆጠቡ እየተጠቀሙ እንደሆነ ተዘግቧል።

ዜሌንስኪ እና የሲአይኤ ኃላፊ ዊሊያም በርንስ ዩክሬን ከአሜሪካ እርዳታ ካልደረሳት በቀር ጦርነቱን መሸነፏ የማይቀር ነው ብለው ነበር።

ባለፉት ስድስት ወራት ሩሲያ በርካታ ግዛቶችን በቁጥጥሯ ሥር ያዋለች ሲሆን ሌሎች ምዕራባውያን የዩክሬን አጋሮች ከአሜሪካ የሚመጣው እርዳታ በመጓተቱ ተፈትነው ነበር።

ምንም እንኳ እርዳታው ዩክሬን ጦርነቱ እንድትረታ ያግዛል ተብሎ ባይጠበቅም ለመዋጋትና ምናልባትም ድርድር ለማድረግ የሚሆን ኃይል እንዲኖራት ያግዛል ተብሏል።

እርዳታው በምክር ቤቱ የተጓተተው አንዳንድ ሪፐብሊካን ፖለቲከኞች ገንዘቡን ለዩክሬን ከምናውለው ይልቅ በአሜሪካ-ሜክሲኮ ላለው የስደተኞች ፍልሰት ልናውለው ይገባል ብለው በመቃወማቸው ነው።

በሚቀጥለው ምርጫ ሪፐብሊካኖች ድምፅ አግኝተው ኮንግረስ መግባት የሚችሉ ከሆነ ለዩክሬን የሚደረገው ድጋፍ ሊቋረጥ ይችላል የሚል ስጋት አለ።

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

## “ፓርታሉ“- ለትምህርት ዘርፉ እድገት ያለው ፋይዳ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ትምህርት ሚኒስቴር በአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት በአጠቃላይና ከፍተኛ ትምህርት ዘርፎች ተዋቅሮ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት የሚሠራ ተቋም ነው። በዚህ አደረጃጀት መሠረት በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ከ50 ሺህ በላይ የሚሆኑ የቅድመ አንደኛ፣ የአንደኛ ደረጃ፣ የመካከለኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ 47 ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን፣ የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን እና የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎትን የያዘ ነው።

የአጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ሕጎችንና ፕሮግራሞችን መቅረጽ፤ የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ ማዘጋጀት፤ የትምህርት እና የትምህርት ተቋማትን ስታንዳርድ ማውጣት፤ ሀገራዊ የብቃት ማዕቀፍ ማዘጋጀትና በሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፤ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውን መተግበር፤ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ማዘጋጀትና ጥራቱን ማረጋገጥ፤ የፈፃሚ አካላትን አቅም መገንባት፣ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በአዋጅ ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶቹ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ሚኒስቴር መሥሪያቤቱ ተግባራቶቹን ወደ ማኅበረሰቡ ለማውረድ ከዘረጋቸው ዘዴዎች መካከል የትምህርት ቤት ማሻሻያ ፖርታል አንዱ ነው። ይህ ፖርታል ዋና መጠሪያው ሲፕ ፖርታል (SIP Portal) በመባል ይታወቃል። የዛሬ ዋና ትኩረታችን ይህንኑ ጉዳይ የሚያብራራ ይሆናል። በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት መረጃ አስተዳደርና አይ.ሲ.ቲ ክፍል ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሰብስቤ ለማ፤ በጉዳዩ ላይ የሰጡንን ሰፋ ያለ ማብራሪያ እንደሚከተለው አሰናድተን ይዘን ቀርበናል።

እንደአቶ ሰብስቤ ማብራሪያ፤ የትምህርት ጥራት መጓደል መንስኤው ዘርፈ ብዙ ነው። ሆኖም የእኛ ክፍል ትኩረቱ ትምህርት ቤቶችን ማሻሻል ላይ ነው። በመሆኑም የትምህርት ቤቶች ያሉበትን ደረጃ ለመመልከት እንገደዳለን። ከዚህ አንጻር በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፉ ብቻ ያሉትን ከ50ሺህ በላይ ትምህርት ቤቶች ያሉበትን ደረጃ ስንመለከት፤ ከ86 በመቶ በላይ የሚሆኑት የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከደረጃ በታች ናቸው። በተመሳሳይ ከ71 በመቶ በላይ የሚሆኑት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ አስፈላጊ መሠረተ ልማቶች እንዳልተሟላላቸው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያወጣቸው መረጃዎች ያሳያሉ።

ትምህርት ቤቶቹ ለመማር ማስተማር ምቹ ያልሆኑና አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ-ልማቶች ያልተሟሉባቸው ከደረጃ በታች በመሆናቸው፤ ተማሪዎች በተጓደለ የትምህርት ከባቢ ውስጥ እንዲማሩ ይገደዳሉ። በዚህም በየደረጃው ያሉ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን እውቀትና ክህሎት እንዳይቀስሙ እንዲሁም የባሕሪ ለውጥ እንዳያመጡ ያደርጋቸዋል። ይህ ችግር ካልተፈታ ሀገሪቱ የምታፈራቸው ተማሪዎች ፍሬያማ አይሆኑም። ስለዚህ ችግሩን የመቅረፍ ሥራ ለነገ የሚባል አይደለም። ይሁን እንጂ ችግሩን በመንግሥት አቅም ብቻ ግን መቅረፍ አይቻልም። መንግሥት ብቻዬን ልወጣው ቢል እንኳን ከሦስት አስርተ ዓመታት በላይ ሊፈጅበት ይችላል። ከዚህ አኳያ መንግሥት አዲስ ስትራቴጂ መቀየስና መምራት ይጠበቅበታል። በዚህም መንግሥት ትምህርት ቤቶችን በዘላቂነት የማሻሻል ተግባርን የማኅበረሰብና የልዩ ልዩ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ድርሻ ለማድረግ መርሐግብር ነድፎ ወደ ሥራ ገብቷል።

መርሐግብሩ «ትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ» የሚሰኝ ሲሆን፤ በየደረጃው ያሉ አመራሮችን፣ የአካባቢው ማኅበረሰብን፣ የቀድሞ ተማሪዎችን፣ ታዋቂ ግለሰቦችን፣ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሚያቅፍ ነው። እነዚህ ባለድርሻ አካላት በትውልድ ቦታቸው፣ በተማሩበት ቦታ፣ በሚሠሩባቸውና በሚኖሩባቸው አካባቢ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች “ምን አይነት ችግር አለባቸው?” የሚለውን ለይተው ችግሩን ለመቅረፍ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ዕድል የሚሰጥ ነው። እነዚህ አካላት የጎደሉ መሠረተ-ልማቶችን ማሻሻል የሚችሉት ደግሞ ነባራዊ ሁኔታውን በደንብ ሲያውቁና ሲረዱ ነው። ያሉ ክፍተቶችን እንዲያውቁና እንዲረዱ የሚያግዝ “የትምህርት ቤት ማሻሻያ ፖርታል” ትምህርት ሚኒስቴር አዘጋጅቷል።

ፖርታሉ ለአጠቃቀም ቀላልና ምቹ ነው። ወደ ፖርታሉ ለመግባት በየትኛም ብሮዘር/ Browser/ መጠቀም የሚቻል ሲሆን፤ «sip.moe.gov.et» ብሎ በመግባት የተለያዩ መረጃዎችን ማግኘት ይቻላል። የመጀመሪያው «Home page» የሚለውን በመጫን፤ ስለፖርታሉ አጠቃላይ ምን ማለት እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ሌላው «Our Progress» የሚለውን በመጫን ደግሞ በጎ ፈቃደኞችና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት አሁናዊ የትምህርት ቤቶችን ሁኔታ ማወቅ ይችላሉ። እንዲሁም ደግሞ አዲስ የኢትዮጵያ የትምህርት ቤት ዲዛይን ምን እንደሚመስል ያስቃኛል። ዲዛይኑ በትምህርት ሚኒስቴር የሚገኙ ሲሆን፤ ትምህርት ቤት ግንባታ ለማከናወን ወይም ፕሮጀክት ቀርጾ ለመያዝ የሚፈልጉ በጎ ፈቃደኞች አዲስ የኢትዮጵያ የትምህርት ቤት ዲዛይን በነፃ ከተቋሙ ማግኘት ይችላሉ።

ከዚህ በተጨማሪ «About The Campaign» የሚለውን በመንካት ስለትምህርት ሚኒስቴር አጠቃላይ መረጃ ማግኘት ይቻላል። «Schools» በሚለው ስር የተቀመጠውን ስንከፍት ደግሞ የምናገኘው አጠቃላይ የትምህርት ቤቶችን ነባራዊ ሁኔታ ነው። ይህም በሃገሪቱ የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን በዋናነት በተለዩ 46 ዝርዝር ነጥቦች ላይ ያሉበትን ደረጃ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። በጥቅሉ ፖርታሉ ሁለት መሠረታዊ ጥቅሞችን ለማንኛውም አካል ይሰጣል። የመጀመሪያው የትኛውንም አካል በየትኛውም ቦታ ሆኖ የተማረበት ትምህርት ቤት፣ ቀድሞ የሠራበትን ወይንም በሚሠሩበት አካባቢ የሚገኝን ትምህርት ቤት አጠቃላይ መረጃ በቀላሉ እንዲያገኙ ይረዳል። ሁለተኛው ደግሞ አጠቃላይ ትምህርት ቤቶች ያሉባቸውን የትምህርት ቤት መሠረተ-ልማትና የትምህርት ግብዓቶችን ክፍተት በመለየት ቀጥታ ከትምህርት ቤቶቹ ኮሚቴዎች ጋር በመገናኘት የሚፈልጉትን ድጋፍ ማድረግ እንዲችሉ ያግዛል።



**አቶ ሰብስቤ ለማ፤**

ከዚህ ባሻገር ፖርታሉ ስለ ትምህርት ቤቶቹ የተለያዩ መረጃዎችን ይሰጣል። የመጀመሪያው አጠቃላይ ሀገራዊ የትምህርት ቤቶችን ጥሬ መረጃ በ« Dashboard National Figure» የሚያሳይ ሲሆን፤ ሌላኛው ስለ ትምህርት ቤቶቹ መሠረተ-ልማት ዝርዝር መረጃ “Facility”፣ የፎቶ መግለጫ “Gallary” እና የትምህርት ቤቶችን ኮሚቴ “committee” የሚያሳይ ጠቅለል ያለ መረጃ ይሰጣል።

በአጠቃላይ ፖርታሉ የትምህርት ቤቶችን ነባራዊ ሁኔታ በመለየት እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ወደ ቦታው መሄድ ሳይጠበቅበት በቀላሉ ባለበት ቦታ እንዲረዳ ስለሚያደርግ ሥራን ያቃላል። ይህም ማኅበረሰቡና ልዩ ልዩ አካላት በሙያቸው፣ በእውቀታቸውና በጉልበታቸው አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ዕድል ስለሚሰጥና የትምህርት ቤት መሠረተ-ልማት ማሻሻል ሥራው ዘላቂነት ያለው የአሠራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ስለሚያግዝ በትምህርት ቤቶች ደረጃ ማሻሻል ላይ በርካታ ውጤቶችን እንደሚያስገኝ አቶ ሰብስቤ ተናግረዋል።

# ፋሽን

## የፊት ቆዳ እንክብካቤ- የገበያው አማራጮች

ሰሚራ በርሀ

የአንድን ሰው ውበት ከሚገልጹ እና ሰዎችም አብዝተው ከሚጨነቁበት ነገር ውስጥ የፊታቸው ቆዳ ነው፡፡ የሰዎች ፊት ጥርት ማለት ያላቸውን ውበት እና ሰላም እንደሚያሳይ ይገለጻል፡፡ ኮሪያውያን በዓለም ላይ ከሚገኙ ሀገራት ከፊት ቆዳ እንክብካቤ ጋር የቆየ ባህል እና ልምድ እንዳላቸው ይገለጻል፡፡

የፊት ቆዳ በየእለቱ ለፀሐይ እና ለንፋስ የተጋለጠ በመሆኑ እንዲሁም በውስጣችን ባሉ የጤና እክሎችም ሆነ በእድሜ ምክንያት በሚመጡ ችግሮች ምክንያት የፊት ቆዳ በቀላሉ ለጉዳት ሊዳረግ ይችላል፡፡ ሰዎችም ፊታቸው ላይ የሚያዩዋቸውን ምልክቶች ለማጥፋት እና ጥርት ያለ የፊት ቆዳን ለመያዝ የተለያዩ ግብዓቶችንና ምርቶችን ይጠቀማሉ፡፡

ውበትን ለመጠበቅ ዘመን አመጣሽ ተጨማሪ መዋቢያ ምርቶችን ከመጠቀም ይልቅ ሰዎች በቻሉት መጠን ያላቸውን ጠብቀውና አጉልተው መቆየት እንደሚችሉ የሥነ-ውበት ባለሙያዎች ቢመክሩም፣ ሰዎች ከዚህ ይልቅ ለተለያዩ ሕክምናዎች ወደ ጤና ተቋማት ይሄዳሉ ወይም የውበት መጠበቂያ ድርጅቶች ሲያመሩ ይስተዋላሉ፡፡

በሀገራችን በስፋት የሚታወቀው የቆዳ ሕክምና ሲሆን፣ ሰዎች ቆዳቸው ላይ የሚመለከቷቸውን ችግሮች ለመታከም የቆዳ ሐኪሞች ወደሚገኙበት የጤና ተቋም ያመራሉ፡፡ ይሁንና ፊትን አልያም ከአንገት በላይ ያለን ቆዳ መንከባከብ የሚያስችል ተቋም ብዙም አልተለመደም፡፡

ዶክተር ሮዚና አረጋዊ በ‹‹ ኤቨር ግሪን ሜዲካል ስፓ›› ውስጥ የፊት እንክብካቤ ባለሙያ (facial treatment specialist) ናት፡፡ ተቋሙ የፊት እንክብካቤ፣ የቆዳ ሕክምና እና የጸጉር ንቅለ ተከላ አገልግሎትን ይሰጣል፡፡ እንደ ዶክተር ሮዚና ገለጻ፤ የቆዳ ሕክምና የሚባለው ከጸጉር ቆዳ እስከ ጥፍር ያለውን የሚያክም ራሱን የቻለ ስፔሻሊስቶች ያሉት ነው፡፡ የፊት እንክብካቤ ደግሞ የፊታችንን የቆዳ ዓይነት፣ የተጎዳበትን ምክንያት ለይቶ በማጥናት በተለያዩ ሳይንሳዊና ተፈጥሯዊ መንገዶች ወደቦታው እንዲመለስ የሚያደርግ አገልግሎት ነው፡፡



ሰዎች እንደሚኖራቸው የቆዳ ዓይነት የሚሰጠው አገልግሎትም ይለያያል፡፡ የፊት ቆዳ እንዲፍታታ ማሳጅ በማድረግ፣ የተለያዩ ግብዓቶችን በመጠቀም ፊት ላይ የወጡ ጠባሳዎች፣ በቡጉር ምክንያት የተፈጠሩ ጥቋቁር ነጠብጣቦች እንዲደበዝዙ ማድረግ፣ በፀሐይ የተጎዳን ፊትና በተለያዩ ምክንያቶች ፊት ላይ ወጥ ያልሆነ ቀለም (ዲስከለሬሽን)፣ ዓይን ስር መጥቆር ሲታዩ እነዚህን በማከም የፊት ትክክለኛ መልክ እንዲወጣና እንዲያበራ የማድረግ ሥራን ይሰራሉ፡፡

‹‹በሀገራችን የፊትን ቆዳ መንከባከብና መጠበቅ በአብዛኛው አልተለመደም›› የምትለው ዶክተር ሮዚና፣ በሌሎች ሀገራት ሰዎች ፊታቸው በፀሐይ እንዳይጎዳ የፀሐይ መከላከያ ቅባቶችን፣ ፊት እንዳይደርቅ የሚያደርጉ ማለስለሻዎችን እና ለፊት ቆዳ ብቻ የተለዩ መታጠቢያዎችን እንደሚጠቀሙ ትገልጻለች፡፡

ዶክተር ሮዚና በዚህ ሥራ ውስጥ ሁለት ዓመት ያህል ጊዜ ቆይታለች፡፡ ‹‹ሥራውን ስንጀምር ሰዎች ብዙም ስለቆዳቸው እውቀት አልነበራቸውም፤ አሁን ብዙ ሰዎች ስለቆዳቸው በማወቅ በተለያየ ጊዜ ወደ እኛ ይመጣሉ›› በማለት ጠቅሳ፣ አንዳንዶች ባለማወቅ ፊታቸው ቀይ እንዲሆን ብቻ በማሰብ ወደ ማእከሉ እንደሚመጡም ትናገራለች፡፡

ዶክተር ሮዚና አሁን ላይ የተለያዩ የውበት መጠበቂያዎች እንደሚተዋወቁ ጠቅሳ፣ የፊት ቆዳ ውበት በራስ መተማመንን ያላብሳል የሚሉ ማስታወቂያዎችም በርከት ብለዋል ትላለች፡፡ ሰዎችም የፊት ቆዳቸውን ለመንከባከብና ጥርት ያለ ለማድረግ ከቆዳ መጠበቂያ ምርቶች ባሻገር በቤታቸው ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ግብዓቶችን ቀምመው እንደሚጠቀሙ ትገልፃለች፡፡ ንጥረ ነገሮቹም እርድን ከማር ጋር ፣ የሩዝ ዱቄትና አቮካዶ ከግብዓቶቹ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ግብዓቶች ቆዳን የማለስለስና የማፍካት ባህሪ ስላላቸው እንደሚስማማቸው ለማወቅ ከተጠቀሙ በኋላ የማሳከክ፣ የማቃጠልና በቶሎ የመቆጣት ነገርን ካስተዋሉ ቢተውት ጥሩ ነገር ካገኙበት ደግሞ የመረጡትን ግብዓት በሳምንት አንዴ መጠቀም እንደሚችሉ ትመክራለች፡፡ የፊት ቆዳ እንክብካቤ ለሴቶች ብቻ ሳይሆን ለወንዶችም እንደሚያስፈልግ ያነሳችው ዶክተር ሮዚና፣ ይህን አገልግሎት አሁን አሁን ወንዶችም ፈልገው ወደ ማእከሏ እንደሚመጡ አስታውቃለች፡፡

እንደ ዶክተር ሮዚና ገለጻ፤ የሰዎች የፊት ቆዳ ዓይነት የተለያየ በመሆኑ ለአንደኛው ሰው ቆዳ የሚስማማ ግብዓትም ሆነ የቆዳ መጠበቂያ ምርት ለሁሉም ሰው አይሆንም። ስለሆነም ሰዎች የቆዳቸውን ጤና ለመጠበቅ ሲያስቡ አስቀድመው ምን ዓይነት የፊት ቆዳ እንዳላቸው ቢያውቁ ደህና ነው ስትል እንደባለሙያ ትመክራለች፡፡

እንደ እሷ ማብራሪያ፤ ደረቅ የቆዳ ዓይነት ፣ ወዛም (ቅባታማ) ፣ ደረቅ እና ወዛምን አንድላይ የያዘ የቆዳ ዓይነት እና በቶሎ ሊቆጡ የሚችሉ (sensitive) ዓይነት የምንላቸው የቆዳ ዓይነቶች አሉ፡፡ ሰዎች ፊታቸውን በሳሙና በመታጠብ እና ለ15 ደቂቃ በመጠበቅ የቆዳቸውን ዓይነት ማወቅ ይችላሉ። የቆዳ መጠበቂያ ምርቶችን ሲገዙ ምርቱ የያዘውን ግብዓት እና ለየትኛው የቆዳ ዓይነት እንደሚሆን የተሰጡ መግለጫዎችን በማሰብ መግዛት እንደሚገባቸው ገልጻለች፡፡

እነዚህ ምርቶች እና አገልግሎቶች ቅንጡ ዝርዝር ውስጥ ቢካተቱም፣ ዶክተር ሮዚና ግን ፊታችን ከመጎዳቱ በፊት ለመንከባከብ ስም ያላቸውን ምርቶች ከመግዛት ይልቅ የሚስማማቸውን ምርት ቢገዙ የተሻለ እንደሚሆን ትገልጻለች።

እንደ ዶክተር ሮዚና ማብራሪያ፤ አንድ ደንበኛ የፊት ቆዳው ጉዳይ አሳስቦት ሲመጣ በቅድሚያ ፊቱ ላይ የተመለከተውን ለውጥ የሚጠቀማቸውን ምርቶች እና ምን ዓይነት አገልግሎት እንደሚፈልግ ከባለሙያ ጋር ቆይታ ያደርጋል፤ ከዚያም ስለሚሰጠው አገልግሎት ገለጻ ከተደረገለት በኋላ የቆዳ እንክብካቤ የሚያስፈልገው ከሆነ የፊት አገልግሎት፣ ተከታታይ የቆዳ ሕክምና የሚያስፈልገው ከሆነ ደግሞ ወደ ባለሙያ ይመራል፡፡ የፊት እንክብካቤው የፊት ቆዳን ማጽዳት፣ የተዘጉ ቀዳዳዎች እንዲከፈቱ የሚያደርጉ ግብዓቶችን መጠቀም እና የፊት ቆዳን ዘና እንዲል የሚያደርግ ማሳጅን ያካተተ ሲሆን፣ እነዚህን አገልግሎት ካገኙ በኋላም ማድረግ ያለባቸውን ጥንቃቄና የሚጠቀሟቸውን ምርቶች እንደሚነገሯቸው አብራርታለች።

ለሁሉም የቆዳ ዓይነቶች በአንድ ጊዜ ሕክምና አልያም እንክብካቤ ብቻ መቀየር አልያም ወደቦታቸው እንዲመለሱ ማድረግ ባይቻልም፣ ከአንድ ወር የዘለለ የቆዳ እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸውም ይኖራሉ ትላለች፡፡ አንድ የፊት እንክብካቤ የተደረገለት ደንበኛ ሰውም የፊቱን ውበት የሚያየው ከሁለትና ከሶስት ቀን በኋላ ነው ስትል ታብራራለች፡፡

ሰዎች ለፊታቸው ቆዳ የሚሰጡት ትኩረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን የምታነሳው ዶክተር ሮዚና፣ ሰዎች የሠርጋቸው ወቅት ሲደርስ እና የተለየ ፕሮግራም ሲኖራቸው እንደ ኤቨር ግሪን ወዳሉ የፊት እንክብካቤ መስጫዎች ጎራ እንደሚሉም ነው የገለጸችው፡፡ በዚህ ወቅትም ሰዎች ካለባቸው ፕሮግራም አንድ ሳምንት ቀደም ብለው ቢመጡ አገልግሎቱን ካገኙ በኋላ ፊታቸው ላይ ይበልጥ ለውጥ ያዩበታል ስትል ነው ያስገነዘበችው፡፡

ለፊት ቆዳ ተስማሚ የሆነ የፊት መታጠቢያ፣ ማለስለሻ እና የፀሐይ መከላከያ ቅባቶችን አዘውትረው ቢጠቀሙ የተጎዳ ፊታቸውን ወደነበረበት መመለስም ሆነ ያላቸውን ንጹህ ቆዳ እንዳለ እንዲቆይ ማድረግ እንደሚችሉ ዶክተር ሮዚና አረጋዊ ትመክራለች፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## «አየር በአየር» ሥራ ምንድነው?

ዋሰልኝ አየለ

በሙያው ከአሥርት ዓመታት በላይ ያገለገለ አንድ ጋዜጠኛ በማህበራዊ ገጹ የጻፈውን አንድ ገጠመኝ እና ትዝብት አነበብኩ፡፡ የጋዜጠኛውን ገጠመኝና ትዝብት አጠር አድርጌ ሃሳቡን ብቻ ላስቀምጥ፡፡

ወደ ሀገረ ቻይና ሄዶ በርዕሰ መዲናዋ ቤጂንግ አድሯል፡፡ በኢትዮጵያ ዓውድ ከረፋዱ 4፡00 በሚሆንበት ሰዓት ተነስቶ ከተማዋን ሲያይ ጎዳናዎቿ ፀጥ ረጭ ብለዋል፡፡ ከ20 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ይኖርባታል የምትባለዋ ከተማ እንዴት እንዲህ ትሆናለች? ብሎ ተገርሟል፡፡ ወዲያውም አጠገቡ ያገኘውን ሰው ምክንያቱን ጠየቀ፡፡ የተጠያቂው ምላሽ አጭርና ተጨማሪ ማብራሪያ የማያስፈልገው ነበር፡፡ ‹‹በዚህ ሰዓት ሰው ሥራ ቦታው ላይ እንጂ ጎዳና ላይ ምን ይሠራል?›› የሚል ነበር፡፡

ጋዜጠኛው ይህን ገጠመኙን የጠቀሰው የአዲስ አበባን ሙሉቀን የመጨናነቅ ምክንያት ለመጠየቅ ነበር፡፡

የዚህን ጋዜጠኛ ትዝብት የሚያጠናክር ከሦስት ዓመታት በፊት የሰማሁት አንድ የራሴን ገጠመኝ ልጨምር፡፡ ጉዳዩ የአዲስ አበባን የትራፊክ ሁኔታ የተመለከተ ውይይት ነበር፡፡ በውይይቱ ላይ አንድ ተወያይ ያነሱት ሃሳብ በየአጋጣሚው ትዝ ይለኛል፡፡ የተወያዩ ሃሳብ በአጭሩ የሚከተለው ነበር፡፡

የመንግሥት ሠራተኛ እስከ ጠዋት 2፡30 ድረስ በሥራ ቦታው ላይ ይገኛል፡፡ የግል ተቋማት የሥራ መግቢያ ሰዓትም ከዚሁ ጋር እኩል ነው፡፡ በግል የንግድ ዘርፍ የተሰማሩ ደግሞ ጭራሽ ከዚህ ሰዓት በፊት የሚገቡ ናቸው፡፡ የሚታወቁ የሥራ ዘርፎች ቢበዛ እስከ ጠዋት 3፡00 ድረስ በየሥራ ቦታቸው ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡

ሰውየው ይህን ካብራሩ በኋላ የጠየቁት ጥያቄ ብዙዎችን ‹‹እውነቱን እኮ ነው!›› በሚል ያስገረመ፣ አንዳንዶችንም ፈገግ ያሰኘ ነበር፡፡ ‹‹ታዲያ ከ3፡00 እስከ 11፡00 ድረስ መንገድ ዘግቶ የሚውለው ያ ሁሉ ባለመኪና በምን ሥራ ላይ የተሰማራ ነው?›› ብለው ነበር የጠየቁት፡፡

የምርምር ለብዙዎች መልስ ያልተገኘለት ጥያቄ ነበር፡፡ የሞኝ ጥያቄ ቢመስልም፤ ዳሩ ግን ትልቅ ጥናት የሚጠይቅ ነገር ነው፡፡ ለድሮው ‹‹የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት›› የሚባል ነበር፡፡ አሁን ግን የሥራ መግቢያና መውጫውም ሆነ ከዚያ በኋላና በፊት ያለው ምንም ልዩነት የለውም፡፡ በየትኛውም ቦታ ላይ መንገዶች ይዘጋጋሉ፣ በየትኛውም ካፌና ሬስቶራንት ባዶ ወንበሮች አይኖሩም፡፡ ከረፋድ 3፡00 በኋላ ውድ የሚባሉ መኪኖች ናቸው መንገዱን ዘግተውት የሚውሉት፡፡ በየሆቴሉ እና በየካፌው በር ላይ ውድ መኪኖች ናቸው ተሰግስገው የሚውሉት፡፡ በየመዝናኛ ቦታዎች አካባቢ የእግረኛ መንገድ የሚዘጉ መኪኖች ቁጥር ሥፍር የላቸውም፡፡ እነዚህ ሰዎች በምን የሥራ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ናቸው?

ይህንን ጥያቄ አጠገቤ ለሚገኙ ሰዎች ጠይቄ አውቃለሁ፡፡ የሚሰጠኝ መልስ ግን ተለምዷዊ እና የግምት መልስ ነው፡፡ በርግጥ ይህ ከፍተኛ ጥናት የሚጠይቅ ውስብስብ ጉዳይ እንጂ ዝም ብሎ በግምት የሚገኝ አይደለም፡፡ ብዙ ሰው ሲለው የምሰማው መልስ ግን ‹‹አየር በአየር›› የሚባል ምንነቱን የማላውቀው ሥራ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎችም ‹‹ምንድነው የምትሠራ?›› ሲባሉ ‹‹ዝም ብሎ አየር በአየር ነው›› ሲሉ ይሰማል፡፡ ስለአንዳንድ ሰዎች ሲያወሩም ‹‹እሱ እኮ ዝም ብሎ አየር በአየር ነው የሚሰራ›› ሲባል ይሰማል፡፡

ለመሆኑ ይህ አየር በአየር የሚባል ሥራ ምን ይሆን? ቋሚ ቅጥር ያልሆነ ማለት ይሆን? ቋሚ መገኛ የሌለው ተንቀሳቃሽ ሥራ ማለት ይሆን? የአገልግሎት ዓይነት ይሆን ወይስ የዕቃ (goods) ዓይነት ይሆን?

እዚህ ላይ ከማስተውለው ነገር ተነስቼ ትንንሽ የሽያጭ ዓይነቶችን ልጥስ፡፡ በተቀምጥኩበት ካፌ ወይም ምግብ ቤት የተለያዩ ምርቶችን የሚይዙ ሰዎች ይመጣሉ፡፡ ይህ ራሱን የቻለ ሥራ ነው፤ ይህ ምንነቱ የማይታወቀው ‹‹አየር በአየር›› የሚባለው ሥራ የሚገልጸው አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም ተጨባጭ የሆነ ነገር አለው፡፡ ሲቀጥል እነዚህ ሰዎች በአነስተኛ ንግድ ላይ የተሰማሩ እንጂ በውድ መኪኖች አስፋልትና የእግረኛ መንገድ ዘግተው የሚውሉ አይደሉም፡፡

ሌላው ሊገመት የሚችለው ነገር ድለላ ነው፡፡ ድለላ ደግሞ የራሱ ቢሮና ቦታ ያለው ነው፡፡ በርግጥ ድለላ ዓይነቱ ብዙ ነው፡፡ በተለይም ሕገ ወጥ የድለላ ዓይነቶች ቋሚ ቢሮና ቦታ አይኖራቸውም፤ ሥራቸውም በግልጽ አይነገርም፣ አይታወቅም፡፡ የሚደልሉትም እንደ ቤት እና መኪና ያሉ በግልጽ የሚታወቁ ነገሮችን ሳይሆን ብዙ ነውር የሆኑ ነገሮችን ሁሉ እንደሚሆን በሀሜት ደረጃ ሲወራ እንሰማለን፡፡ ‹‹አየር በአየር›› የሚባለው ሥራ ከዚህ ውስጥ የሚካተት ይሆን?

አንዳንድ ሰዎች አሉ፤ ምን እንደሚሰሩ የት እንደሚሰሩ የማይታወቅ፤ ብቻ ግን በሥራ ሲለፉ ከሚውሉ ሰዎች የተሻለ ኑሮ ሲኖሩ የሚታይ፤ ውድ መኪና ይዘው የሚታይ፤ ‹‹አየር በአየር›› ማለት የሆነ በአስማት የሚገኝ ገንዘብ ማለት ይሆን?

አንዳንድ ወገኖች ምናልባት በውጭ ሀገር ጥሩ ኑሮ ያለው ቤተሰብ ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች ምንም ሥራ ላይሰሩ ይችላሉ፡፡ ከውጭ በሚላክላቸው ገንዘብ ብቻ ሲዝናኑ ሊውሉ ይችላሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት እንደሚኖር ቢታወቅም ቢያንስ ግን ይህ ሁሉ ሰው በዚህ ሁኔታ የሚኖር ሊሆን ይችላል? ጥያቄው ለአንዳንድ የሰዎች የሞኝ ጥያቄ እንደሚመስል አምናለሁ!

ከረፋድ ጀምሮ እስከ ሥራ መውጫ ሰዓት ድረስ ሲርመሰመስ የሚውለው ሁሉ ከሥራ ውጭ ነው ማለት አይደለም፤ ይህን አምናለሁ፡፡ የአንዳንድ ሰዎች ሥራ በባህሪው በዚያን ሰዓት መንቀሳቀስን የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በግል ጉዳዮች ምክንያት በዚያን ሰዓት መንቀሳቀስ የግድ ሊሆን ይችላል፡፡ ዳሩ ግን፤ እነዚህ አጋጣሚዎች ይህን ሁሉ መርመስመስ ይፈጥራሉ?

የመንገዱ ነገር ከመሠረተ ልማት ዕድገት ደረጃችን ጋር የሚያያዝ ስለሆነ በጥቂት መኪኖች ብቻ ይዘጋጋል ብለን እንያዘው፡፡ ዳሩ ግን በነጩ የሥራ ቀን ካፌዎችና ሆቴሎች፣ መዝናኛዎች ከአፍ እስከ ገደፋቸው ሞልተው የሚውሉት ሥራ ጥለው በሚሄዱ ሰዎች ነው? ለሆቴሎችና ካፌዎች ጥሩ የሥራ ሰዓት ነው፤ በረንዳ ላይ ሳይቀር አንድ ጠረጴዛ ላይ አራት አምስት ሆኖ የሚታየው ያ ሁሉ ሰው ግን በምን የሥራ ዘርፍ ላይ የተሰማራ ይሆን? የሚል የጅል ጥያቄ ይመጣብኛል፡፡

የሥራ ዘርፍ ማለት የግድ እኔ የምሠራው፣ ወይም እኔ የማውቃቸው ሰዎች የሚሰሩት ብቻ ማለት እንዳልሆነ አውቃለሁ፡፡ ዳሩ ግን የእረፍት ቀናት ከሆኑት በላይ በሥራ ቀን የምግብና መጠጥ ቤቶች የበለጠ ሞልተው ሲታይ ‹‹በመብላትና መጠጣት ገቢ የሚገኝበት የሥራ ዘርፍ አለ እንዴ?›› የሚል ጥያቄ ያጭራል፡፡ እሁድ ወይም ሌላ ካላንደር በሚዘጋበት ቀን እንዲያውም በተቃራኒው ካፌዎች ሰው የማይበዛባቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ በሥራ ቀን፣ በሥራ ሰዓት የበለጠ የሚሆንበት ምክንያት ምን ይሆን? ‹‹አየር በአየር›› የሚባለው ሥራ በእንዲህ ዓይነት ቦታዎች የሚሰራ ይሆን?

ለመሆኑ ‹‹አየር በአየር›› ሥራ ምንድነው?

# ስፖርት





# የአፍሪካ ዞን 5 የወጣቶች እጅ ኳስ ውድድር በኢትዮጵያ ይካሄዳል

ዓለማየሁ ግዛው

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዞን አምስት (ቀጣና-5) ከ18 ዓመትና ከ20 ዓመት በታች ታዳጊዎችና ወጣት ወንዶች የእጅ ኳስ ውድድርን እንደምታስተናግድ የኢትዮጵያ እጅ ኳስ ፌዴሬሽን አስታውቋል። በውድድሩ የሚያሸንፉ ሀገራት በቀጥታ ለአፍሪካ እጅ ኳስ ሻምፒዮና እንደሚያልፉ ተገልጿል።

ውድድሩን የኢትዮጵያ እጅ ኳስ ፌዴሬሽን ከአፍሪካ እጅ ኳስ ኮንፌዴሬሽንና ዓለም አቀፉ የእጅ ኳስ ፌዴሬሽን ጋር በትብብር እንደሚያዘጋጁት ተነግሯል። ውድድሩ ከግንቦት 4-9/2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ይካሄዳል። ዓለም አቀፉ የእጅ ኳስ ፌዴሬሽን ሻምፒዮናውን በበላይነት በመምራት በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ፣ በአራት ኪሎ ትምህርትና ሥልጠና እና በአዲስ አበባ ትንሿ ስቴድየም ይከናወናል። ውድድሩ ቀጣናዊ እንደመሆኑ ኢትዮጵያ በማዘጋጀቷ ከስፖርታዊ ውድድር ባሻገር ቀጣናዊ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊው ፋይዳው የላቀ እንደሆነ ተመላክቷል።

የውድድሩ መክፈቻና መዝጊያ ሥነ ሥርዓት በዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም ለማካሄድ ከተማ አስተዳደሩን ለማስፈቀድ ጥረት እየተደረገ ነው። አዘጋጇን ሀገር ኢትዮጵያን ጨምሮ አስር የቀጣናው ሀገራት በውድድሩ ይሳተፋሉ። ውድድሩ ባማረና በደመቀ መልኩ ከተከናወነ ለሀገርና ለፌዴሬሽኑ የጎላ አስተዋፅዖ ስለሚያበረክት ሰፊ ቅድመ ዝግጅት እንደሚደረግ ተገልጿል።

የውድድሩ ዓርማ የተዋወቀ ሲሆን "የምሥራቅ አፍሪካን የሕዝብ ለሕዝብ ወዳጅነት እናጠናክራለን" በሚል መሪ ሃሳብ በተቀመጠው መርሐ ግብር ይካሄዳል። የውድድሩ ስያሜ የዓለም አቀፍ እጅ ኳስ ፌዴሬሽን ዋንጫ 2024 (IHF THROPHY 2024 AFRICA ZONE-5) በመባል ይጠራል።

ከውድድሩ ጎን ለጎን የIHF THROPHY የአሠልጣኞች ሥልጠና እና IHF THROPHY የዳኞች ሥልጠና ከዓለም አቀፉ የእጅ ኳስ ፌዴሬሽን በሚመጡ ባለሙያዎች ይሰጣል። ከ 20 ቡድኖች የተወጣጡ 40 አሠልጣኞች የሚሠለጥኑ ሲሆን ኢትዮጵያ አዘጋጅ ሀገር በመሆኗ ተጨማሪ አሠልጣኞችንና ዳኞችን እንድታሰለጥን በር እንደሚከፍት ተገልጿል።




ከግንቦት 4-9 በሚካሄደው ውድድር ኢትዮጵያን የሚወክሉ ስፖርተኞች ተመርጠው ዝግጅት ጀምረዋል፣

ከሁሉም ተወዳዳሪ ሀገሮች በሁለቱ የእድሜ ክልል የሚገኙ ወጣቶችና ታዳጊዎች ውድድራቸውን ለማድረግ ወደ ኢትዮጵያ ይገባሉ። በዚህም መሠረት አንድ ሀገር ሁለት ቡድን ሲኖረው አንድ ቡድን 17 ልዑካኖችን ያቅፋል። በአጠቃላይ ለውድድሩ የሚመጡት 400 የሚደርሱ ልዑካኖች መሆናቸው ተነግሯል። የውድድሩ የበላይ ጠባቂ አምባሳደር መስፍን ቸርነት እንደሆኑም ተጠቁሟል።

በሁለቱም የእድሜ እርከን የሚያሸንፉ ብሔራዊ ቡድኖች ለአፍሪካ ሻምፒዮና በቀጥታ የማለፍ እድል የሚፈጥር ውድድር በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በሁለቱም የእድሜ እርከን ተጫዋቾች መርጦ በመጨረሱ ከሚያዝያ አራት ጀምሮ ሆቴል በመግባት ዝግጅት ይጀምራሉ። የ18 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን በዋና አሠልጣኝ ዋና ኢንስፔክተር ተስፋዬ ሙለታና በምክትል አሠልጣኝ ጃቢር ሽምሱ ይሠለጥናል። የፌዴሬሽኑ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ሰጠኝ አዲስ በቡድን መሪነት ተሰይመዋል።

በዚህም መሠረት ተጠባባቂን ጨምሮ 16 ተጫዋቾች ምርጫ ተደርጓል። የቡድኑ አሠልጣኝ ተስፋዬ ሙለታ ብሔራዊ ቡድኑ ከዚህ በፊት ያለ በቂ ዝግጅት ተሳትፎዎችን በማድረግ ሜዳሊያ ውስጥ መግባቱን ተናግረው፣ አሁን ውድድሩ በኢትዮጵያ በመሆኑ በደንብ ዝግጅት ከተደረገ ለአፍሪካ ዋንጫ የማይታለፍበት ምክንያት እንደማይኖር ተናግሯል።

ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን በአሠልጣኝ ሙሉጌታ ግርማ እና በምክትል አሠልጣኝ አማኑኤል ሥዩም የ16 ተጫዋቾች ምርጫ ተደርጓል። የ18 ዓመት በታች ቡድኑ አብዛኛው ተጫዋቾች የፓስፖርት ሂደት የተጠናቀቀ ሲሆን የ20 ዓመት በታች ሙሉ ለሙሉ ተጠናቋል። የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊው አቶ ሞላ ተፈራ የዚህ ቡድን መሪ ሆነዋል።

አሠልጣኝ ሙሉጌታ ግርማ ሥራው ከተሰጣቸው ግዜ ጀምሮ ቅደመ ዝግጅት ማድረጋቸውን ተናግረው፣ በእጅ ኳስ አስር ክለቦች በመኖራቸው ሰፊ የመምረጥ ዕድልን ተጠቅመው ከሁሉም ክለብ ተጫዋቾች ተመርጠዋል። ኢትዮጵያ በ2006 ውድድሩን አዘጋጅታ አሸንፋ የነበር ሲሆን አሁንም ጥሩ ዝግጅት በማድረግ ታሪክ መሥራት እንደሚፈልግ ጠቁሟል። በዚም መሠረት ፌዴሬሽኑ በጊዜ ወደ ሆቴል አስገብቶ ጥሩ ዝግጅት ከተደረገ፣ ሚዲያው የሚያበረታታ ከሆነ፣ የተጫዋቾቹ መነሳሳት እና የተፎካካሪ ሀገራት አቋም ከታወቀ ድል የማይመጣበት ሁኔታ እንደማይኖር ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ እጅ ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ዶክተር ፍትሕ ወልደሰንበት ኢትዮጵያ የዞኑን ፌዴሬሽን በኃላፊነት መምራቷ ውድድሩ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ ዕድል ሊፈጥር ችሏል። ከውድድሩ ጎን ለጎን የአሠልጣኞችና የዳኞች ሥልጠና ይሰጣል። ይህም ለኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ዕድሉን ተጠቅሞ እራሳቸውን ለማሻሻል ይጠቅማል። ለውድድሩ ልዑካን ጥሩ የሆነ አቀባበልንና ዝግጅት በማድረግ ኢትዮጵያ ሌሎች ውድድሮችን እንድታዘጋጅ ለማመቻቸት ይሠራል።

የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ውድድሩ የተሳካ እንዲሆን አስፈላጊውን የማዘወተርያ ስፍራዎች ዝግጅት እና የበጀት ድጋፎች እንደሚያደርግ አስታውቋል። ለዚህም መንግሥት አስፈላጊውን ሁሉ ቅድመ ዝግጅት አድርጓል። ለብሔራዊ ቡድኑ ዝግጅት ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ ሲሆን በቂ ዝግጅት አድርጎ ለውጤት እንዲበቃ ይሠራልም ተብሏል።


## ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ

**የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ከዚህ በታች በተጠቀሱት ክፍት የሥራ መደቦች ላይ ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡**

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ደረጃ | ደመወዝ | የቅጥር ሁኔታ | ብዛት | ተፈላጊ ችሎታዎች | | የሥራ ልምድ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የትምህርት ደረጃ | የትምህርት ዓይነት | |
| 1 | የሕግ ባለሙያ IV | XIV | 9,056.00 | ኮንትራት | 1 | የመጀመሪያ ዲግሪ | ኮምፓራቲቭ ፐብሊክ ሎው፣ ኢንተርናሽናል ሎው፣ ሌጋል ሰርቪስ፣ ሌጋል ሰርቪስ ማኔጅመንት፣ ሌጋል ሰርቪስ ኦፕሬሽን፣ ሌጋል ስተድስ፣ ሎዎር ጀነሪክ፣ ፐብሊክ ሎው፣ ኮንሰንትሬሽናል እና ፐብሊክ ሎው፣ ኮምፓራቲቭ ፐብሊክ ሎው እና ጉድ ገቨርናንስ፣ ሎው እና ሎው ሳይንስ፣ ሕግ | 6 ዓመት |
| 2 | የሕፃናት ድጋፍና እንክብካቤ ሠራተኛ | VII | 3,333.00 | ኮንትራት | 4 | 10ኛ ክፍል | ቀለም እና ስልጠናውን የወሰዱ | 0 |

### ማሳሰቢያ

1. አመልካቾች ለማመልከት ሲመጡ ማንነታቸውን የሚገልጽ መታወቂያ እንዲሁም የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃዎችን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ ከአንድ ጉርድ ፎቶግራፍ ጋር በማያያዝ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
2. አመልካቾች በምዝገባ ወቅት የሚያመለክቱበትን የሥራ መደብ መጠሪያውን፣ ደረጃውንና ደመወዝ በሚሞሉት ቅጽ ላይ በጥንቃቄ መሙላት ይኖርባቸዋል፣
3. ከተጠቀሰው ሙያ ውጭ የሆነ የአገልግሎት ማስረጃ ለዚህ ውድድር የሚያዝ አይሆንም፣
4. ከቴክኒክና ሙያ በደረጃ ለሚቀርቡ የትምህርት ማስረጃዎች የብቃት ማረጋገጫ ወይም COC ተያይዞ መቅረብ አለበት፣
5. ከግል ድርጅቶች የሚቀርብ የሥራ ልምድ ማስረጃ ግብር የተከፈለበት መሆን ይኖርበታል፣
6. ሴት አመልካቾች ይበረታታሉ፣
7. የምዝገባ ቦታና ጊዜ፡- ይህ ማስታወቂያ ከወጣበትለ ቀን ጀምሮ ባሉት 5 ተከታታይ የሥራ ቀናት፣
8. የመመዝገቢያ ሰዓት ከጠዋቱ 3፡00-6፡00 ከሰዓት ከ8፡00-11፡00 ሰዓት 6 ኪሎ የካቲት 12 ሆስፒታል ፊት ለፊት በሚገኘው የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ፤
9. የሥራ ቦታ አዲስ አበባ፣

**የፕላንና ልማት ሚኒስቴር**